# የመንፈስ ፍሬዎች

## THE FRUTS OF THE SPRIT

የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ
ብፁዕ አቡነ ሺኖዳ ሣስተኛ እንደ ጻፉት።

ትርጉም ያዕቆብ ስንደቁ

አምስተኛ እትም ህዳር 2004 ዓ.ም

አድራሻ 0911 63 63 93
Email : yakobzz@yahoo.com

# መግቢያ

በአንድ ሰው ውስጥ ያለ መንፈስ የራሱ የሆነ ፍሬ ሊኖረው ይገባል።ጌታ«...ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።» /ማቴ7÷20/እንዳለ። በተጨማሪም «መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል»/ማቴ.7÷19/ በማለት አስተምሯል።

መልካም ፍሬ ሁሉ የመንፈስ ፍሬ እንጂ የሥጋ አይጠ ደለም። የአንድ ሰው መንፈስ ከእግዚአብሔር ጋር ሲሠራና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ወደ መተባበር ሲመጣ ፍሬን ያፈራል። 2ኛ.ቆሮ13÷4 እናም የአንድ ሰው መንፈስ ኅብረትን ካገኘ ሥጋንም ደግሞ በኅብረቱ ውስጥ እንዲሳተፍ ማድረግ ወደ መንፈሳዊ መንገድም መምራት ይችላል።

የመንፈስ ፍሬ ታዲያ ሥጋን የሚመራ የሰብአዊ መንፈስ ፍሬ ነው፤እንዲሁም ሁለቱም ሰብአዊ መንፈስና ሥጋ በአንድነት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ሥር የሚሆኑበት ነው።

ለምሳሌም«በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።»/ሮሜ.8÷14/ ስለዚህ የመንፈስ ፍሬ ማለት በመንፈስ ቅዱስ እና በሰብአዊ መንፈስ መካከል ያለ ኅብረት ማለት ነው፤ በውስጡ ካለው ከእግዚአብሔር መንፈስ ውጪ በራሱ ምንም ነገር መሥራት አይችልም።

ሰው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው የእግዚአብሔር መንፈስም በእርሱ ላይ ይኖራል /1ቆሮ. 3+16፣6-19/። የእግዚአብሔር መንፈስ በሰው ላይ ያድራል በእርሱም ውስጥ ይሠራል። ነገር ግን ሰው በእርሱ ውስጥ ለሠራለት ሥራ መልስ መስጠት አለበት ከዚህም በተጨማሪ ከእርሱ

# ምዕራፍ አንድ

# ፍቅር

«ፍቅር» ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ ነው። መለኮታዊ መንሳሳት በሐዋርያው በጳውሎስ እንደበት «የመንፈስ ፍሬ ፍቅር ደስታ፣ሰላም፣ትዕግሥት በጎነት፣ ቸርነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ራስን መግዛት ነው።»/ገላ5፥22-23/ ሲል ከገለጻቸው ውስጥ የመጀመሪያው የመንፈስ ፍሬ ፍቅር ነው። አሁን በዚህ የመጀመሪያ ፍሬ በሆነው ፍቅር ላይ እናተኩራለን።

ሰው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነና የእግዚ አብሔር መንፈስም በውስጡ እንደሚያድር ይታወቃል። ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስን ወደ እኛ የላከው በእኛ ውስጥ ለዘላለም እንዲያድር፤ በእኛ ውስጥ በእኛ በኩል እንዲሠራ፣ሥራውም ፍሬ እንዲያፈራ ላከው ይኸውም የመንፈስ ፍሬ ነው/1ቆሮ 3፥16 ዮሐ.14፥16-17/። የመጀመሪያዎቹ ሦስት ፍሬዎች ፍቅር፣ ደስታ፣ እና ሰላም ናቸው። በፍቅር እንጀምርና ከደስታና ሰላም ጋር ያለውን ግንኙነትም እናሳያለን ።

እጅግ ጠቃሚዎቹ የፍቅር ዓይነቶች የእግዚአብሔር ፍቅር እና ለመልካም ነገር ያለን ፍቅር ናቸው፤እያንዳንዳቸውም ወደሌላው ይመራሉ። የእግዚአብሔር ፍቅርለመልካም ነገርና ምግባር ወደሚደረግ ፍቅር ይመራል ይህም ወደ እግዚ አብሔር ፍቅር ይመራል።አንዱም ሌላውን ያጠነክራል።

አንድ ሰው መልካም ነገር ከወደደ ከክፋት ጋር አይታገልም። ብዙ ሰዎች ከኃጢአት ጋር በመታገል ወይም ሰይጣንን በመታገል ሕይወታቸውን ያባክናሉ።

የንሥሐ ሕይወትን ማግኘት ይፈልጋሉ:: ነገር ግን ይህ ከማንኛውም እነርሱ ከሚወዱት ኃጢአት ጋር እንዲቆዩ ያደርጋቸዋል:: በሌላ በኩል መልካምን የሚወድ ሰው ከንሥሐ ደረጃ በላይ ከፍ ይላል ኃጢአትን በመቃወም ይታገላል:: «ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛል::» የሚሉት ቃላት ጀማሪዎችን የሚመለከቱ ናቸው:: ሥጋን መቃወም አይፈልጉም መልካም ነገርን የሚወድ የንሥሐን ለማግኘት መታገል አያስፈልገውም ይልቁንም ትግሉ በእግዚአብሔር ፍቅር እና መልካም ነገርን በመውደድ ፍቅር ለማደግ ይሆናል::ገላ.5÷17

መልካም ነገርን ለመውደድ ፍላጎት ያለው መልካም ነገርን ለመመለስ አይታገልም ነገርግን የእርሱ ትግል የሚሆነው በእግዚአብሔር ፍቅርና መልካም- ነገርን በመውደድ ማደግ ነው:: የእንደዚህ ዓይነት ሰው ትግል የተቃውሞ ከመሆን ይልቅ አወንታዊ ነው:: ከፍላጎት አልባነት ይልቅ አዎንታዊነቱ የላቀ ነው:: ይህ ከአንድ የቅድስና ደረጃ ወደ ከፍተኛ ደረጃ መሸጋገር ነው::

ይህ መንፈሳዊ ትግል ፈጽሞ አድካሚ ሳይሆን ጣፋጭ ነው::

ከብርሃን ይልቅ ጨለማን የሚወድና መልካም ምግባርን የሚጠላ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ይዝላል:: ዮሐ 3÷19 ነገር ግን መልካምን የሚወድ እርሱ መጨረሻ ወደ ሌለበት የጌታ ሰንበት፣ ያለድካምም ከአንድ መልካም ነገር ወደ ሌላ ከፍተኛ መልካም ነገር ሊሸጋገር ወደ ሚችልበት ፍፃሜ ወደ ሌለው እረፍት ይገባል::

ግዴታ እ፡ደ አንድ ምግባር መልካም ነገር ማድረግ



ለሚወዱ ለተቀደሱ ሰዎች መልካም ለመሥራት ራሳቸውን ማስገደድ የተገባ አይደለም:: እነርሱ ማንም ድካምና ጫና ሳያደርግባቸው ፈጥነው መልካም ነገርን ያደርጋሉ::

መልካም ነገርን የሚወድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አክብዶ አይመለከትም:: ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፤ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል/መዝ1÷2/ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ «ትዕዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም::»/1ኛዮሐ.5÷3/ ብሏል:: እኛም ትእዛዛቱን የምንወዳቸው ከሆነ ይህ ስሜት ይሰማን እና «የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው፤ ልብንም ደስ ያሰኛል፤ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፤ ዓይንንም ያበራል»/መዝ 18÷8/ ማለት እንጀምራለን::

ጌታን እና መልካም ምግባርን የሚወድ ማንኛውም ሰው ሕግ ከሚጠይቀው የላቀ እና ወደ ፍቅር መንገድ ውስጥ የገባ ነው:: እንደዚህ ዓይነት ሰው ትእዛዝን ሳይጠብቅ መልካም ነገርን ይሠራል:: መልካም ባሕርይው መልካም ነገርን ለመሥራት ጥሪን እንዲጠባበቅ አያደርገውም ::

እንዲህ ያለው ሰው መልካምነት ባሕርይው ውስጥ ስላለና የእግዚአብሔር አምሳል ስለሆነ መልካም ነገርን ያደርጋል:: እንደ አንድ የተለመደ ነገር ወደ ውጪ እንደሚወጣ እስትንፋስ፣ ያልተለመደ አዲስ ነገር ወይም ከችሎታው በላይ እንደሚሠራ ዓይነት ስሜት ሳይሰማው መልካም ነገር ይሠራል:: በሥራው ከመኩራት ይልቅ የሚፈጽመውን ተግባር እንደተለመደ ሥራ ይመለከተዋል::

በተቃራኒው መልካምን የማይወድ የእግዚ አብሔር ትእዛዝ ከባድ ሆኖ ያገኘዋል፤ እርሱም የእግዚአብሔር ጠላት

ይሆናል። እግዚአብሔር በኃጢአት የሚገኘውን ደስታ እንደከለከለው፤ የእርሱም ትእዛዝ እንዳስጨነቀው፤ ወደ ማይፈልገው መንገድ እየመራው እንደሆነ ያስባል! ስለዚህ ለእርሱ የእግዚአብሔር መንገድ አስቸጋሪ ይሆንበታል በመንገዱም የሚጓዝ ከሆነ በኃይልና በግዴታ ይጓዛል።

ይህ ዓይነቱ ሰው በእግዚአብሔር ሕልውና የማያምን ነው። ምክንያቱም ይህ በእግዚአብሔር የማያምን ሰው በርሱ ሕልውና የእግዚአብሔር መኖር እንቅፋት እንደሆነበት እራሱን አሳምኗልና...።

በእግዚአብሔር የማያምን ከሆነ የመኖር ስሜት ሊሰማው አይችልም እኔ የምኖር ከሆነ እግዚአብሔር ባይኖር የተሻለ ነው ብሎ ሊናገር የቻለው፤ ለዚህ ዋናው ምክንያቱ እግዚአብሔርን አለመውደዱ ነው። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ የጠፋው ልጅ ከቤተሰቦቹ እርቆ ተጓዘ፤ በነፃነቱ መደሰት በፈለገ ጊዜ የአባቱን ቤት ጥሎ ሄደ።/ሉቃ 15÷13/

በሌላ በኩል መልካም ነገርን የሚወድ ፍቃዱ ከእግዚ አብሔር ፈቃድ ጋር ይስማማል እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር አይጣላም።እግዚአብሔርን ይወዳል የሚያስበውንም ነገር ከእርሱ ያገኛል። ሊያደርገው የተነሳሳበትን መልካም ነገር ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ብሎ ይወዳል። እግዚአብሔር የእርሱ ብቸኛ ምኞቱ እና ብቸኛ ደስታው ይሆናል።

- **መልካም ነገርን የሚወድ ዘላቂ በሆነ ደስታና ሰላም ውስጥ ይኖራል።**

በመጽሐፍ «ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ አሁንም ደስ ይበላችሁ።» /ፊሊ 4÷4/ ተብሎ



እንደተጻፈ መልካም ምኞትን የሚወድ ሰው በጌታ ደስ ይለዋል። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ከጌታ ጋር በመኖር ሐሴትን ስለሚያገኝ ነው። ከዚህም ጋር የጌታን ፍቃድ እንደ እርሱ ፍቃድ የእርሱም ስምምነትም ከጌታ ፍቃድ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ያገኘዋልና ደስ ይለዋል።

ታዲያ አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅርና መልካም ነገር ለማድረግ ያለውን ፍቅር የሚያጣው መቼ ነው? ይህ የሚሆነው ክፋትን ወደ ማወቅና ወደ መለማመድ እንዲሁም በእርሱም ደስታን ወደማግኘት ሲመጣ ነው።

የመጀመሪያውም ሰው በዲያቢሎስ ፈተና የወደቀበት መጥፎ ድርጊት ይህ ነበር። አዳምና ሔዋን ያውቁ የነበረው መልካምን ብቻ ነበር። ሰይጣን ግን መልካምንና ክፉን ወደ ማወቅ አመጣቸው።በእውቀታቸው ላይ ክፋትን ጨመረባቸው።ሰውም ክፋትን መለማመድ በእርሱና በክፋት መካከልም የፍቅር ግንኙነት መቀስቀስ ጀመረ። /ዘፍ 3÷5/

ሰው እንዳያውቃቸውና እንዳይለማመዳቸው የሚመረጡ ነገሮች አሉ። ስለእነዚህ ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስ «እውቀትንም የሚጨምር ሐዘንንም ይጨምራል» /መክ 1÷18/ ይላል። ሰይጣን ለሔዋን «ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ።»ዘፍ 3÷4-5 አላት ለእነርሱም በእንደዚያ ዓይነት እውቀት ዓይኖቻችሁ ባይከፈቱ የተሻለ ነበር።

ለሰው መልካም ብቻ ማወቁ እጅግ የተሻለ ነው፤ እርሱም በደስታና ሌሎችን በማፍቀር ይኖራል፤ ምክንያቱም በሰዎች ውስጥ መልካም ነገርን ብቻ ስለሚመለከት ሌሎችን ይወዳል። በዘለዓለማዊው መኖሪያ መልካምንና ክፉን

የማወቂያ ፍሬን ከውስጣችን የምናወጣበት ጊዜ ይመጣል:: እናም ታዲያ ከፋትን እንረሳለን የመልካም እውቀት ብቻም ይኖራል:: እግዚአብሔር ከፀሐይ በታች ንሥሓ የገባንበትን ማንኛውንም ክፋት ከአእምሮአችን ጠራርጎ ያወጣዋል:: መልካም ነገር ብቻ ይቀራል እርሱንም እናውቀዋለን፣ እናስበዋለን፣ እንቀምሰዋለን፣ እንወደዋለን እናም እንተገብረዋለን:: በኃይል ሳይሆን፣ በትእዛዝ ተገደንም ሳይሆን ወይም ለማድረግ የመታዘዝ ስሜት እየተሰማን ሳይሆን በደስታና በእውነተኛ ውሳጣዊ መንፈስ መልካም ነገር ማድረግ አለብን:: ይልቁንም ለማፍቀር ለመውደድ ስንል መልካም ነገር መሥራት አለብን::

ምን ያህል መልካም ነገር እንደፈጸምህ ለማየት ሥራ ዎችህ በዘለዓለማዊነት ውስጥ ባሉ ደረጃዎች በተቀመጡ ጊዜ በውስጣቸው ያለውን ፍቅር እግዚአብሔር እንደሚለካ እርግ ጠኛ ሁን! እግዚአብሔር የሚቀበለውና ስለ እርሱም ምክንያት በእግዚአብሔር የምትሸለምበት ፍቅር ይህ ነው::

ይህ በሕይወታችን እና በሥራዎቻችን እንዴት ተግባራዊ ይሆናል? ለምሳሌ አገልግሎትን ውሰድ አገልግሎት ዝም ብሎ ሥራ፣ እንቅስቃሴ ወይም ስብከት አይደለም:: ነገር ግን ሰዎችን ስለምትወዳቸው እና እንዲድኑ ስለምትፈልግ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እና መንግሥት እንዲስፋፋ ስለምትወድ፤ እነርሱን የሚወዳቸውን እግዚአብሔርን ስለምትወድ እና እነርሱም እርሱን እንዲሁ እንዲወዱ ስለምትፈልግ ታገለግላቸዋለህ እንደዚህ ከሆነ በእርግጠኝነት እግዚአብሔር ያንን ፍቅር በአገልግሎትህ ውስጥ ያበዛል:: በአገልግሎት ውስጥ ስኬትን የሚጎናጸፈው ማን ነው? አገልግሎትን እንደተቀደሰ ፍቅር፣ለእግዚአብሔር እንደሆነ



ፍቅር እና በአገልግሎቱ ለሚያገለግላቸው እንደሆነ ፍቅር አድርጎ የሚገነዘብ እርሱ እንጂ::

- ለመስጠት እንዲሁ ተመሳሳይ ነገር ተግባራዊ ይደረጋል::

መስጠት ወይም ልግስና ትእዛዙን ሟሟላት ብቻ አይደለም መጽሐፍ ቅዱስ «እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና::» /2ቆሮ9÷7/ እንዲል:: እግዚአብሔር የምትሰጠውን ገንዘብ ሳይሆን የመጀመሪያውን ፍሬ እና ቃልኪዳን የሆነውን ከማዕረጎች ሁሉ የሚልቀውንና ያለ ነቀፋ በነፃነት የሚሰጠውን ፍቅር ከአንተ ይጠብቃል ::

ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያ ፍሬ ነው:: ስለዚህ ጌታ የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን በነቀፋ ንሥሐም እንዲገባ በጠራው ጊዜ ነቀፋውን የተወሰነ ኃጢአትን በመግለጽ ሳይሆን በአንድ ሐረግ አጠቃልሎ «ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና::»/ራዕ 2÷4/ በማለት ነው::

እግዚአብሔር ይህንን ፍቅር ይፈልጋል ስለዚህም «ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ ዓይኖችህም መንገዴን ይውደዱ» /ምሳ 23÷26/ አለ:: ትእዛዙን መፈጸም የፍቅር ተፈጥሮአዊ ፍሬ ነው::

ውጪያዊ የንሥሓ ሕይወትን ብቻ የሚኖሩ ነገር ግን ውስጣዊ ፍቅር የሌላቸው ይወድቃሉ:: ምክንያቱም ሥራ ዎቻቸውና ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ፍቅር የጎደለው ነውና::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሕግ ማኛይቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት ? ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጠው መልስ «ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም

አሳብህም ውደድ።ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች እርስዋም ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት ። አሪትና ነቢያት በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸኑ ።» /ማቴ 22÷36-40/ የሚል ነበር።

በዚያን ቀን ብዙዎቹ«ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንም በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን...? » /ማቴ7÷22/ ይሉታል። ነገር ግን እርሱ ይህን ሁሉ ትቶ በውስጣቸው ስላለው ፍቅር ይጠይቃቸዋል።

ይህ የተአምራት እና የስጦታዎች ችግር አይደለም። ባሏቸው በተሰጡአቸው ስጦታዎች የተነሳ የሚጠፉ ብዙዎች ናቸውና። ለዚያ ነው ሐዋርያት ስለመንፈሳዊ ስጦታዎች ባወሩ ጊዜ ሁሉ ይህንን ከሁሉ ይልቅ በተሻለ መንገድ አብራርተውታል 1ኛ ቆሮ 1÷3።

- **እግዚአብሔርን እስከ ወደድነው ድረስ ደስታችን እና እርካታችን ዘላለማዊ ይሆናል።**

«በክብር አንድ ኮከብ ከሌላው ኮከብ ይለያል።» /1ቆሮ 15÷41/ ፍቅርንም እንዲሁ ይህ ሊገልጸው ይችላል። እግዚአብሔርን ከወደድህ አትፈራም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላልና ይህ ፍቅር ካለህ እግዚአብሔርን አትፈራም ኃጢያትንም ሰዎችንም ሞትንም እንኳን አትፈራም።

ከፍቅር ጋር በመሆን ሰው በማያቋርጥ ደስታ ከአንድ መልካም ነገር ወደሌላው በሚደረግ የድል ሂደት ውስጥ እርሱን በሚመራው በጌታ ደስታ እና ከጌታ ጋር ባለው ሕይወት በሚደሰተው ደስታ በልቡም ውስጥ ኃጢአት ቦታ የሌለው በመሆኑ ምክንያት በሚያገኘው ደስታ ውስጥ ይኖራ



ል።

ከዲያቢሎስ የሚመጡ አንዳንድ ውጊያዎች እና ትግሎች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ነገር ግን እነዚህ ውጪያዊ መሰናክሎች ሲሆኑ ውስጣዊ የሆነ በብዛት የሚገኝ ሰላም ግን ከውስጥ አለ።

በእንደዚህ ዓይነት ፍቅር ውስጥ ራስህን እንድታለማምድ እፈልጋለሁ። ውጪያዊ ከሆነ የመንፈሳዊነት ልምምድ ውጣና ወደ ፍቅር ጥልቅ ስሜት ውስጥ ግባ። ፍቅር ፈጽሞ አይወድቅም።

ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታውን ክዶ እንደማያውቀውም ምሎ ተናገረ። ጌታችን ግን አንዲት ጥያቄ ብቻ ጠየቀው «ትወደኛለህን?» የሚል። ቅዱስ ጴጥሮስም አለ «ጌታ ሆይ አንተ ሁሉን ታውቃለህ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ።» አለው። /ዮሐ 21÷15-17 ቅዱስ ጴጥሮስ በዚያ ፍቅር ይቅርታን ተቀበለ በሐዋርያት ዘንድ የነበረውን ደረጃውንም አስመለሰ።

በዚህ መጽሐፌ ስለ ፍቅር ጥልቅ የሆነ ነገር አልጽፍም ምክንያቱም ስለ ፍቅር የሚያስተምር ከዚህ በፊት ያዘጋጀሁት ሌላ መጽሐፍ አለና።

ተሰጥኦ ጋር ውህደት የፈጠረ ደስታ ነው።

- **አንዳንድ ሰዎች በኃጢአት ይደሰታሉ !**

በዚህ ሁናቴ ደስታ በእነዚህ ሰዎች በኃጢአቶቻቸው ላይ የተጨመረ ሌላ ኃጢአት ነው። ይህም ሐዋርያው «...ክብራቸው በነውራቸው ነው አሳባቸው ምድራዊ ነው።» ሲል የገለጻቸውን ያሳስበናል። /ፊል.3÷19/ ሌሎች የተወሰኑት ደግሞ በቁሳዊ ነገሮች ይደሰታሉ። የጠፋው ልጅ በተመለሰ ጊዜ ያልተደሰተው ታላቁ ወንድሙ የነዚህ ሰዎች ምሳሌ ነው። ይልቁንም «...ለእኔም ከወዳጆቼ ጋር ደስ እንዲለኝ አንድ ጥቦት ስንኳ አልሰጠኸኝም።»/ሉቃ15÷29/ በማለት አባቱን ወቅሷል። ጥቦት በማግኘት የሚደሰት እንደዚህ ዓይነት ሰው በእርግጠኝነት የዘቀጠ መንፈሳዊነት ያለው እና ምኞቶቹም ሁሉ ምድራዊ የሆኑ ናቸው።

ጠቢቡ ሰሎሞን ይህንን የደስታ ዓይነት በሕይወቱ አሳልፏል። «ዓይኖቼንም ከፈለጉት ሁሉ አልከለከልኳቸውም» ብሏል። ስለዚህ የጥበብ ቃሉን «....የደስታ ፍጻሜ ልቅሶ ነው»፣ «ልብ ለሌለው ሰው ስንፍና ደስታ ናት»፣ «የጠቢባን ልብ በልቅሶ ቤት ነው»/ምሳ.14÷13፤15÷21 መክ.7÷4/ ሲል የእውቀት ቃሉን ተናግሯል። በእርግጥም ይህንን ሁሉ ማለቱ የውሸት ደስታ እና ስሕተት የሆነ የሥሜቶች እና የሥጋ ጊዜያዊ ልቅሶ ወይም መንፈሳዊ ያልሆነ ደስታን ማለቱ ነው። ይህ ታዲያ መንፈሳዊ ደስታ ምንድር ነው? ወደሚል ጥያቄ ያመጣናል።

## መንፈሳዊ ደስታ

1. መንፈሳዊ ደስታ በጌታ በእርሱ ሕልውና እና ጥበቃ ውስጥ በመሆን እና ከእርሱም ጋር በመገናኘት መደሰት



ነው። ደቀመዛሙርት«ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው።» «እንደገና አያችኋለሁ ልባችሁም ደስ ይለዋል ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም» ብሏቸዋልና።/ዮሐ16÷22ዮሐ.20÷20/በዚህ ደስታ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ።» /ፊል4÷4/ ብሏል።

በጌታ መደሰት ማለት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እየነገራቸው ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እንደነበረ ሁሉ ሁልጊዜ ከእኛም ጋር እንደሆነ ሲሰማን ነው። /ሐዋ1÷3/ በአንተ እና በሌሎች ሕይወት ውስጥ ባለው የእግዚአብሔር ሕልውና ተደስተሃልን ? ዘወትር ራስህን ጠይቅ ? ደስታህ ከጌታ ጋር በመሆንህ ነው? ወይስ በሌሎች ምክንያቶች ?

2. ድንግል ማርያም ይህንን በጌታ ያለ መንፈሳዊ ደስታ ታውቃለች። ይህንንም በመዝሙሯ «ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደጋለች።»/ሉቃ1÷47/ስትል ገልጻዋለች።

ቅድስት ድንግል ማርያም በጌታና በእርሱ ማዳን ደስተኛ ነበረች። አንተስ? በድኅነት ሥራ ይኸውም ለአንተ ሲል ራሱን መሥዋዕት ባደረገበት ካሳ ሐሴት አድርገሃል ?ቤተ ክርስቲያን በየዕለቱ በስድስተኛው ሰዓት ጸሎቷ በዚህ የድኅነት ሥራ መደሰት እንዳለብን ታሳስበናለች። ስለዚህም ኃጢአቶቻችንን ሁሉ በፋቀበት፣ ባስወገደበት ካሳ እና ባጠበበት ውድ ደሙ እንደሰታለን። ጌታ አምላካችን በደሙ ገዝቶናልና፤ የእርሱ ሆነናልና፤ከእርሱም ጋር ታርቀናልና እንደሰታለን።

3. የመንፈሳዊ ደስታ ሌላው ምሳሌ በንሥሓና ኃጢአትን

በማስወገድ የሚገኝ ደስታ ነው:: ይህ የአንድ ሰው ተደጋጋሚ ከሆኑ ኃጢአቶች ወይም ተገዢ ከሆነበት መጥፎ ልማድ ነፃ የመውጣት እና በንሥሐና ድል የመንሳት ይቅርታንም የማግኘት ደስታ ነው:: ይህ ደስታ የጠፋው ልጅ ወደ አባቱ ቤት በመመለሱ የተደሰተው ደስታ ነው::/ሉቃ 15/

ነቢዩ ዳዊት ምን እንዳለ ተመልከት «በሂሶጵ እርጨኝ እነጻማለሁ እጠበኝ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ:: ሐሴትንና ደስታን አሰማኝ የሰበርሃቸውም አጥንቶቼ ደስ ይላቸዋል::» /መዝ. 51÷8-12/

ይልቁንም ለረዥም ጊዜ በእርሱ ላይ ከሰለጠነበት መጥፎ ልማድ ወይም በተደጋጋሚ ንሥሐ ከገባበት እና ከተሸነፈበት ኃጢአት ነፃ የወጣ ሰው እንዴት በደስታ የተሞላ ነው? ከሱስ ነፃ የወጣ፣ ከክፋት አስተሳሰቦች እና ከተበከሉ ሕልሞች የፀዳ ሰው እንዴት ደስተኛ ነው!

4. ራስን ማሸነፍ ታላቅ ነገር ነው!

ራስን ማሸነፍ ሌሎችን ከማሸነፍ በላቀ ሁኔታ የተሻለ ነው በዚህ አንድ ሰው ውስጡ ነፃነትን ይሆናልና:: ስለዚህ ጠቢቡ ሰሎሞን እንዲህ ብሏል «ትእግስተኛ ሰው ከኃይለኛ ሰው ይሻላል በመንፈሱም ላይ የሚገዛ ከተማ ከሚወስድ ይበልጣል::»/ምሳ16÷32/ ራሱን የሚበቀል ሰው ራሱን እንደሚገዛ እና ጽናት እንዳለው ሰው ደስተኛ አይደለም ለዚህም ነው ነቢዩ ዳዊት አቢግያን ልኮ ወደ ደም እንዳይሄድ በእጁም በቀል እንዳያደርግ የከለከላቸውን የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር በማመስገን የተደሰተው /1ሳሙ.25÷



32-33/

5. በኃጢአተኛ መመለስ የሚገኝ ደስታም አለ

ይህ ደስታ መጽሐፍ ቅዱስ «...ንሥሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል...»/ሉቃ15÷7/ እንደሚል በምድር ብቻ ሳይሆን በሰማይም የሚደረግ ደስታ ነው:: የጠፋው ልጅ አባትም «ይህ ወንድምህ ሞቶ ነበረ ሕያው ስለሆነ ጠፍቶም ነበር ስለተገኘ ደስ እንዲለን ፍሥሐም እንድናደርግ ይገባናል::»አለ /ሉቃ 15÷32/ በሌላም ስፍራ አንድም ድሪም የጠፋባት ሴትም ባገኘችው ጊዜ ወዳጆችዋንና ጎረቤቶችዋን ጠርታ ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ ትላቸዋለች /ሉቃ 15÷8-9/ በማለት ተጽፎአል::

የጠፉ ኃጢአተኞችን መፈለግና መመለስ እንዴት ያለ ታላቅ ደስታ ነው? ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ኢየሱስ ክርስቶስ የማስታረቅም አገልግሎት ሰጠን በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ እንለምናለን::»/2ቆሮ5÷18-20/ እንዳለ ይህ የአንዳንድ ሰዎች አገልግሎት ነው:: አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሲታረቅ ደስ ይለናል:: ስለዚህ ለዚህ አገልግሎት ከሰማይ የሚሰጥ ሽልማት ባሻገር በተጨማሪ በምድርም ደስታ አለ:: ዳግመኛም መጽሐፍ ቅዱስ «ወንድሞች ሆይ ከእናንተ ማንም ከእውነት ቢስት አንዱም ቢመልሰው ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን የኃጢአትንም ብዛት እንዲሸፍን ይወቅ::»/ያዕ.5÷20/ ይላል:: ነፍስን ከሞት ያዳነ ወይም ሃይማኖቱን የካደን የመለሰ ወይም የጠፋች ሴትን የመለሰ ጥልቅ የሆነ ደስታ በእርግጥ አለው::

6.የራሱ የሆነ ማንኛውንም መልካም ተግባር ፈጽሞ በመፈፀም የሚገኝ ደስታ ይኖርኃል።

መልካም ሥራ በምድር እና በሰማይ ደስታን ያመጣል። ድሃ የሆኑ ሰዎችን በምትረዳበት ጊዜ ድሃ ቤተሰቦችን እንዲ ደሰቱ በምታደርግበት ጊዜ ወይም በችግር ውስጥ ያለን ሰው ምቾት እንዲሰማው በምታደርግበት ጊዜ በእርግጠኝነት ትደስታለህ። የተሰበረ ልብን ደስተኛ በማድረግህ ወይም ለተጨነቀ ሰው ፍትህን በመስጠትህ ውስጣዊ ደስታ ይሰማሃል፤ ለእንስሳት እንኳን መልካም ስታደርግ ደስታ ይሰማሃል።

በሥነ ጽሑፍ የሚጠቀስ አንድ ሰው አንድ ጊዜ ይህን በተመለከተ «ዛፌን ውሃ አጠጣታለሁ ነገር ግን የምሥጋና ቃል ለእኔ አትሰጠኝም። ይሁንና ዛፏ ሕይወት ስትዘራ ሳያት እኔም ሕይወት እዘራለሁ» ብሏል። በተመሳሳይ ሁኔታ እናት ልጇ ስኬታማ ሆኖ በምታይበት ጊዜ ትደሰታለች። ሌሎችን ደስተኛ ማድረግ ደስታ ነው።

አሥራትን ያለ ፍቃዱ የሚሰጥ ይህንን ደስታ አያገኝም። ቢከፍልም እንኳን የሚከፈለው አስራት እግዚ አብሔር ዘንድ አይደርስም «እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠ ውን ይወዳልና» /2ቆሮ 9፥7/ ለመስጠት ደስተኛ በሆነ ልብ የሚሰጥን እርሱ ይወዳል ይህንን የመስጠት ደስታ በሕ ይወትህ ውስጥ ሞክር።ሌላው ዓይነት የአባቶችና የመሪዎች መንፈሳዊ ደስታ ነው።

7. የመንፈሳዊ አባቶች እና መሪዎች ደስታ

ቅዱስ ዮሐንስ ለተወዳጁ ለጋይዮስ በመልእክቱ «ወዳጅ ሆይ ነፍስህ እንደሚከናወን በነገረ ሁሉ እንዲከናወንልህና



ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ። ወንድሞች መጥተው አንተ በእውነት እንደምትሄድ ስለ እውነትህ ሲመሰክሩ እጅግ ደስ ብሎኛልና። ልጆቼ በእውነት እንዲሄዱ ከመስማት ይልቅ የሚበልጥ ደስታ የለኝም።/3ዮሐ2፥4/ ብሏል። ይህ ከአገልግሎት የሚገኝ ደስታ ክፍል ነው። ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው ይህንኑ የደስታ እንጂ በኃዘን እንዲ ያደርጉት ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና ስለነፍሳችሁ ይተጋሉ።» ብሏል።/ዕብ 13፥17/

አንድ መንፈሳዊ መሪ ልጆቹ መንፈሳዊነትን ሲያከብሩ ማየትን ይወዳል። በእርሱ ይደሰታል አገልግሎቱ ፍሬ በማፍራቱም በራሱ ይደሰታል። በሌላ በኩል አባቱን ወይም መሪውን የማይታዘዝ ልጅ ወይም ከእነርሱ ጋር የማይስማማ እና የማይገዛ እነርሱን የማያከብር በእጅጉ ያሳዝናቸዋል። በተቃራኒው የሚታዘዝ እና የምክር ቃልን የሚቀበል ልጅ ዘወትር ፍሬ ይሰጣል። እንደዚህ አይነት ሰው ፊሊጶስን የሰማውን፣ እምነት የተቀበለውን እና የተጠመቀውን፣ «ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ የነበረውን» ኢትዮጲያዊውን ጃንደረባ ያስታውሰናል። /ሐዋ8፥39/

በሌሎች ደስታ እንደሰት በጥልቅ ስሜትም ደስታቸውን እንካፈል። አንድ ሕፃን ብዙ ሰዎች ልደቱን ለማክበር ዙሪያውን ከበው በደስታ ለእርሱ በሚዘምሩለት ጊዜ ታላቅ ደስታ ይሰማዋል። ታላላቆችም ቢሆኑ የደስታ በዓላቸውን የተወሰኑ ሰዎች ተገኝተው አብረዋቸው ከነርሱ ጋር በሚያከብሩበት ጊዜ ይደሰታሉ።

ይህ ደስታ የሰላም መሥዋዕትን ያስታውሰናል። ዐአብዛኛው ይህን መሥዋዕት የሚከፍሉት መሥዋዕቱን

የሚያቀርቡትና በጌታ ሥራ ደስተኞች የሆኑት፣ የምሥጋና ተሳትፎም ያላቸው ባልንጀሮቻቸው ናቸው።/ዘሌ 7÷12-19/ ጳግመኛ ይህ ለሊቀ መልአኩ ሚካኤል እንደምስጋና መሥዋዕት ሆኖ የተዘጋጀውን እርሾ ያለበትን የጸዲቅ ኅብስት ያስታውሰናል። በመልአኩ ተዓምር ስለተሰራላቸው ከእነርሱ ጋር እንዲደሰቱ ይህን ህብስት ሰርተው ለባልንጀሮቻቸው ይልኩላቸዋል ከሌሎች ጋር መደሰታችን እኛ ሁላችንም አንድ ቤተሰብ እንድንሆን እንዲሰማን ያደርገናል።

8.ታላቁ የደስታ ማዕረግ መከራዎች ለቡራኬያት እና ለአክሊላት መሆናቸውን በማመን መደሰት ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ «...ልዩ ልዩ ፈተና ቢደር ስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት» /ያዕ 1÷2/ ብሏል። ፈተናዎችን መሸከም መታገስ ብቻ ሳይሆን በፈተናዎችም መደሰት አለብን። በመስቀሉ፣ በጠባቧ በር፣ በሥቃይ እና በስደት ሁሉ እንደሰታለን። በጌታ እና መከራውን በመካፈልም መደሰት አለብን /ፊል.3÷10/ በእርግጠኝነት ከእርሱ ጋር መከራውን ብንቀበል ከእነርሱ ጋር አብረን እንከብራለን። /ሮሜ.8÷17/ በእምነት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲ ደረግ እናውቃለን። /ሮሜ8÷28/ የምንቀበለውን መከራ ብቻ አንመልከት ይልቁንም ጌታ የሚያደርገውን በተስፋ እንመልከት ስለዚህ ሐዋርያው «በተስፋ ደስ ይበላችሁ» /ሮሜ13÷12/ ብሏል።

9. በተስፋ መደሰት /ሮሜ 12÷12/

ወደፊት ሊፈጸም በሚችል ነገር ውስጥ ያለ ተስፋ እግዚ አብሔር ጣልቃ ከሚገባበት እና ከሚሠራበት እምነት



ይመጣል። ይህም መዝሙረኛው «በአንተ የሚታመኑት ሁሉ ደስ ይላቸዋል።»/መዝ5÷11/ እንዳለው ልብን ደስተኛ ያደርጋል። እምነቱን በጌታ የሚጥል አይሸነፍም ጌታ የሚሰ ጠው ደስታ በውስጡ ይሰማዋል እንጂ አይሸነፍም።

የእግዚአብሔር ልጆች በማያቋርጥ ደስታ ውስጥ ይኖራሉ ደስታ የመንፈስ ፍሬ ነውና።

የመንፈስ ፍሬ ፍቅር፣ደስታ፣ሰላም...ወዘተ ነው/ገላ5÷22/ እግዚአብሔርን የሚወድ እና በእግዚአብሔር የሚወደድ መንፈሳዊ ሰው ሁልጊዜ ደስተኛ ነው። በምንም ሁኔታ ይሁን በምንም እግዚአብሔር በእርግጠኝነት እንደሚሠራለት ይሰማዋል በእርሱም ሥራ ይደሰታል። በእርግጥም እግዚ አብሔር ሥራውን ባናየውም እንኳን ይሠራል። ሥራውን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ልናየው እንችላለን በዚህም እንደሰታለን። ይህን ደስታችንም ማንም አይወስድብንም። ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጆች የሚደሰቱት በስጦታዎቹ ብቻ ሳይሆን በራሱ በጌታም ነው።

10. በአገልግሎት ስኬታማነት የሚገኝ ደስታ

መጥምቁ ዮሐንስ በጌታ አገልግሎት እና በአገልግሎቱ ስኬት ተደስቷል። ስለዚህ መጥምቁ «ሙሽራይቱ ያላቸው እርሱ ሙሽራ ነው ቆሞ የሚሰማው ሚዜው ግን በሙሽራው ድምፅ እጅግ ደስ ይለዋል። እንግዲህ ይህ ደስታዬ ተፈ ጸመ።» ብሏል። /ዮሐ3÷29/ መጥምቁ የአገልግሎቱ መጨረሻ በዚህ ቢያልቅም ሙሽራይቱን በሙሽራው እጅ በማስረከቡ ምክንያት ተደስቷል። ይህ ደስታ ከራስ ምኞት ነፃ የሆነ መንፈሳዊ ደስታ ነው። በሌላ በኩል ራስ ወዳድ ሰው ብቸኛው አገልጋይ እርሱ ብቻ ይመስለዋል። ከዚህ

በኋላ ፉክክር እና ቅናት በአገልጋዮች መካከል ይመጣል በሌላው ሥራ የሚደሰትም ማንም አይኖርም፡፡

ዘሩባቤል ቤተ መቅደሱን በታላቅ ድካም በገነባ ጊዜ ሰዎች ምን ያህል ደስተኛ እንደነበሩ መገመት ያስቸግራል! መጽሐፍ ቅዱስ ያንን ደስታ «...ይህ መቅደስ በፊታቸው በተመሠረተ ጊዜ በታላቅ ድምፅ ያለቅሱ ነበር ብዙ ሰዎችም በደስታ ይጮኹ ነበር ደስ ብሎአቸው የሚጮኹትን ድምፅ ከሕዝቡ ልቅሶ ድምፅ መለየት የሚችል አልነበረም፡፡»/ዕዝ 3 ÷12-13/

«በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ያጭዳሉ»መዝ12÷65 የሚለው የመዝሙረኛው ቃል በእርግጥም እውነት ነው፡፡ በጌታ ሥፍራ የሚሠሩ ከፍሬው የተነሳ ደስተኞች ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ለአገልግሎት ብዙ ቢደክሙምሐዋርያው «ኀዘንተኞች ስንሆን ዘወትር ደስ ይለናል፡፡» እንዳለው ድካማቸው ደስታቸውን ይጨምርላቸዋል፡፡ 2ኛቆሮ6÷10

በውጪያዊው እኛነታችን ከአገልግሎት ድካምና ሥቃይ የተነሳ ኀዘንተኞች ልንመስል እንችላለን ነገር ግን በውስጣችን በትክክል ደስተኞች ነን፡፡ ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «አሁን በመከራዬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል» አለ፡፡

11. እያንዳንዱ ሰው በድካሙ ፍሬ እና ጌታ ለእርሱ በሠራ ለት ሥራ ይደሰታል፡፡

የዳዊት መዝሙር «እግዚአብሔር ታላቅ ነገርን አደረገልን ደስም አለን፡፡» /መዝ12÷63/ ይላል፡፡ እዚህ ላይ ቃሉ ምስጋናን ያመለክታል፡፡ መዝሙር /102/ በዚህ ታላቅ



ደስታ የተሞላ ነው፡፡ «ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ፡፡» ከጌታ ጋር የሚሠራ ሁሉ ከእርሱ ጋር በመሠረቱ ሥራውም የሚጠፋ ባለመሆኑ ይደሰታል፡፡ ጌታም « የሚዘራና የሚያጭድ አብረው ደስ ይላቸዋል» ዮሐ4÷36 ይላል፡፡

12.መንፈሳዊ ሰው በሌሎች ደስታ ደስ ይለዋል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ «ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ» /ሮሜ 11÷5/ ሲል ያዝዘናል፡፡ እኛ አንድ አካል ነን አንድ ሰው ቢሠቃይም ሌሎቹ ሰዎች ከርሱ ጋር ይሠቃያሉ ፡ እንዲሁም እርሱ ቢደሰት ሌላውም ከእርሱ ጋር እና በእርሱ ይደሰታሉ፡፡ በሰዎች ደስታ መካፈል መልካም ምግባር ነው፡፡ መካን የነበረችው ኤልሳቤጥ ጎረቤቶችዋም ዘመዶችዋም ጌታ ምህረቱን እንዳደረገላት ሰምተው ከእርስዋ ጋር ደስ አላቸው፡፡ /ሉቃ15÷8/

ይሁንና ስጦታዎችን በመቀበል ብቻ መደሰት አደገኛ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ስጦታዎች ካልተሰጡን ወይም ከዘገዩ ልብ ሊለወጥ ወይም ኃዘን ሊሰማው እና ሰውዬው ጌታን በመጸረር የሚያማርር ሊሆን ይችላልና፡፡ ስለዚህ መንፈሳዊ ሰዎች በስጦታው በራሱ ሳይሆን ይልቁንም በሰው በእግዚ አብሔር ፍቅር እና ትሕትና ይደሰታሉ፡፡ ስለዚህ ሁል ጊዜ በጌታ ደስ ይላቸዋል፡፡

በአባታዊ ጥበቃውና በሚያሟላላቸው ፍላጎቶቻቸው መ ጠን ደስ ይላቸዋል፡፡ ምንም እንኳን ስጦታውን ባያዩትም ሁል ጊዜ ይሰጣቸዋልና በዚህ እግርጠኛ በመሆን በፍቅሩ ደስ ይላቸዋል፡፡

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ይነሳል፡- ሞት የደስታ ወይስ የኀዘን ወይስ የፍርሃት ምክንያት ነው? «ልሄድ ከክርስቶስ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነው።»/ፊል1÷24/ በማለት ለመሞት እንደተመኘው እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከሞት በኋላ ስላላቸው ዕጣ ፋንታ እርግጠኞች ለሆኑት ለእነርሱ ሞት የመንፈሳዊ ደስታ ምክንያት ነው። «ጌታ ሆይ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን ታሰናብተዋለህ ዓይኖቼ ማዳንህን አይተዋልና።» /ሉቃ 2÷29 -30/ ሲል የተናገረው ታላቁ ስምዖን ሌላው ምሳሌ ነው።

በሌላ በኩል ጌታን ፊት ለፊት ለማየት ያልተዘጋጁት ሞትን እና ከሞት በኋላ ያለውን ሁሉን ይፈራሉ። የእነርሱ አለመዘጋጀት በሞት ከመደሰት ይከለክላቸዋል። በአጠቃላይ ኃጢአት መንፈሳዊ ደስታን ይደብቃል።



# ምዕራፍ ሦስት

# ሰላም

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የገለጸው የመንፈስ ፍሬ ፍቅርን፣ደስታናሰላምን.../ገላ.5÷22/ያጠቃልላል። አስቀድመን ስለ ፍቅር እና ደስታ ተነጋግረናል አሁን ደግሞ ወደ ሰላም እንሸጋገራለን።

በቅድሚያ በቅዱስ መጽሐፍ፣ በጸሎት እና በሕይወታችን ሰላም ያለውን አስፈላጊነት እና ጥቅም በማግለጽ እንጀምር። በመቀጠልም ስለ ሰላም ሦስት መሠረታዊ ነገሮችን እንጽፋለን፡

- ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እና ከእግዚአብሔር የሚገኝ ሰላም
- ሰላም ከሰዎች ጋር
- ከራስ ጋር የሚደረግ በልብ ያለ ውስጣዊ ሰላም

### የሰላም አስፈላጊነት

ሰላም ለሰዎች ሕይወት በጣም አስፈላጊ ነው። ከሰላም ውጪ ማኅበረሰብ ሊረጋጋ አይችልም በጸጥታ የሚኖር ሰው የለም አይኖርም።ስለዚህም ሰላም የሁሉም መንግሥታት እና ብሔሮች ፍላጎት ነው ያለሰላም በጸጥታ ሊኖሩ አይችሉምና ። ያለ እርሱም ዓለም በሙሉ በዱርነት ሕግ ሥር የምትተዳደር ትሆናለች።

- እግዚአብሔር ሰላም እንዲኖረን ይፈልጋል እርሱንም ሰጥቶናል።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ «ሰላምን እተውላችኋለሁ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ ልባችሁ አይታወክ አይፍራም» /ዮሐ14+27/ ብሏቸዋል:: ይህ የወንጌል ክፍል በየዕለቱ በሦሥተኛው ሰዓት ጸሎት የምን ጸልየው ነው:: በዚህም ምክንያት ስለ ሰላም ራሳችንን እንድናሳስብ ያደረገናል:: ልባችንም መሰናከል አይገጥመውም ወይም አንፈራም::

ሰላም ቅዱሳን መላእክት በጌታችን ልደት ዕለት «ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር...» /ሉቃ 3+14/ እያሉ የዘመሩት መዝሙር ነው:: በሥርዓተ ቅዳሴም ጊዜ «ሰላም ለሁላችሁ ይሁን» የሚለው ቃል በሚቀድሰው ካህን ቅዳሴው እስኪያልቅ ድረስ ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ የሚሰጥ ብራኬ ነው ::

ካህኑ በእያንዳንዱ በቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ጸሎት መጀመሪያ ላይ፣ በንሥሐ ጸሎት መጀመሪያ ላይ እና በቅዳሴ ውስጥ ብዙ ጊዜ ይህንን ቃል ይለዋል:: ካህኑ ሰላም በሁሉም ምዕመናን ልቦና ውስጥ እንዲሆን ይጸልያል:: ያለ እርሱ ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ እና ከሌሎች ጋር በሚያ ደርጓቸው ስምምነቶች ውስጥ ዋናውን መሠረታዊ ነገር ያጣሉና::

ዳግመኛም ሰላም በሰዎች መካከል ያለ ዕለታዊ ሰላምታ ነው:: ይህ ሰላም ከጌታ እና ከመላእክቱ የሚመጣ፣ የሚፈስ ነው::

ጌታ ከትንሣኤው በኋላ ሁለቱን ማርያም ባገኛቸው ጊዜ ሰላምን ሰጣቸው /ማቴ 28÷9/ ደቀመዛሙርቱ ተሰብስበው በነበሩበት በመምጣት«ሰላም ለእናንተ ይሁን» /ዮሐ 20+19/



ብሏቸዋል:: ይህ ቃል በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፎች ውስጥ ሦስት ጊዜ ተደግሟል:: / ሉቃ 24+36 ተመልከት/

ዳግመኛም ጌታ ደቀመዛሙርቱን ሲልክ ወደ ምትገቡበት ቤት ሁሉ አስቀድማችሁ ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን በሉ:: በዚያም የሰላም ልጅ ቢኖር ሰላማችሁ ያድርበታል አለዚያም ይመለስላችኋል ብሏቸዋል::/ሉቃ 10+5-6/

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቅድስት ኤልሳቤጥን በጎበኘችበት ወቅት ሰላምታ በመስጠት ነው የጀመረችው:: «ስለዚህ ኤልሳቤጥ የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ጽንሱ በማህጸን ዘለለ በእርሷም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት::»/ሉቃ1+41/ ያ ሰላምታ እንዴት በመንፈሳዊ ኃይል የተሞላ እንደነበር ይደንቃል!

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም እንዲሁ የጌታን ልደት ለቅድስት ድንግል ማርያም ባበሰራት ጊዜ በተመሳሳይ ሰላምታ ሰጥቷታል:: /ሉቃ1+28/

አባቶቻችን ሐዋርያትም መልእክቶቻቸውን ለመጀመር «ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን» የሚል ቃልን ተጠቅመዋል:: /ሮሜ 1+7 1ቆሮ1+2 2ቆሮ 1+2 ገላ 1+3 ኤፌ1+2 ሮሜ.16+1 3ኛዮሐ15+1/ ከጠቃሚነቱ የተነሣ ከመጀመሪያዎቹ የመንፈስ ፍሬዎች መካከል ሆኖ ተገልጿል:: /ገላ 5+22/

ከዚህ በተጨማሪም በውይይቶች መካከል ሰላም ይፈለጋል ሐዋርያው «የጽድቅም ፍሬ ሰላምን ለሚያደርጉት ሰዎች በሰላም ይዘራል» /ያዕ 3+18/ እንዳለው:: በአብዛኛው ሰላም የንግግር መጀመሪያና መጨረሻም ነው:: ነብዩ

ኤልሳዕ ከሶሪያዊው ከንዕማን ጋር ያደረገውን ንግግር«በሰላም ሂድ» /2ነገሥ 5+19/ በሚል ቃል እንዳጠቃለለ እናነባለንናጌታችን ኢየሱስ ክርስቶሰም ከኃጢአተኛዋ ሴት ጋር ያደረገውን ንግግሩን «በሰላም ሂጂ»/ሉቃ7+50/ በሚል ቃል አጠቃሏል፡፡

- **ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም መሆን**

ሰው ሲፈጠር ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ነበር፡፡ ነገር ግን በኃጢአት ሲወድቅ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ያንን ሰላም አጣ፡፡ ስለዚህ ይህ ሰላም ማጣት በአዳም ዘንድና በቃየን ዘንድ ተከስቷል፡፡ /ዘፍ 3÷4/ ዳግመኛም በልጅ ልጆቻቸውና በትውልዱ ሁሉ ውስጥ በነበሩት ክፉ ሰዎች ዘንድም እንዲሁ ተከስቷል፡፡ ኃጢአት ከእግዚአብሔር መለየት እና ከእግዚአብሔር ጋር መጣላት ነውና፡፡/ያዕ4+4 1ኛዮሐ.2÷5/ በመጽሐፍ እንደተጻፈ «ለክፉዎች ሰላም የላቸውም» /ኢሳ 48+22. 57+21/

ክፉዎች በዚህ ምድር በሚኖሩበት ጊዜና በዚህ ዓለም መጨረሻ በጌታ ዳግመኛ መምጣት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ሰላም ያጣሉ፡፡ ስለዚህም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲናገር « በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው፡፡» /ዕብ 10+31/ ብሏል፡፡ ታዲያ ከእግዚ አብሔር ጋር መታረቅ እንዴት ይቻላል? /2ቆሮ 5+20/ እምነት የሌላችው እምነት በመቀበል ኃጢአተኞችም በንሥሓ ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቃሉ፡፡

ስለ እምነት መጽሐፍ ቅዱስ «እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ ...» /ሮሜ 5+1/ ይላል፡፡



ይህ ሰላም በቀራንዮ አደባባይ የተሰቀለው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለእኛ ያፈሰሰው ቅዱስ ደሙ ፍሬ ነው፣ «እርሱ ሰላማችን ነውና...የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰው....» /ኤፌ3+14/ እርሱ በሰማይና በምድር መካከል ሰላምን አደረገ፡፡

ንሥሓን በተመለከተ ስሙ የተመሰገነ ይሁንና እግዚ አብሔር «ወደ እኔ ተመለሱ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ» /ሚል3+7/ ብሏል፡፡ ተወዳጁ ቅዱስ ዮሐንስም «ልባችንስ ባይፈርድብን በእግዚአብሔር ዘንድ ድፍረት አለን ትእዛዙንም የምንጠብቅና በፊቱም ደስ የሚያሰኘውን የምናደርግ ስለሆንን የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እናገኛለን፡፡» /1ዮሐ 3+21/ ቅዱስ አውግስጢኖስ ደግሞ ኑዛዜዎች በተሰኘው መጽሐፉ «ልቦችን በእርሱ ውስጥ ግረፊያቸውን እስኪያገኙ ድረስ ሲቀሰቀሱ ይቆያሉ፡፡» ብሏል፡፡

- **ከእግዚአብሔር የሚገኝ ሰላም**

የዳዊት መዝሙር «እግዚአብሔር ሕዝቡን በሰላም ይባርካል»/መዝ 28+11/ እንዳለው እውነተኛ ሰላም የሚገኘው ከእግዚአብሔር ነው፡፡ ስለዚህ ሰላም ሐዋርያው «አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል፡፡» /ፊሊ 4+7/ ብሏል፡፡

እግዚአብሔር የሰላም ምንጭ፣ የሰላም ልዑልና የሰላም ንጉሥ ነው፡፡ ለእርሱ «አ የሰላም ንጉሥ ሰላምህን ስጠን፣ ሰላምህን ፍቀድልን» የሚለውን መዝሙር እንዘምራለን፡፡ በአምልኮ ሥርዓት ውስጥ የመጀመሪያው የንስሐ ጸሎት እግዚአብሔርን በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሚሰበሰቡት

ክርስቲያኖች ሰላም የምንጠይቅበት «የሰላም ጸሎት» ነው።

የእግዚአብሔር ሰላም ከዲያቢሎስ እንዲሁም ከፍርሃትና ከጭንቀት ይጠብቀናል። ስለዚህ እግዚአብሔር ለእኛ የገባውን ቃል ኪዳን ማስታወስ አለብን። የጌታን ቃል የምታስታውስ ከሆንህ በልብህ ውስጥ ሰላምን ታገኛለህ «እነሆ በእጄ መዳፍ ቀርጫለሁ።» /ኢሳ 49+16/ «የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳን ተቆጥሯል።» /ማቴ10+30/ «ከራሳችሁ አንዲት ጠጉር እንኳ አትጠፋም።» /ሉቃ 21+18/ «ከእናንተ ከአንዱ የራስ ጠጉር እንኳን አትጠፋምና» /ሐዋ 27+34/

ስለ እግዚአብሔር ጥበቃ የተናገሩትን የዳዊት መዝሙራት በምታስታውስበት ጊዜም ያ የደስታ ስሜት ይሰማሃል።ለምሳሌ/መዝሙር120/ «እግዚአብሔር ይጠብቅሃል እግዚአብሔር በቀኝ እጅህ በኩል ይጋርድሃል። ፀሐይ በቀን አያቃጥልህም ጨረቃም በሌሊት። እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል ነፍስህንም ይጠብቃታል ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለም እግዚአብሔር ይጠብቃል።»/መዝ91/ «በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል...ከሌሊት ግርማ በቀን ከሚበር ፍላጻ...በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም አሥር ሺህ ይወድቃሉ ወደ አንተ ግን አይቀርብም።»የሚሉትን አስታወሰ።

ብዙዎቹ በእርግጥም በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ የሚገኙ የእግዚአብሔር የሰላም ቃልኪዳኖች ናቸው። ስለዚህ መዝሙረ ዳዊትን በልብህ ተማራቸው የዳዊት መዝሙራትም አንተን ይጠብቁሃል።



## ሐሰተኛ /የውሸት/ ሰላም

ይህ ሰላም ልክ ሐሰተኛ ነቢያት ሰዎችን ከመማረካቸው በፊት ሰዎችን ለማታለል ለዚህ ጥፋታቸውም ንሥሐ የማይገቡ የእግዚአብሔርን ቁጣም የማይፈሩ የሆኑት እንደሚጠቀሙበት ዓይነት ነው።ስለዚህ በነቢዩ በሕዝቅኤል መጽሐፍ እግዚአብሔር አምላክ «ሰላም ሳይኖር ሰላም እያሉ ሕዝቤን አታልለዋልና...»/ሕዝ 1+10/ «ሰላም ሳይሆን ሰላም ሰላም ይላሉ።» /ኤር6+14/ ብሏል። ይህ የኀሊናን መስመር የሳተ የሚያስጨንቅ የማታለል ዓይነት ነው።

ሰይጣን የመጀመሪያዎቹን አባት እና እናታችንን ባታለላቸው ጊዜ «ሞትን አትሞቱም ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ» /ዘፍ 3+4-5/ በማለት እንዲሁ አድርጓል።

በተመሳሳይ መልኩ የተወሰነ ኃጢአት ሌብነትንና ጉበኝነትም ይሁን ዝሙት ወይም ማጭበርበር እንዲሠራ የሚፈልግ ማንኛውንም ሰው ምንም ጉዳት እንደማይከሰትበት እና ሁሉም ነገር በሰላም እንደሚጠናቀቅ ይነግረዋል።

እንደዚህ ዓይነት ሐሰተኛ ሰላም ከመጠን በላይ ከራስ ከመተማመን እና ከትዕቢት ሊመነጭ የሚችል ነው። ይህን መሰል ሰው ይሠራቸው ዘንድ የሚፈልጋቸውን ስህተት የሆኑ ሥራዎች በሰላም ሊሠራቸው እንደሚችል ያስባል ለምሳሌ አንድ ነፍሰ ገዳይ ምንም አይነት መሰናክል ከፊቱ ሳይገጥመው ወንጀሉን በጥንቃቄ እንደሚፈጽም እና ሁሉም

ነገር በሰላም እንደሚጠናቀቅ ያምናል።

ይህ ሁሉ በአንድ ሰው የራሱ የማሰብ ችሎታ በዲያቢሎስ፣ በመጥፎ ጓደኛ ወይም ገፋፊ ምክንያት በዚያ ሰው ላይ ሊገለጽ የሚችል ሐሰተኛ ደስታ ነው።

## ከሰዎች ጋር ሰላም

ሰዎች በእጃቸው በመጨባበጥ ብቻ ሳይሆን በልብ እና በድርጊትም ጭምር እርስበርሳቸው ሰላምታ ይሰጣጣሉ። ለሌሎች እውነተኛ ሰላምን በመመኘት ከልባቸው ሰላም ለእናንተ ይሁን ይባባላሉ።

በሁለት ሰዎች መካከል ማንኛውም ዓይነት ግጭት አለመስማማት ከተፈጠረ መታረቅ አለባቸው።ጌታ በተራራው ስብከቱ «እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ»/ማቴ5÷23.24/ ያለው ለዚህ ነው።

ዳግመኛም ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ቁርባን ከመቀበላችን በፊት እንድንታረቅ የምትፈልገው ለዚያ ነው። በቅዱስ ቁርባንም ውስጥ «ከቅዱሳኑ ቅዳሴ» በፊት ስለ እርቅ እን ጸልያለን። እርሱም ከሥርዓተ ቅዳሴ /ከቅዳሴ ሥርዓት እና ከካህን ሹመት በፊት ነው።

ነገር ግን ለብዙ ጠላቶች ወይም ባላንጣዎች እርቅን መፈጸም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል በማለት ሐዋርያው «ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ።» /ሮሜ 12÷18/ ብሎአል።

እርግጠኛ ለመሆን አንዳንድ ጊዜ አንድ ሰው ከሌሎች



ሰዎች ጋር በኃጢአታቸው ውስጥ አብሯአቸው ኃጢአታቸውን እስካልሠራ ድረስ ወይም ከሌሎች ሰዎች ጤነኛ ያልሆኑ ባሕሪ የተነሳ በሰላም መኖር ካልቻለም ሌሎች አንዳንድ ቀናተኞች፣አንተን በመቃወም ክፋትን ተንኮልን የሚያሴሩብህ፣ምናልባት ያንተን መልካም ጠባይ የእነርሱን ስሕተት ይገልጽብናል ብለው ወይም በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች ስሕተትን የሚፈጽሙ ይሆናሉ። ነገር ግን ከእያንዳንዱ ሰው ጋር በሰላም መኖር የማይቻል ከሆነ ምን ይጎዳል ?

- የጭቅጭቅ ምክንያት አትሁን

የምትሰቅል ሳይሆን የምትሰቀል ሁን። ከሌሎች ጋር ልትጋፈጥ ትችላለህ ነገር ግን የክፋት ጀማሪ አትሁን። ከዚህ በተጨማሪ የሌሎችን ስሕተት በተመለከተ ከልክ ያለፈ ስሜታዊ አትሁን።

- ትሑትና ትዕግሥተኛ ሁን

በምድረ ገጽ ላይ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት የነበረውን ነቢዩን ሙሴን ምሰል። /ዘኁ 12÷3/

- ሁልጊዜ መሐሪ እና ይቅር ባይ ለመሆን ሞክር

ሐዋርያው «ለማንም ስለ ክፉ ፋንታ ክፉን አትመልሱ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ ...ተወዳጆች ሆይ ራሳችሁ አትበቀሉ ለቁጣ ፋንታ ስጡ እንጂ....» /ሮሜ 12÷17-19/ ብሏልና። እንዲሁም ቁጣን ጊዜያዊ ስሜትን እና ንዴትን እንድናስወግድ «ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ»/ሮሜ 12+21/ በማለት ያጠይቀናል።

በእርግጥ መታገስ የሚችል ሰው ዕድለኛ ሲሆን ይህንን

የማይችል ግን ደካማ ነው:: ለዚህ ነው ሐዋርያውም «እኛም ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ራሳችንንም ደስ እንድናሰኝ ይገባናል::» /ሮሜ 15+1/ ያለው::

ሌሎች አንተ እንዳሰብካቸው ፍጹም የሚስማሙ እንዲሆኑ አትፈልግ:: ነገር ግን መሆን እንዳለባቸው ሳይሆን እንደሆኑት አድርገህ ተቀበላቸው ሁላችንም ተፈጥሮን እንደራሷ አድርገን ተቀብለናል:: ወቅቶችን ዝናባማ ፣ማዕበላማም ይሁን ሞቃታማ ተፈጥሮ ራሱን እንዲለውጥ ሳንጠይቅ ተቀብለነዋል:: ከሰዎችም ጋርም ልክ እንዲሁ እናድርግ::

ሰዎች ሁሉ ጻድቅ እና መልካም አይደሉም:: ብዙዎቹ ድክመቶች ወይም የተወሰኑ ባሕሪያቸውን ተቆጣጣሪ የሆኑ አመሎች አሉባቸው:: ሰዎች የተለያዩ ዓይነቶች ናቸው:: ከእነዚህም አንዳንዶች ሁከተኞች ናቸው:: ስለዚህ በጠባያቸው ተጽዕኖ እንደማይደረግበት ተመልካች እንሁን፤ባሕሪያቸውንም በጥበብ እንቀበላቸው::

አንድ ሰው በየዋህነት እና በትሕትና ከሌሎች ጋር በመልካም ሁኔታዎች ውስጥ ሊሆን ይችላል አንድ ሰው ብዙዎችን በጥሩ መንፈስ ማሸነፍ ከቻለ ከእነርሱም ጋር ሰላም ከሆነ ይልቁንም በየዋህነት እና በትሕትና ምን ያህል ሰላም ይሆን! ለእውነት የምትከራከር ከሆንህ በጸጥታ በእርጋታ እና በትህትና አድርግ:: እውነትን ልትወድ እና ለእርሱም ልትቆም መብት አለህ ነገር ግን እውነትን እንዲከተሉ ሌሎችን ማስገደድ አትችልም:: እግዚአብሔር ራሱ ትእዛዛቱን ሰጥቶናል ነገር ግን ለእነርሱ እንድንታዘዝ አላስገደደንም::



ብቸኛው ነገር ከመናፍቃን እና እምነት ከሌላቸው ከከሃዲያን ጋር የምትከራከርበት ጊዜ ነው:: በእምነት ጉዳይ ለመናፍቃን ትሁት ደግና ሩሕሩህ መሆን አንችልም:: ተወዳጁ ቅዱስ ዮሐንስ ይህንን በተመለከተ ያለውን ተመልከት «ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉትም ሰላምም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና::» /2ዮሐ10÷11/::

ከእምነት ሊያስወጣህ የሚፈልገውን ማንኛውንም ሰው በመቃወም ራስህን ጠብቅ:: ለእንደዚህ ዓይነት ሰው ትሁት ደግና ርህሩህ አትሁን እርሱንም በቤትህ አትቀበል::

አንተን ወደ ሥነ-ምግባር ውድቀት እና ወደ ኃጢአት ሊመራህ ለሚፈልግ ለማንም ተመሳሳይ ነገር ተግባራዊ ያደረገል እንደዚህ ዓይነት ሰዎችን ከዙሪያህ አስወግድ::

የመጽሐፍ ቅዱሱን ቃል አስታውስ «አትሳቱ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል::»/1ቆሮ 15÷33/ «ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ በኃጢአተኞች መንገድ ያልቆመ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ::» /መዝ 1+1/ እንዳለ::

**•ውስጣዊ ሰላም ጸጥታን ያመጣል ፍርሃትንም ያስወግዳል**

**ፍርሃት:**

ውስጣዊ ሰላም ማጣት ፍርሃትን፣መረበሽን፣ ለተቃውሞ መነሳሳትን እና ሌሎች ብዙ የተፈጥሮ ችግሮችን ያስከትላል::

የልብ ሰላም ያለውን ነቢዩ ዳዊትን ተመልከት እርሱ ምን አለ «ሠራዊት ቢሰፍርብኝ ልቤ አይፈራም ሰልፍም ቢ

ነሳብኝ በዚህ እተማመናለሁ::» /መዝ 26+3/ «በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም::» /መዝ 22/ «በእርግጥም ከዳዊት በስተቀር መላ ሠራዊቱ ጎልያድን መግጠም ይፈራ ነበር::

ዳዊት ምንም ብላቴና ቢሆንም እንኳን የአንበሳ ልብ ነበረው:: ታላላቅ ወንድሞቹ ግን በፍርሃት ውስጥ ነበሩ:: ንጉሥ ሳዖልም እንኳን «አንተ ገና ብላቴና ነህና እርሱም ከብላቴንነቱ ጀምሮ ጦረኛ ነውና ይህን ፍልስጥኤማዊ ለመውጋት ትሄድ ዘንድ አትችልም::» /2ሳሙ 17+33/ አለው:: ነገር ግን ጠንካራ ኃይለኛና ደፋር ልብ ያለው ዳዊት ለንጉሡ «ስለ እርሱ የማንም ልብ አይውደቅ፤ እኔ ባሪያህ ሄጄ ያንን ፍልስጤማዊ እዋጋዋለሁ::» አለው:: ዳዊትም ሳኦልን «የአባቴን በጎች ስጠብቅ አንበሳና ድብ ይመጣ ነበር:: ከመንጋውም ጠቦት ሲወስድ በኋላውም እከተለውና እየመታው እንደ ነበር፤ ከአፉም አስጥለው እንደ ነበር በተነሳበትም ጊዜ ጉሮሮውን ይዤ እመታውና እገድለው ነበር::» ብሎ ነገረው:: /1ሳሙ 17+32-36/

ዳዊት በእግዚአብሔር ሥራ ስለተመካ ደፋሩ ጎልያድን አልፈራውም ነበር:: ዳዊት «ሰይፉ የእግዚአብሔር ነው» አለ:: ታዲያ ይህ ሰይፍ የሰይፍና የጦር አይደለም ዳዊትም ለጎልያድ «አንተ ሰይፍና ጦር ጭሬም ይዘህ ትመጣብኛለህ እኔ ግን ዛሬ በተገዳደርኸው በእስራኤል ጭፍሮች አምላክ ስም፤ በሠራዊትጌታ በእግዚአብሔርስም እመጣብሃለሁ... እግዚአብሔር ዛሬ አንተን በእጄ አሳልፎ ይሰጣል:: /1ሳም 17÷45.../ አለው:: እንዴት ያለ ጥንካሬ፤ በእግዚአብሔር ሥራዎች እና በጥበቃው መታመን ነው:: ዳዊት ፈጽሞ አልፈራም በእምነቱም የእግዚአብሔርን ስም በጦር ሜዳው



ስፍራ አወጀ:: ዳዊት እግዚአብሔር ከጎልያድ እና በምድር ላይ ካሉ ሌሎች ደፋር ጦረኞች ይልቅ እጅግ ኃያል እንደሆነ እርግጠኛ ነበር:: ስለዚህ «ስለ እርሱ የማንም ልብ አይውደቅ ሲል አረጋገጠላቸው::» /1ሳሙ 17÷32/

ሰላም በአንድ ሰው ልብ ውስጥ በነገሠ ጊዜ ያሰው በራሱ የሚተማመን እና ሰላማዊ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ልቦችም ውስጥ ሰላማዊነትን የሚያሰራጭ ጭምር ይሆናል::

ሌሎች ተመሳሳይ ምሳሌዎች ሙሴና ኤልሳዕ ናቸው:: እያንዳንዳቸው በራሳቸው የሚተማመኑ በመሆናቸው በሌሎች ልብ ውስጥ ሰላም ይፈጥራሉ::

የሰማሪያ ከተማን ሠራዊት በከበባት ጊዜ ሎሌው ግያዝ ሲፈራ ኤልሳዕ ግን ሰላማዊ ነበር:: ግያዝ ከተማይቱን የከጠበባትን የእግዚአብሔር እርዳታ አልተመለከተም ስለዚህ ኤልሳ «ከእኛ ጋር ያሉት ከእነርሱ ጋር ካሉት ይበልጣሉና አትፍራ::» አለው /2ነገ 6÷6/ ኤልሳዕም ሎሌው ያይ ዘንድ ዓይኖቹን እንዲከፈትለት ወደ እግዚአብሔር ጸለየ::

እስራኤላውያን ባሕረ ኤርትራን ሲጀገሩ የፈርዖን ሠራዊት ወደ እነርሱ እንደተጠጉ ሲመለከቱ እጅግ አዝነውና ፈርተው ነበር:: የእግዚአብሔርን ማዳን ሲመለከቱ የሚችሉበት እምነት አልነበራቸውምና:: ስለዚህ ሙሴ ለሕዝቡ «አትፍሩ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያንን ለዘለዓለም አታዩአቸውምና ቁሙ:: ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋትን የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ::እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል እናንተም ዝም ትላላችሁ አላቸው::»/ዘጸ14÷13-14/

•በእምነት የእግዚአብሔርን እርዳታ እና ድኅነት ማየት

ስለምንችል እንፈራ ።

ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ጌታ ሊደርስ በውሃው ላይ ሄደ ነገር ግን የንፋሱን ኃይል አይቶ ፈራ ሊሰጥምም ጀመረ:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሳይሆን ማዕበሉን ተመልክቶ ነበርና ወዲያውም ኢየሱስ እጁን ዘርግቶ ያዘውና «አንተ እምነት የጎደለህ ስለምን ተጠራጠርህ?» በማለት ገሠጸው:: /ማቴ 14÷30-31/

- እግዚአብሔር ሁልጊዜ እንዳንፈራ ይፈልጋል

እርሱ ለቅዱሳን ሐዋርያት «ሰላምን እተውላችኋለሁ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ....:: ልባችሁ አይታወክ አይፍራ ም::»/ዮሐ 14÷27/ አለ:: እግዚአብሔር ሁልጊዜ ልጆቹን ማበረታታት ይኗል ፍርሃትን አስወግደው እንዲጥሉም ይጠራ ቸዋል::

ኢያሱ ከሙሴ ሞት በኋላ ድካም በተሰማው ጊዜ እግዚአብሔር «ከሙሴ ጋር እንደሆንሁ እንዲሁ ከአናንተ ጋር እሆናለሁ አልጥልህም አልተውህም.... በምትሄድበት ሁሉ አምላክህን እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና አይዞህ አትፍራ አትደንግጥ::» ብሎታል:: /ኢያሱ 1÷5-9/

ጌታ ለሐዋርያው ለጳውሎስ እንዴት ውብ የሆነ የማጽናኛ ቃል እንደተናገረው ተመልከት«እኔ ከአንተ ጋር ነኝ ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሳብህ የለምና አትፍራ:: ነገር ግን ተናገር ዝምም አትበል::»/ ሐዋ18+9-10/

ያዕቆብ ወንድሙን ኤሳውን በፈራበት ጊዜ በሕልም ተገለጸለት «እነሆ እኔ ከአንተ ጋር ነኝ በምትሄድባትም መንገድ ሁሉ እጠብቅሀለሁ ወደዚህችም ምድር



እመልስሀለሁ::» /ዘፍ 28+15/ በማለት አጽናንቶታል::

- ፍርሃት ከሰብዓዊ ተፈጥሮ ጋር የሚጻረር ነው:: ወደ ሰው ነፍስ የሚገባውም ከኃጢአት በኋላ ብቻ ነው::

አዳም ከአራዊት ከአናብርትና ከአናብስት እንዲሁም ከእባቦችና በሰውነታቸው ከሚሳቡ ነፍሳት ጋር ይኖር የነበረ ሲሆን ፈጽሞ አይፈራም ነበር:: አባታችን ኖኅም ከነዚህ ሁሉ አራዊት ጋር እነርሱን በመመገብ እና ለእነርሱ ጥበቃ በማድረግ በመርከብ ውስጥ ነበር:: በዚህም ፈጽሞ ፍርሃት አልነበረበትም:: ነገር ግን አዳም በኃጢአት በወደቀ ጊዜ መፍራት ጀመረ፤ በዛፎች ውስጥም ተሸሸገ፤ ለእግዚአብሐ ‚ርም «በገነት ድምፅህን ሰማሁ ዕራቁቴንም ስለሆንሁ ፈራሁ ተሸሸግሁም::» /ዘፍ 3÷10/ አለው::

ቃየንም እንደ አዳም በፈራ ጊዜ እግዚአብሔርን አለው «ኃጢአቴ ልሸከማት የማልችላት ታላቅ ናት:: እነሆ ዛሬ ከም ድር ፊት አሳደድኸኝ ከፊትህም እሰወራለሁ በምድር ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ እሆናለሁ የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል::» /ዘፍ 4÷13-14/ ቃየንም ቀሪዎቹን ቀናቱን በድንጋጤ እና የልብ ሰላም በማጣት አሳለፈ::

- ኃጢአት ሰው ከእግዚአብሔር ኃይል እና ጥበቃው እንደተለየ እንዲሰማው ታደርጋለች ስለዚህም ይፈራል

ኃጢአተኛ ሰው ኃጢአት የሚያስከትለውን ውጤት በማኅበረሰቡ ወይም በሕግ የሚደርስበትን ቅጣት እንዲሁም እግዚአብሔርን እና ፍርዱን ይፈራል:: ጻግመኛም በኃጢአት ፊት ያለውን የራሱን ድክመት እና በእርሱ ላይ የሰለጠ ነበትን ዲያብሎስን ይፈራል::

አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ይቅርታ እና ጥበቃ በሚያገኝበት፣ በድካሙቱ እና በእግዚአብሔር እርዳታ ላይ እምነት በሚኖረው ጊዜ ፍርሃት ይወገዳል። አንድ ሰው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደሆነ ከተሰማው አይፈራም በእርግጥም ይህ ስሜት ፍርሃትን ከልቡ አውጥቶ ይጥልለታል።

ፈሪ ሰው ትኩረት የሚያደርገው ፍርሃትን በሚያስከትሉ ምክንያቶች ላይ እንጂ ከእነዚህ ሊታደገው በሚችለው በእግዚአብሔር ላይ አይደለም።

## የፍርሃት ምክንያቶች

የፍርሃት ምክንያቶች ብዙዎቹ ናቸው። እነርሱም በሙሉ የሚወጡት ከአንድ ሰው ከራሱ ልብ ውስጥ ነው። አንዳንድ ሰዎች የሌሎች ሰዎች ሐሜተኝነት ኀጺነትን እና ሴራቸውን ይፈራሉ። አንዳንዶችም ምቀኝነታቸውን ይፈራሉ። በቀናተኛ ዓይን እና በሚያስከትለው ጉዳት የሚያምን ሰው ይፈራል። የፍርሃቱ ምክንያት የቀናተኛው ዓይን ኃይል ሳይሆን በዚያ ያመነው የልቡ ድካሙት ነው።

- የእግዚአብሔርን እርዳታም ከፊታቸው ያላስቀመጡ ሰዎች አታላይና አጭበርባሪ ሰዎችን ይፈራሉ።

እግዚአብሔር ሕዝቡን ለፈራው ለኤርምያስ «እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና ከፊታቸው አትፍራ.... እነሆ በምድሪቱ ላይ እንደተመሸገ ከተማ እንደብረትም ዓምድ እንደናስም ቅጥር ዛሬ አድርጌሃለሁ....ከአንተ ጋር ይዋጋሉ ነገሬ ግን አድንህ ዘንድ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና ድል አይነሱህም።» /ኤር 1÷8፣18÷19/ ያለው ለዚህ ነው።



አንድ ሰው አንዳንድ ሰዎች ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ ምንም ዓይነት ጉዳት በእርሱ ላይ ለማድረግ ባያስቡም እንኳን ሰዎችን መፍራት ሊሰማው ይችላል።

ለምሳሌ ምንም እንኳን ዳዊት በሳኦል ላይ ፈጽሞ ጉዳት ለማድረስ ባያስብም እርሱ ግን ዳዊትን ይፈራው እና እርሱን ለመግደል በማንኛውም ቦታ የሚያሳድደው ይመስለው ነበር። ሳኦል በዳዊት እጅ በነበረበት፣ ዳዊት እርሱን ለመግደል እድሉ በእጁ ሳለ እና ተከታዮቹም ይህንን እንዲያደርግ በመከሩት ጊዜ እንኳን «እግዚአብሔር የቀባው ነውና እግዚአብሔር በቀባው በጌታዬ ላይ እንዲህ ያለውን ነገር አደርግ ዘንድ እጄንም እጥልበት ዘንድ እግዚአብሔር ከእኔ ያርቀው።» /1ሳሙ 24÷6-7/ ብሎአቸዋል።

ዳዊትም ለንጉሡ ምን እንዳለው ተመልከት «የእስራኤል ንጉሥ ለማሳደድ መጥቶአል አንተስ ማንን ታሳድዳለህ? የሞተ ውሻን ወይስ ቁንጫን ታሳድዳለህን? » እነዚህ ቃላት ሳኦል ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲያለቅስ አድርጎታል ለዳዊትም «አንተ ከእኔ ይልቅ ጻድቅ ነህ።» አለው።/ሳሙ 24÷14.15/

- አንዳንድ ሰው ልክ እንደ ሕፃናት ሕልውና የሌለውን ነገር ይፈራል።

የሕፃን አእምሮ አስፈሪ የሆን እንግዳ አሳቦችን ይፈጥራል። በውስጣቸው የተደበቁ ነገሮችን እንዳሉ አድርጎ በማሰብ እንደ ጨለማ ያሉ ነገሮችን ይፈራል። በተጨባጭ የሌለ ዘራፊንና እርግጠኝነት የሌላቸውን መናፍስትንም ይፈራል። እነዚህ ነገሮች በፈሪ ልብ የተፈጠሩ ቅዠቶች ናቸው። አንዳንድ ጊዜ ሕፃን ካልታወቀ አደጋ የሚጠብቀው ማንም

ሰው በሌለበት ብቻውን መሆን ይፈራል፤ ስለዚህ ከፍርሃት ውጪ ያለ ምንም ምክንያት ያለቅሳል።

እንደነዚህ ዓይነት ፍርሃቶች ከአንዳንዶቹ ጋር ካደጉ በኋላም ሊቀጥሉ ይችላሉ። ስለዚህ ፈተናዎችን የሚፈሩ እና ፈተናዎች አስቸጋሪ እንደሆኑ አድርገው የሚያስቡ ወይም ቢ ያንስ ቢያንስ እርማቱ ከባድ እንደሚሆን የሚያስቡ አንዳንድ ተማሪዎችን እናገኛለን፤ ሌሎች ለሥራ የሚያደርጉትን ቃለመጠይቅ እንወድቃለን ብለው በማሰብ ይፈራሉ።

በተመሳሳይ መንገድ አንዲት ልጃገረድ አንድ ሰው ለጋብቻ ሲጠይቃት ፍርሃት ሊሰማት ይችላል። ምናልባት ላይወደኝና ሊተወኝ ይችላል ብላ ትፈራለች። በዚህም ምክንያት ሰዎችን ላትቋቋም ወይም ይኼኛውም ደግሞ ሊተወኝ ይችላል ብላ በማሰብ ሌላ ሙሽራ ላትፈልግ ትችላለች። ፍርሃትም በውስጧ የበለጠ እያደገ ይሄዳል።

• ሌሎች ውድቀትን ይፈራሉ

ምንጊዜም ሰው ሥራ ለመሥራት ሲያስብ ሥራው ይወድቃል ወይም እንቅፋቶች ይገጥሙታል ወይም ደግሞ ተፎካካሪዎች ይገጥሙኛል ብሎ ይፈራል። ደሀ ከሆነም ተረጂነትን እና ችግርን፤ ባለጸጋ ከሆነም ዝርፊያን በአጠቃላይ በነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ፍርሃት ያድርበታል።

• አንዳንድ ሰዎች አደጋዎችን ይፈራሉ

እንደዚህ አይነት ሰው በአውሮፕላን ከተጓዘ አደጋ ሊ ከሰት ይችላል በማለት ወይም በጋዜጣ የወጡ እንደዚህ ያሉ ነገሮችን በማስታወስ ይፈራል።

በማንኛውም የትራንስፖርት ወይም የመጓጓዣ ዘዴዎች



ውስጥ ሊከሰቱ ለሚችሉ አደጋዎች የፍርሃት ሰለባ ይሆናል። በዚህ ሁኔታ ጥቁር ትዝታዎች ወደ አእምሮው ይመጡበታል ይህም ሁልጊዜ እንዲፈራ ያደርገዋል።

• የራሳቸውን ድክመት የሚፈሩ የሰዎች አሉ።

እንደዚህ ዓይነት ሰው የራሱን የችሎታ ማነስ ዝንጉነት በተቀናቃኞቹ እና በጠላቶቹ ኃይል ፊት የሚያሳየውን ድክመቱን እና እነርሱን ለመቋቋም አለመቻሉን ይፈራል። ይህ በራስ የመተማመን መንፈሱን የጀግንነት መንፈሱን እና ውሳኔ ለመውሰድ ያለውን ኃይሉን ያሳጣዋል። ያለመቻል እና የውድቀት አሳብ ሁልጊዜ ከዓይኖቹ ፊት ነው። ኃጢአትንም እንኳን ይፈራል እርሱንም በመቋቋም ችሎታ እንደሌለው እንደማይችል ይሰማዋል።

እንደዚህ ዓይነት ፍርሃት በአንድ ሰው ላይ ግራ መጋባት፣መረበሽ እና ችግር ያስከትልበታል ይህ ብቻ አደለም ለመሥራት ያለውን ችሎታም ሽባ ያደርግበታል።

በመንፈሱ እና በነርቮቹ ላይ መጥፎ ውጤት ያመጣል በወደፊት ተስፋው፣በአመለካከቱ፣ በንግግሩ እና በእንቅስቃሴዎቹ ላይ ፍርሃት ይከሰታል። ይህ ሰው ይንቀጠቀጣል፤ ይፈዛል የልብ ምቱም ይጨምራል። በጠባዩ፤ በወላዋይነቱ፣ ውሳኔ ለመወሰን ባለመቻሉ እና በጥበቃ ፈላጊነቱ ውስጥ ሰው ሁሉ ፍርሃቱን ይመለከትበታል።

• ፍርሃት አንዳንዶቹን ወደ ኀዘን ይመራቸዋል።

«የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል።»/ዘፍ 4÷4/ የሚል ቃልን በፊታቸው ያስቀምጣሉ። በሌላ በኩል ስላም

መንፈሳዊ ሰው ድፍረትን በመስጠት በልቡ ላይ ይነግሳል እንጂ አይፈራም።

አንዳንዶቹ የሞት ፍርሃት ወይም ወደ ሞት የሚመራ ሕመም ይሰማቸዋል። ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት ሰው በሕመም በበሽታ፣ ሲጠቃ ተስፋ ይቆርጣል በዚህም በሽታ የሚደርስበትን ከፍተኛ አደጋ ያስባል። አንዳንዶቹ ሐኪሞች በዚህ ፍርሃት ይወድቃሉ አንዳንድ ሰዎችም ደግሞ ተላላፊ በሽታን እና ያልተለመዱ የመከላከያ ዘዴዎችን መውሰድ ይፈራሉ።

## የማይፈሩ ሰዎች

በልቡ ሰላም የነገሠበት መንፈሳዊ ሰው ሞትን ፈጽሞ አይፈራም። የተቀደሰ ሕይወት መምራት የሞት ፍርሃትን ከአንድ ሰው ልብ ያስወግዳል። ይልቁንም በእንደዚህ ዓይነት ቅድስና የተዘጋጀ ሰው ሞትን ይመኛል፤ምክንያቱም ይህ ወደ ክርስቶስ፣ እንዲሁም ወደ መላእክት እና ወደ ጻድቃን ኅብረት ይወስደዋልና ።

የሰማዕታት እና የቅዱሳን የበረሀ አባቶች ታሪክ ለዚህ ድርጊት መልካም ምስክር ነው። ሰማዕታት ሞትን፣ ሥቃይን ዛቻን እንዲሁም ገዢዎችን፣ ለፍርድ መቅረብን እና እስር ቤቶችን አይፈሩም። ይልቁንም በእስር ቤት ይዘምራሉ ከጌታ ጋር በመገናኘታቸውም ደስ ይላቸዋል። የእነርሱ የሕይወት ታሪክ በልቦቻችን ሰላም እንዲነግሥ እንጂ እንዳንፈራ በሚያደርግ በእነዚህ አይነት ኃይል የበለጠ እንድንሠራ ለማበረታታት የቀረቡ ናቸው።

በተመሳሳይ ሁኔታ በረሃውን የማይፈሩ ስለነበሩትና በብቸኝነት መንፈሳዊ ደስታ ስላገኙት በበረሃ ጉያ ውስጥ



ይኖሩ ስለነበሩት አባቶች ታሪክ እንብበናል።የዲያቢሉስን ውጊያዎች እና በረሃውን ከአራዊቱ ጋር ሳይፈሩ እንዴት ይኖሩ እንደነበር እና ከእነርሱ ውስጥ አንዳንዶቹ እንዴት በመቃብር ውስጥ ፍርሃትም በውስጣቸው እንዳልነበር ባወቅን ጊዜ ከሕይወት ታሪኮቻቸው ጥንካሬን እናገኛለን አባ መቃርዮስ በምሽት በመቃብር ውስጥ የራስ ቅል ተንተርሶ ይተኛ እንደነበር አንብበናል።አንድ ጊዜ ዲያቢሉስ ከራስ ቅሉ ሥፍራ በማፌዝ ተናገረው። ምክንያቱም በዚህ አባ መቃርዮስም ፀጥታ ሊያጣ ይችል እንደሆነ እንጂ ፈጽሞ አልፈራም።

አንተም ታዲያ ጠንካራ እና የማትፈራ ሁን። ሰላም በልብህ ይንገሥ። የሰላምና የልብ ሙሉነት ባለቤት ለመሆን የእግዚአብሔርን የጥበቃ ኃይል ማስታወስ በራሱ ይበቃል ።

የእግዚአብሔርን ሕልውና እና ለአንተም እንደሚሠራ እምነት ይኑርህ። እያንዳንዱ ችግር መፍትሔ እንዳለው፣እግዚአብሔርም ብዙ መፍትሔዎች እንዳሉት እመን። በሰዎች ዘንድ የማይቻለው በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላልና።ከዚህ በተጨማሪም «ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል።» /ማር 9፥23/

የውስጣዊ ሰላም ባለቤት ለመሆን የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ዙሪያ እንደሚሰፍርና እንደሚያድናቸው ቅዱሳት መጻሕፍትም በብዙ ምሳሌዎች እንደሚመሰክሩልን ብዙ መላእክት እኛን ለመጠበቅ በዙሪያችን እንደሰፈሩ እናስታውስ። ዳግመኛም እኛ ብቻችንን እንዳልሆንን ለማወቅ

የቅዱሳንን ሥራዎች፣ ጸሎታቸውንና እና ለእኛ ያላቸውን አማላጅነት እናስታውስ:: በውስጣችን የእግዚአብሔር ሥራና እና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እንዳለም እናስታውስ::

- **ይሁንና በውሸት ከመታመን ራሳችንን መጠበቅ አለብን::**

መሳሌዎች- በካንሰር ሕመም የተያዘ ሰውን በዙሪያው ያሉ ሰዎች አደገኛ ያልሆነ በቀላሉ ሊድን የሚችል ሕመም እንደሆነ በመንገር ሊያጽናኑት ይሞክራሉ:: ወይም አንድ አስተዳደር በረዳቱ ላይ ጥገኛ ሆኖ እርሱ ያለው ነገር ሁሉ ተሠራው ስራ ትክክል ነው በማለት የማይመረመርና በራሱ የማይተማመን አይነት ሰው ይሆናል::



# ምዕራፍ አራት
# ትዕግስት

## ሀ. የእግዚአብሔር ትዕግሥት

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው የመንፈስ ፍሬ «ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት...» /ገላ.5+22-23/ ነው:: እነዚህ ምግባራት እርስበርሳቸው ግንኙነት አላቸው፤ እርሱም ፍቅር ያለው ደስታና ሰላም ከእነዚህም ጋር ትዕግስትም አለው «ፍቅር ይታገሳል እንዲል»/1ኛ.ቆሮ 13+4/

ትዕግስት ቻይ፣ ልበ ሰፊ ትሁት እና መሀሪ የሆነ ሰው ጠባይ መለያ ነው:: ጠቢቡ ሰሎሞን ምሳሌያችን ነው «እግዚ አብሔርም ለሰሎሞን እጅግ ብዙ ጥበብና ማስተዋል በባሕ ርም ዳር እንዳለ አሸዋ የልብ ስፋት ሰጠው::»/1ኛነገ.ሥ 4 .+29/ ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሁት ሰው ነበር:: /ዘኍ 12+3/

- **እግዚአብሔር ትዕግስተኛ ነው፤**

እራሱ ታጋሽ እና ትሁት ነው:: እንደ እራሱ ትዕግስት ባይሆን እኛ ሁላችን እንጠፋለን የእግዚአብሔር ትዕግስት ከጥልቅ ምህረቱ እና ርህራሄው ይመነጫል:: ነቢዩ ዳዊት «እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ ነው ከቁጣ የራቀ ምሕ ረቱም የበዛ::»/መዝ103+8/ ሲል ገልፆታል::ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «የጌታችሁ ትዕግስት መዳናችሁ እንደ ሆነ ቁጠሩ::» /2ጴጥ 3+15/ ብሏል::

• እግዚአብሔር ለኃጢአተኞች እጅግ ታጋሽ ነው

አህዛብን እና የጣዖት አምልኮአቸውን ንሥሐ እስኪገቡ እና እርሱን ወደ ማምለክ እስኪመለሱ ድረስ እጅግ ታግሶአል፡፡ ራሳቸውን በእርሱ ፊት በጾም ትሁት እስኪ ያደርጉ ድረስ የነነዌ ሰዎችን ታግሶአል፡፡ እርሱ ግን ንሥሐቸውን ተቀበለ ምንም እንኳን ዮናስ ባይደሰት፡፡ /ዮና 3+4/

ፈርዖን ብዙ ጊዜ ቃልኪዳኑን ባይፈጽምም እግዚአብሔር ለረዠም ጊዜ ታግሶታል፡፡ የፈርኦንን ጭካኔ በማየት ለአንድ ጊዜና ለመጨረሻ ጊዜ ከመቅጣት ይልቅ ሊመለስ የሚችልባቸውን አሥር መቅሰፍቶችን በማድረስ እግዚ አብሔር እጅግ ታግሶት ነበር፡፡ በእያንዳንዱ ሰዓትም ፈርዖን «በደልሁ» /ዘጸ.27+10-16/ በማለት አለቀሰ ንሥሐ ለመግባትም ቃል ገባ ነገር ግን ዳግመኛ በደለ እግዚ አብሔርም በትዕግስት ጠበቀው፡፡

የእግዚአብሔር ትዕግሥት ኃጢአተኛን ወደ ንሥሐ ይመራል ነገር ግን ንሥሐ ካልገባ ለእግዚአብሔር ቅጣት ተገዥ ይሆናል፡፡

ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ኃጢአተኛን «ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንሥሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን? ነገር ግን እንደጥንካሬህና ንሥሐ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቁጣ ቀን ቁጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ፡፡» ሮሜ 2+4-5/ በማለት ያስ ጠነቅቃል፡፡



ብዙ ኃጢአት ብትሠራ እና ቅጣት ባያገኝህ እግዚ አብሔር አይሠራም ብለህ አታስብ፡፡ በእርግጥ ጽዋህ ገና አልሞላችም፤ አንድ ጊዜ ጌታ «የአሞራውያን ኃጢአት ገና አልተፈጸመችም፡፡»/ዘፍ15+16/ ብሏልና፡፡ የሰዶም ጽዋ በሞላች ጊዜ እግዚአብሔር በእሳት አነደዳት /ዘፍ 19/

ትዕግሥት በእግዚአብሔር ባሕርይ ውስጥ አለች እርሱም ወደ ንሥሐ አለያም ወደ ፍርድ ይመራሃል፡፡ ለእግዚአብሔር ትዕግሥት መልካም ምሳሌ የምትሆነው ለሦስት ዓመታት ፍሬ ያልሰጠችው የበለሷ ዛፍ ምሳሌ ነው፡፡ ባለቤቷ ስለምን ደግሞ መሬቱን ታጎሳቁላለች ስለዚህ ትቆረጥ ብሎ አሰበ፡፡ የወይን አትክልት ሠራተኛው ግን «ዙሪያዋን እስክኮተኩትላትና ፋንድያ እስካፈስላት ድረስ በዚ ች ዓመት ደግሞ ተዋት ወደ ፊት ብታፈራ ደህና ነው ያለዚያ ግን ትቆርጣታለህ፡፡» /ሉቃ 13+6-9/ አለው፡፡

ስለዚህ ትዕግሥት ለማስተካከል ዕድልን ይሰጣል፡፡ በበረሃ ያሉ ሰዎች ምንም እንኳን በአስቃቂ ችግር ውስጥ ያሉ ሁልጊዜ የሚያማርሩ እና የሚለዋወጡ ቢሆኑም እግዚ አብሔር ትዕግሥት ያሳያቸዋል፡፡ «ቀኑን ሁሉ ወደማይታዘዝ ወደሚቃወም ሕዝብ እጆቼን ዘረጋሁ፡፡»/ሮሜ.10+21/ ይላል፡፡ ይሁንና ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለው እርሱ ይታገሳቸዋል፡፡ «እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደሰዶም በሆንን እንደገሞራም በመሰልን ነበር፡፡»/ኢሳ 1+9/

ሌላው የእግዚአብሔር ትዕግሥት ምሳሌ የሰማርያ ሰዎችን የተቀበለበት ዘዴ ነው፡፡ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን ባቀና ጊዜ የሰማርያ መንደሮች ጌታን ለመቀበል ሲቃወሙ ደቀመዛሙርቱ ያዕቆብና ዮሐንስ ይህንን «...እሳት

ከሰማይ ወርዶ ያጥፋቸው እንል ዘንድ ትወዳለህን?» አሉት። ነገር ግን እርሱ በትዕግሥቱ ይህንን አልፈቀደም ዘወር ብሎ ገሥጻቸውና «ምን ዓይነት መንፈስ እንደሆናችሁ አታውቁም የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም»አለ።/ሉቃ9+2-56/። የሰማርያ ሰዎችም እምነትን የሚቀበሉበት ጊዜ መጣ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ድኅነትንም አገኙ/ሐዋ 8+14.17/።

አስደሳቹ ተግባርም ቤተ ክርስቲያንን በሚያሳድድ ላይ የሚገለጽ የእግዚአብሔር ትዕግሥት ነው። ከእነዚህ ውስጥ ዋናው ስለራሱ «አስቀድሞ ተሳዳቢና አሳዳጅ አንገላችም ምንም ብሆን ይህን አደረገልኝ ነገር ግን ሳላውቅ ባለማመን ስላደረግሁት ምሕረትን አገኘሁ።»/1ጢሞ1+13/ ሲል የተናገረው የተርሴሱ ሳውል ነው። ሳውል የጌታን ደቀመዛሙርት እንዲገድላቸው ገና እየዛተ ወንዶችንም ሴቶችንም ቢያገኝ እያሰረ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣቸው ነበር። /ሐዋ.9+1-2/ ይሁንና የመውጊያውን ብረት መቃወም እስከማይቻል ድረስ ታግሶ በደማስቆ መንገድ ተገለጸለት ለአገልግሎትም ጠራው።

ስለዚህም ሳውል በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት የጌታን ስም ይሸከም ዘንድ ለእርሱ የተመረጠ እቃ ሆነ።/ሐዋ 9+3-16 1ቆሮ 15+10/ በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን እንደ ጳውሎስ ያለ አንድ ታላቅ አገልጋይ ቤተ ክርስቲያን ስታጣ እግዚአብሔር በሳውል ላይ ታጋሽ አልሆነምን!

በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን ቅዱሳንን በማሳደድ እጅግ በጣም ጨካኝ እና ቀጡ ኃይለኛ የነበረውን የኢንስና ገዥ



በእጆቹ ብዙ ቅዱሳን ሰማዕትነትን ተቀብለዋል። ይሁንና የእግዚአብሔር ትዕግሥት ኢራንዮስን ወደ እምነት መርቶታል። እርሱም እንኳን ሰማዕትነትን ተቀብሏል፤ ቤተክርስቲያንም መታሰቢያን ታደርጋለች።

እግዚአብሔር ትዕግሥቱን የሚያሳያቸው ብዙዎች ናቸው። ከእነዚህም መካከል ቅዱስ አውግስጢኖስ፣ ግብፃዊቷ ማርያም ፔላጂያ፣ ሙሴ ጸሊም እና ሌሎችም ብዙዎቹ ይጠቀሳሉ። እነዚህ ሁሉ ከኃጢአት ተመልሰው ንሥሐ የገቡ ንሥሐ በሚገቡ በሌሎች ሰዎች ልብ ውስጥም ተስፋን በመፍጠር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብርሃኖች የሆኑ ናቸው። አውግስጢኖስ ጳጳስ እና ታላቅ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሆኗል። ሙሴ ጸሊም ከታላላቅ መነኩሳት አንዱ ማርያም ዘግብፅም ባሕታዊ ሆነዋል። እግዚአብሔር በእነዚህ ሁሉ ታጋሽ ባይሆን ቅጣትን ያገኙ ነበርን፤ ይጠፉም ነበርን? የሚለው ይደንቃል። ቤተ ክርስቲያንስ ቡራኬያቸውን ታጣ ነበርን?

እግዚአብሔር በእርሱ መኖር ለማያምኑት እና ለአሕዛባውያን ትዕግስቱን ያሳይ ነበር። እግዚአብሔር ከአንድ ሚሊዮን ሩሲያዊያን በላይ ወደ እምነት እስኪመለሱ ድረስ ሶሻሊዝምን ታግሶአል። በተመሳሳይ መንገድ ሩማኒያ እና ሶቪየት ህብረት ውስጥ ብዙዎቹ ወደ ክርስትና ተመልሰዋል በጌታም ደስ ብሏቸዋል። በተጨማሪም ፈላስፎችን ወደ ክርስቲያን ተፈላሳፊዎች ቀይሯቸዋል።

ለቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳይ መርዝ እንዳዘጋጀው እንደ ጠንቋዩ እንደ አትናቴዎስ ያሉ ብዙ ጠንቋዮች ተለውጠዋል።ለአቢብ ካስቱር መርዝ ያዘጋጀው ጠንቋዩ ሲድራኩስም ሌላው ምሳሌ ነው። እነዚህ ሁለቱ አስማተኞች እምነትን

የነበረውን ኢራነስን ለረዥም ጊዜ ታገሠው:: ተቀብለዋል የሰማዕትነትንም ዘውዶች ተቀብለዋል:: የእግዚአብሔር ትዕግሥት ከእነርሱ አስማት የበለጠ ኃይል እንዳለው በመገንዘብ ወደ እምነት ተመልሰዋል::

የእግዚአብሔር ትዕግሥት ኃጢአተኛ ንሥሐ እስኪገባ ድረስ ብቻ የሚቀጥል ሳይሆን እግዚአብሔር ጣልቃ የሚገባበትን ትክክለኛ ጊዜ እስኪመርጥ ድረስ በተጨማሪነት ይዘልቃል::

- **እግዚአብሔር ለሥራው፣ ለጥበቡ እና ለመለኮታዊ ሥርዓት ሕግ ተስማሚውን ጊዜ ይመርጣል::**

እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ቤተሰቦቻችን የሴቲቱ ልጅ የእባቡን ራስ ይቀጠቅጣል ሲል ቃልኪዳን ሰጥቷቸዋል:: /ዘፍ 3÷15/ ነገር ግን ሺህ ዘመናት አልፎ እባብም የብዙዎቹን የሴቲቱን ልጆች ስኮና መቀጥቀጥ ቀጥሏል:: እግዚአብሔር በሚያስደንቅ ትዕግሥቱ ከሕግ በታች የተወለደውን ልጁን ለመላክ የዘመኑን ፍጻሜ ይጠብቅ ነበር:: /ገላ 4÷4/

ድንግል ማርያም እስክትወለድ ድረስ ጠብቋል:: ይህንን ክብር ልትሸከም የምትችል እርሷ ብቻ ናትና:: ከእርሱ በፊት በኋላ አገልግሎቱን የሚሸከሙትን የሚረከቡትን አሥራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት ጠብቋል:: ትንቢቶች ሁሉ እና ሌሎች ነገሮች መቼ መፈጸም እንዳለባቸው ትክክለኛውን ጊዜ መርጦአል:: ይህም እውነተኛ ጥበብ ነበር::

የድኅነት ሥራ ለረዥም ጊዜ ለምን ዘገየ ብሎ ማንም አይጠይቅ በእርግጥም አልዘገየም::እግዚአብሔር ለመጀመሪያ በወሰነው ጊዜ ተደርጓል:: ነገርግን የእግዚአብሔር ትዕግሥት



ለእርሱ የሚሆኑ ሁሉንም ነገሮች እና ሰዎች ሥራውን እንዲገነዘቡት እና እንዲቀበሉት እያዘጋጀ ነበር:: የድኅነት ሥራ በአዳም ዘመን ቢፈጸም ኖሮ ይህንን ሥራ የሚረዳ የሚቀበል እና የሚያምን ማንም አይኖርም ነበር:: ችግሩ ጊዜያቱን በእኛ ውሱን በሆኑ አእምሮዎቻችን ለመረዳት መሞከራችን ነው:: ጌታ ግን «አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም::» /ሐዋ 1÷7/ ብሏል::

ዳዊት በችግሩ ጊዜ «እኔን ለመርዳት ፍጠን::» /መዝ 70÷1/ በማለት እንደተናገረ እኛም እግዚአብሔርን ከመጠየቅ በፊት እንኳን በአንተ መንገድ እንደሆነ እምነት ሊኖርህ ይገባል:: የእርሱ እርዳታ እጅግ በተወደደ ተስማሚ ጊዜ ወደ አንተ እየመጣ ነው::

ለምሳሌ የጻድቁ የዮሴፍን ታሪክ ተመልከት ወንድሞቹ ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት እግዚአብሔርም እርሱን ለማዳን ምንም ነገር አላደረገም:: እነርሱ እንደባሪያ ሸጡት እግዚአብሔር ዝም ያለ መሰለ:: ዮሴፍ ባልተገባ ፍርድ ተወነጀለ ዓመታትን ወደ ቀጠረበት እስር ቤትም ተጣለ ነገር ግን እግዚአብሔር እርሱን በእርግጥ ረሳውን ወይንስ ተወውን አልረሳውም! አልተወውም:: እግዚአብሔር በትዕግሥቱ ዝግጅቶችን እያደረገ እና ጊዜ እያዘጋጀ ዮሴፍንም መሪ ወይም ልዑል ለማድረግ ሁኔታዎችን እያመቻቸ ነበር::

እግዚአብሔር የዮሴፍን ችግር ወደ ጉድጓድ እንደተጣለ ፈጥኖ ቢፈታለት ኖሮ ዮሴፍ ተራ እረኛ ሆኖ ብቻ ይቀጥል ነበር::

እግዚአብሔር ልጆቹን ያስተምራል እግዚአብሔር

ትዕግሥተኛ ታጋሽ እንደመሆኑ ልጆቹንም ደግሞ ታጋሾች እንዲሆኑ ያስተምራል ያሰለጥናቸዋልም።

ኤልያስ ከሦስት ዓመት ተኩል ረሃብ በኋላ ዝናብ እንዲዘንም ለጠየቀው ጥያቄ እግዚአብሔር ተስማምቶአል። ነገር ግን ኤልያስ ይህ እንዲሆን አንድ ጊዜ፣ ሁለት ጊዜ፣ ሦስት ጊዜ፣ ለስድስት ጊዜያትም እንኳን ዝናብም አላዘንብ እስከሚል ድረስ ጸልዮአል። ኤልያስ ተስፋ አልቆረጠም በትዕግሥትም መጸለዩን ቀጠለ። በሰባተኛውም ጊዜ የሰው እጅ የመታህል ታናሽ ደመና ከባሕር ወጣች /1ኛ ነገሥ 18+44/ ስለዚህ እግዚአብሔር ለጸሎቱ መልስ እንደሰጠው ኤልያስ አወቀ።

ለ. የሰዎች ትዕግስት

ባለፈው ምዕራፍ ስለ እግዚአብሔር ትዕግሥት ተናግረናል በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለሰዎች ትዕግሥት እንናገራለን። በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል እስከተፈጠርን ድረስ /ዘፍ1+26-27/ በትዕግሥትም እርሱን መምሰል አለብን።

ከሰው ፍጥረት የእግዚአብሔርን ትዕግሥት ያልቀመሰ፣ ያልተለማመደ ወደ ኃጢአት ጥልቅ ያልተወሰደ ማንነው? እናም ሌሎችን በተመሳሳይ መንገድ በትዕግሥት እንቀበላቸው መጽሐፍ ቅዱስ «በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል።» /ማቴ 7+2/ ይላልና።

- በሕብረታችን ውስጥ

አንዳንድ ሰዎች ሌሎች እነርሱን በሚያሰናዱበት በሚቀበሉበት ዘዴ ይከፋሉ ይህንንም መሸከም አይችሉም።



አንድ ሰው «የመግባቢያ መንገዱን እንዲቀይር ደግሜ ደጋግሜ አስጠንቅቄዋለሁ እርሱ ግን ይህን አላደረገም» ሊል ይችላል። አንዲት ሚስትም ስለባሏ እንዲሁ ልትል ትችላለች!

ይህ የአንዳንድ ሰዎች ጠባይ ነው ይህንን ለመለወጥም ከሌሎች ሰዎች ትዕግሥትን ይፈልጋሉ። የአንድን ሰው ጠባይ በፍጥነት መለወጥ ቀላል አይደለም። አንድ ሰው ምኞት ሊኖረው ችሎታ ግን ላይኖረው ይችላል። የእንደዚህ ዓይነት ሰዎች ስሜት በእነርሱ ላይ ከፍተኛ ድርሻ ሊኖረው ይችላል ስለዚህ በስሜትም ይሁን በሥራ ስሕተት እንደሆነም እንኳን ላያውቁ ይችላሉ።

ጌታችን በአንድ ወቅት ከሦስት ዓመት በላይ አብረውት ለነበሩና ትምህርቱን ሲከታተሉ ለቆዩት ደቀ መዛሙርቱ «ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና» ሲል ነግሯቸዋል። /ማቴ 11÷29/ ይሁንና እርሱ በተያዘ ጊዜ ጴጥሮስ የሊቀ ካህናቱ ባሪያ ጆሮ በሰይፉ ቆረጠ /ዮሐ 18+10/ ጌታችንም ጴጥሮስን «ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ» /ማቴ 26+52/ በማለት ገሥጸው።

ቅዱስ ጴጥሮስ ችኩልነቱን መቋቋም አልቻለም ነበር በእርሱም ላይ ለብዙ ጊዜያት ተገልጸዋል። እስከ ሕጽበተ እግር ድረስ ታግሶ ይጸና ዘንድ የጌታን ትዕግሥት ይፈልግ ነበር። /ዮሐ.13+6.10/ ከሽማግሌዎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሳ ዘንድ እንዲገባው ለደቀመዛሙርቱ በገለጠላቸው ጊዜ /ዮሐ.13+6-10/ ተመሳሳይ በሆነ ንዴት

ይህ ስሕተት እንደ ሆነ ጴጥሮስ ተናገረ። ሁሉም ደቀ መዛሙርት ዝምታ ቢመርጡም እርሱ ግን አይሁንብህ ጌታ ሆይ ይህ ከቶ አይደርስብህም በማለት ይገስፀው ጀመር። ጌታም «የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብም እንቅፋት ሆነህብኛል።» ሲል ተናገረው።

ሙሴ ጸሊምም እንዲሁ ባሕርይው እስኪለወጥ እና ተነሳሒ ትሑትም እስኪሆን ድረስ የመሪው የቅዱስ ኤካድሮስን ታላቅ ትዕግሥት ይፈልግ ነበር። እርሱም ወደ ታላቅ ቅድስ እና ለብዙ ሰዎች መምህር ወደ መሆን ተለውጦአል።

- በትዕግሥት በኃጢአተኞች ላይ የምናሳየው ቁጣ በእኛ ላይ አይገለጥም

ስለዚህ ነገር መጽሐፍ ቅዱስ «ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቁጣም የዘገየ ይሁን።» /ያዕ 1+19/ ብሏል። የዘገየ መሆን ማለት ሌሎችን በመስማት ትዕግሥተኛ እና ቻይ መሆን ማለት ነው። በዚህም አእምሮው በጥበብ የመረዳት እድል ይኖረዋል ታጋሹ ሰውም ስሕተቶችን ለማስወገድ ብቁ ይሆናል። ትዕግሥተኛ ሰው ሁልጊዜ ለቁጣ የዘገየ ነው።

- እግዚአብሔር ደካማ ተፈጥሮአችንን ስለሚያውቅ ብዙ ይታገሠናል።

ነቢዩ ዳዊት ይህንን በተመለከተ «ሁል ጊዜ አይቀስፍም ለዘለዓለምም አይቆጣም እንደ ኃጢአታችን አላደረገብንም እንደበደላችንም አልከፈለንም ... ፍጥረታችንን እርሱ ያውቃልና እኛ አፈር እንደሆንን አስብ።» /መዝ 102+9-14/



ብሏል። ስለዚህ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ የሰውን የተፍጥሮ ደካማነት እና ለውድቀት ያለውን ዝንባሌ በማስታወስ እርስበርሳችን በትዕግሥት እንወያይ።

## ሐ. ማስተማር እና አገልግሎት

አንዳንዶቹ አገልግሎታቸው ፈጣን ፍሬያት ሳይሰጥ ሲቀር ሊደክሙ እና ተስፋ ሊቆርጡ ይችላሉ። ይህንንም እንደ ውድቀት ሊቆጥሩት እንኳን ይችላሉ። በእርግጥ አገልግሎት በዝግታ ለማደግ ትግዕሥት ይፈልጋል። ጌታ ደቀመዛሙርቱን በማዘጋጀት ምን ያህል ዓመታት በአገልግሎቱ ውስጥ እንዳለፈ አስታውስ። ሦስት ዓመታት ካለፈ በኋላም እንኳን ከላይ ኃይል እስኪለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ እንዲቆዩ አዝዟቸዋል። /ሉቃ 24+49/

ከዓመታት በኋላ ፍሬ የምትሰጥ ዛፍ አስብ። አንድ አትክልት የተከለ ሰው እንደአትክልቱ ዓይነት ሦስትም ይሁን ከአምስት ወይም ሠባት ዓመት ታግሶ ይጠብቃል። ትዕግሥትንም በተግባር ይማራል።

ዳግመኛም ትዕግሥት ሕፃናትን በመውለድ እና በማሳደግ ውስጥ ጉልህ ሚና አለው። ሴቷ ከፅንስ በኋላ ልጇን ወልዳ ለማየት ዘጠኝ ወራትን ትጠብቃለች ሕፃኑ በሳል እስኪሆን እና ከማህፀን እስኪወጣ ድረስ በማህፀኗ ውስጥ በሕይወት ያድጋል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዚህ ሂደት በመደነቅ «አንድ ፅንስ ለማደግ ይህን ያህል ረዥም ጊዜ ከወሰደ አንድ ሰው በመንፈሳዊነት ለማደግማ ምን ያህል ረዥም ጊዜ እና ትዕግሥት ያስፈልገዋል» ብሏል።

አንድ ሕፃን ለመናገር ለመራመድ እና ለመማር ጊዜ

ይፈልጋል፡፡ በትዕግስት እየተጠባበቅን በአካል እና በእውቀትም ሲያድግ በማየት እንደሰታለን እንጂ ከችሎታው ባሻገር የሆኑ ነገሮችን እንዲሠራ ከእርሱ አንጠብቅም፡፡

ትዕግሥት ለስብከት ለአገልግሎት እና ለማስተማርም ያስፈልጋል፡፡ ልክ እንደዚህ ሁሉ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ከፍተኛ የመንፈሳዊነትን ደረጃዎች ሳይታገሱ ይችላሉ ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀመዝሙሩ ለጢሞቴዎስ «...ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ ዝለፍና ገሥጽ ምከርም፡፡» /2ኛጢሞ.4+2/ ያለው፡፡ ለቆሮንቶሳውያንም «ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤ ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከአሁን ድረስ ገና አትችሉም፡፡» /1ኛቆሮ 3+2-3/ አላቸው፡፡ ደግሞም አባቶች ሐዋርያት በሰጡት ደህንነት ከአሕዛብ ወደ እግዚአብሔር የዞሩትን አናስቸግራቸው ማለታቸውን፤ እና ለጣዖት ከተሰዋ፣ ከደምም፣ ከታነቀም፣ ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው ቢቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛም መንፈስ ቅዱስ ፈቅዶልናል፡፡ ሲሉ መፍቀዳቸውን ልብ እንላለን /ሐዋ15+9-29/፡፡

እንዲሁም ክብር ለርሱ ይሁንና ጌታ ክርስቶስ ጻፎችንና ፈሪሳውያንን «ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ» /ማቴ 23+4/ ሲል ገሠጻቸው፡፡

- የማስተማር ከፍተኛ ደረጃዎች ለሁሉም ሰው አይሰጡም፡፡

ማስተማር ወይም በማስተማር ውስጥ ያለ ትዕግሥት ቀስ በቀስ መልካም ፍሬ ያመጣል፡፡ አንዳንዶች የተወሰኑ መንፈሳዊ ልምምዶችን ገንዘብ ባለማድረጋቸው



አትገሥጻቸው ወይም በእነርሱ አትቀየም ይልቁንም ሐዋርያው «...ድፍረት የሌላቸውን አጽኑአቸው ለደካሞች ትጉላቸው ሰውን ሁሉ ታገሡ፡፡» /1ተሰሎ 5+14/ እንዳለው ታጋሽ ሁን፤ አበርታቸውም፡፡

አንድን ክፍል የምታገለግል በአገልግሎትህም መሻሻል የማይታይብህ አገልጋይ ከሆንህ በአገልግሎትህ ያልተሳካልህ በመሆንህ ተስፋ ማጣት ራስህንም መውቀስም ወይም ክፍሉን ፍሬ አልባ በመሆኑ ማማረር የለብህም፤ ከአንተም ይሁን ከክፍል ተማሪዎችህ ዘንድ ችግር የለም፡፡ ይህ ስለሆነ ጊዜና ትዕግሥት የሚፈልገው የአገልግሎት ባሕርይ ነው፡፡ ታዲያ ታጋሽ ሁን የሰዎች ባሕርይ፣ በአጋጣሚ ወይም በአንድ ቃል ሊለወጥ ይችላል ብለህ አታስብ፡፡ አንዲት ዶሮ እንቁላሎችን እስኪፈለፈሉና ጫጩቶቿን እስኪሰጡ ድረስ ታሞቃቸዋለች፤ትታቃፈቸዋለች፡፡ የዘር ፍሬዎችም አረንጓዴ እስኪሆኑና ፍሬ የሚሰጥ ዛፍ ሆነው እስኪያድጉ ድረስ በአፈር ውስጥ ጊዜ ይወስዳሉ፡፡ ይህ ሁሉ ትዕግሥትና ጽናት አይፈልግምን?

እኛም ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስ «እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል»/ማቴ10+22/«በመታገሳችሁም ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ፡፡»/ሉቃ21÷19/ እንደሚል በትዕግሥት ልንጸና ይገባናል፡፡ ነቢዩ ዳዊትም «ከማለዳው ሰዓት ጀምሮ እስከ ሌሊት ነፍሴ በእግዚአብሔር ታመነች፡፡» /መዝ 128+6/ አለ፡፡ ይህ ማለት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ማለት ነው፡፡

**መ. በጸሎት**

ቻይ እና ትዕግሥተኛ የሆነ ሰው ይጸልያል፤ ስለሚሰጠውም የእግዚአብሔር መልስ አይጨነቅም፡፡ እግዚአብሔር

ጸሎቱን እንደሚሰማው፣እርግጠኛ ነው:: ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ጥበብና ፈቃድ እንደሚሆን፣ በተገቢው ጊዜና መንገድም መልስ እንዲሰጠው በማመን ለእግዚአብሔር ፍቅር ይተዋል::

አንዳንድ ሰዎች ይህ መሰል ትዕግሥት የላቸውም:: እግዚአብሔርን መውቀስ እና ከእርሱ ስሕተት መፈለግ እንጂ መጠባበቅ አይችሉም:: እነርሱ ይወነጅሉታል እርሱ ግን እጅግ ይታገሳቸዋል፣ ወቀሳቸውንም ይሸከማል:: እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር ለእነርሱ እንደሚሠራ ማመን አለባቸው:: እርሱ ሊዘገይ ይችላል:: ይህ ግን ትዕግሥትና እምነት እንዲኖረን እኛን ለማለማመድ እንደሆነም እናስብ:: ይልቁንም በምሽቱ የመጨረሻ ሰዓት፣ በአሥራ አንደኛውም ሰዓት ሠራተኞችን ይጎበኝ ዘንድ ሊመጣ ይችላል::/ማቴ 20+6-7/

• እግዚአብሔር ችግሮችን ለማስወገድ ሊዘገይ ይችላል?

ይህ የሚሆነው ችግርን የሚጋፈጠው ሰው ስለሚጨነቅና፣ ስለሚበሳጭ ነው:: ወዲያውኑ ፈጥኖ በቀጥታ ችግሩ እንዲፈታ ይፈልጋል፣ ስለችግሩ ታጋሽ አይደለም:: በዚህ ወቅት እግዚአብሔር ችግሩን ይቀበላል፣ ችግሩን መፍታትም ይጀምራል:: ነገር ግን ይህን የሚፈጸመው የእርሱ ጥበብ እጅግ ተስማሚ ምቹ አድርጎ በሚገነዘበው መንገድ ነው:: ይልቁንም የእግዚአብሔር ትዕግስት ወደጭንቀት ሳይሆን በጸሎት ወደ መትጋት ይመራሃል::



## ትዕግሥት የማጣት ጉዳት

• ትዕግሥት የሌለው ሰው በጭንቀት፣ በብስጭት እና በመረበሽ ውስጥ ይወድቃል::

እንደዚህ ዓይነት ሰው ሁልጊዜ ጭንቀታም ሰዓቱን በእያንዳንዷ ደቂቃ እና ቅጽበት የሚመለከት ይሆናል:: ጸግመኛም ብስጩ እና ራሱ ብዙ ጉዳይ የሚፈጽም ሊሆን ይችላል:: ይህን ዓይነት ትዕግሥት አልባ ሰው በብስጡነቱ ልክ እግዚአብሔር ለጸሎቶቹ መልስ እንዳልሰጠው በዚህም ምክንያት እግዚአብሔርን የተቃወመ እየመሰለው ወደ ቤተ ክርስቲያን ላለመግባት እንደሚምል ሰው ውሳኔዎችን እና ድርጊቶችን በድንገት ያለ እቅድ ይፈጽማል::

• ጭንቀት እና ትዕግሥት ማጣት በሰው ክንድ እና በተሳሳተ የሰው ጥበብ ወደ መመካት ሊመራ ይችላል::

ለምሳሌ አባታችን አብርሃም እግዚአብሔር ልጅ ሊሰጠው የገባለትን ቃልኪዳን እንዳልፈጸመለት ባሰበ ጊዜ ልጅ ትሰጠው ዘንድ ወደ አጋር ለመግባት የሰውን ጥበብ ተመለከተ /ዘፍ 16+1.4/ ታዲያ ልጁ እንደሰማይ ከዋክብት እንዳልበዛ ባየ ጊዜ ኬጡራ የተባለች ሚስት አገባ እርስዋም ብዙ ልጆችን ወለደችለት /ዘፍ 25+14/

በእርግጥ የሰው ዘዴዎች ፈጣን ውጤቶችን ሊያመጡ ይችላሉ:: ነገር ግን እነዚህ ዘዴዎች ሊዘገይ ቢችልም ለተወሰነ ዓላማ ለቡራኬ እና ለጥቅም እንደሆነው እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ አይደሉም::

የእግዚአብሔር መንገዶች ረጋ ያሉ ቀስ በቀስ እና ደረጃ በደረጃ ወደግብ በሰላም የሚመሩ ናቸው::

አንዳንድ ሰዎች ሁልጊዜ ተናጋሪዎችን መረበሽ እንጂ ተናጋሪዎች ንግግራቸውን እስኪጨርሱ ድረስ ሊያደምጡ የማይችሉ ትዕግስት አልባ ናቸው::

ሌሎች ሰዎች ችግሮቻቸውን ለመፍታት ትዕግስት የሌላቸው ናቸው:: በዚህም ምክንያት እርዳታ እና መፍትሔዎችን እንዲሰጧቸው በመሻት ጠንቋዮችንና መተተኞችን ይፈልጋሉ::

ትዕግስት እና ጽናት የሌላቸው ሰዎች የሚያጠፋቸው ጥፋቶች በእርግጠኝነት እጅግ ብዙዎች ናቸው::



# ምዕራፍ አምስት

# ቸርነት

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን የመንፈስ ፍሬ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት.../ገላ. 5+22/ ነው:: ባለፉት ምዕራፎች ስለ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት ጽፈናል አሁን ደግሞ ወደ ቸርነት እንመጣለን::

ሐዋርያው ስለጌታ ሲናገር «ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንሥሓ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን?»/ሮሜ 2+4/ ይላል:: ይህ ታዲያ የሚገልፀውም እኛን ለሚታገሥ የእግዚአብሔር ትዕግሥት እና ወደ ንሥሓ ስለሚመራን መልካምነቱ ነው ::

ዳግመኛም ሐዋርያው እንዳለው «ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ እንደምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን::»/ቲቶ.3+4-5/ ስለዚህ እስከ መስቀል ሞት ድረስ የከፈለው መሥዋዕትነትና በጥምቀት የሰጠን የእግዚአብሔር ይቅርታ የቸርነቱ የምሕረቱ እና የበጎነቱ ማስረጃ ነው::

ቸርነት የእግዚአብሔር ባሕርይ እንዲሁም ከሰው ልጅ ጋር ባለው ግንኙነት ልዩ መገለጫው ነው:: በተጨማሪም ሐዋርያቱ የሚታወቁበት በዚሁ ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ ስለ እርሱ እና ስለ አገልግሎት አጋሮቹ «በሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችንን እናማጥናለን በብዙ

መጽናት… በድካም፣ እንቅልፍ በማጣት፣ በመጾም፣ በንጽሕና ፣ በእውቀት በትዕግሥት በቸርነት።» /2ቆሮ6÷4-6/

- **አባቶቻችን ሐዋሪያት ቸር እንድንሆን ጥሪ አድርገውልናል**

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እርስበርሳችሁም ቸሮችና ርህሩሆች ሁኑ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ ምሕረትን ርኅራኄን ቸርነትን ትሕትናን የዋህነትን ትዕግሥትን ልበሱ።» /ኤፌ4+32 ቆላ 3+12/ ከጥቅሱ መገንዘብ የሚቻለው እነዚህ ምግባራት እርስ በእርስ የተሳሰሩ መሆናቸውን ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም እንዲሁ «በመጨረሻው ሁላችሁ በአንድ ልብ ሁኑ የሌላው መከራ ለእናንተ እንደሚሆን አድርጉ እንደ ወንድሞች ተዋደዱ ርኅሩሆችና ትሑቶች ሁኑ ክፉን በክፉ ፈንታ ወይም ስድብን በስድብ ፈንታ አትመልሱ በዚህ ፈንታ ባርኩእንጂ…።»/1ጴጥ3+8–9/

ነገር ግን ቸርነት ምንድርነው? ጠባይቱ ምንድር ናቸው ? ቸር ሰዎችን እንዴት እንገልጻቸዋለን ? ብለን እንጠይቃለን።

በእርግጥ ቸርነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአንድነት የተገለጡ እነዚህ ሁሉ ምግባራት ናቸው። እነርሱም ከጭካኔ ከሁከት እና ከትዕቢት የፀዳ የየዋህነት፣የርህራሄ፣የደስታና የትህትና ሕይወት ፍሬ ነው። ቸርነት ቅዱስ ጴጥሮስ እንደ ገለጸው ረጋ ያለ ሰውን የሚያመለክት የእርጋታ መንፈስ ነው። በሚያሳዝን ሁኔታ አንዳንድ ሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት ጾምና ጸሎት ብቻ እንደሆነ አድርገው ያስባሉ፤



በሌሎች ሰዎች ላይ በንዴት ስለሚፈጽሟቸው ክፉ ድርጊቶችን ከግምት ውስጥ አያስገቡም።

ለእነዚህም ከሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነታችሁ በቸርነት እስካልሆነ ድረስ ፈጽማችሁ ሃይማኖተኞች አትሆኑም ማለት አለብን። ይህ የመንፈስ ፍሬ የሌለው ሰው በእርግጥም መንፈሳዊ ሰው አይደለም። በመንፈስ እየተመራ አይጓዝምና። ስለዚህ በትሕትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም እርስበርሳችሁ በፍቅር ታገሡ። /ኤፌ. 4+22/ /ገላ 5+22/።

ቸርነት በጠፋው ልጅ ታሪክ ውስጥ አባት ለጠፋው ልጅ እና ለታላቅ ወንድሙ ርህራሄ ባሳየበት መንገድ በግልጽ ታይቷል።

የጠፋው ልጅ ከአባቱ ገንዘብ የሚደርሰውን ክፍል ለመጠየቅ ወደ አባቱ ሄደ አባቱ ግን በሕይወት እያለሁ የእኔን የአባቱን ገንዘብ እንዴት ለመውረስ ይፈልጋል በማለት አልገሠጸውም። በተቃራኒው በትሕትና እና በቸርነት ሀብቱን በማካፈል ለልጁ ድርሻውን ሰጠው። ልጁም በከንቱ ሕይወት እና በአባካኝ ኑሮ ከአባቱ ገንዘብ የደረሰውን ካጠፋ በኋላ ችግረኛ እና ረሀብተኛ ሆነ፤ ጥፋቱን በማመንም ወደ አባቱ ቤት ተመለሰ። አባቱ በደስታ ተቀበለው። ልጁ ከአባቱ መንገድ ቢያፈነግጥም ከመጸጸቱና ይቅርታ ከመጠየቁ በፊት በደስታ ሮጦም በጉልበቱ በመውደቅ ሳመው። በልጁ መመለስ በመደሰት የተሻለ ልብስ አለበሰው ለእጁ ቀለበት ለእግሩም ጫማ ሰጠው። የሰባ ፍሪዳም አምጥቶ አረደለት። እንዴት ቸር ነበር!አባቱ ከቸርነቱ የተነሳ ልጁ የልብ መሰበር ወይም ኃፍረት እንዲሰማው አላደረገም።

ታላቁ ልጅ አባቱ ወንድሙን በደስታ በመቀበሉ ምክንያት በወንድሙ መመለስ ወደ ቤት ለመግባት ከነእርሱ ጋር ለመደሰት ፍቃደኛ ባለመሆን አባቱን ባግረረውና በተቆጣ ጊዜ እንኳን አልተናደደም:: ስግብግብና ኢሚዛናዊ በመሆኑ ምክንያት እርሱን በመተቸት በተናገራቸው ጠንካራ ቃላት አባቱ አልተበሳጨም::«እነሆ ይህን ያህል ዓመት እንደባሪያ ተገዝቼልሃለሁ ከትእዛዝህም ከቶ አልተላለፍሁም ለእኔም ከወዳጆቼ ጋር ደስ እንዳለኝ አንድ ጥቦት ስንኳ አልሰጠኸኝም ነገር ግን ገንዘብህን ከጋለሞቶች ጋር በልቶ ይህ ልጅህ በመጣ ጊዜ የሰባውን ፍሪዳ አረድህለት::» አለው:: /ሉቃ 15+29.30/

በእነዚህ ቃላት ከመናደድ ይልቅ በትሕትና «ልጄ ሆይ አንተ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ነህ ለእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው ዳሩ ግን ይህ ወንድምህ ሞቶ ነበር ህያው ስለሆነ፤ ጠፍቶም ነበር ስለ ተገኘ፤ ደስ እንዲለን ፍስሐም እንድናደርግ ይገባልና አለው::»/ሉቃ 15+31.32/

ታላቁ ልጁ አባቱን እና ወንድሙን በመቃወም ለተናገረው ትችት አባቱ አልወቀሰውም እንዲሁም አልገሠጸውም ይልቁንም በቸርነት «ለእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው....ደስ እንዲለን ፍስሐም እንድናደርግ ይገባል» ሲል አዎንታዊ መልስ መለሰለት::

ቸር ልብ ብዙ አይወቅስም ቢገስጽም እንኳን ጎጂ በሆኑ ቃላት አይደለም::«ሰውየውን አላውቀውም»/ማቴ.26+69.74/ በማለት ሦስት ጊዜ የካደውን እና የማለውን ቅዱስ ጴጥሮስን ጌታ እንዴት እንደተቀበለው ተመልከት:: ጌታ ከትንሣኤው በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስን ባገኘው ጊዜ ከመሐላ እና ከስድብ ጋር



ሦስት ጊዜ እንደካደው አላስታወሰም ነገር ግን እርሱን ከመገሠጽ «የዮና ልጅ ስምኦን ሆይ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?» ብቻ ነው ያለው በእያንዳንዱ ጊዜም ነበር ጌታም «ጠቦቶቼን ጠብቅ በጎቼን አሰማራ» ያለው ጴጥሮስም አዘነና «ጌታ ሆይ አንተ ሁሉን ታውቃለህ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ» /ዮሐ 21+15-17/ አለው::

በእርግጥ ቸርነት የተሞላ ልብ በደግነቱ ሰዎችን ያሸንፋል:: ጌታ ቀረጥ የሚሰበስበውን ዘኬዎስን እና ሳምራዊቷን ሴትን እንዲሁም እግሮቹን በእንባዋ ያጠበችውን እና በፀጉሯ የጠረገችውን ሴት አሸንፏል:: እነዚህን ሁሉ በቸርነት እና በደግነት በተሞላው አቀራረብ አሸንፋቸው ከእነርሱም አንዳቸውንም ስንኳ አልወቀሰም ፈጽሞም ኃይለ ቃልም አልተናገራቸውም::

በአንጻሩ ግን ኃጢአተኞችን የሚቀበሉ ወይም ኃጢአተኞችን የሚያስቡ ሰዎች ይህን ያደርጋሉ የተቀደሰ ፍላጎት እና የእውነት ምስክርነት አድርገው በማሰብ አዘውትረው ኃጢአተኞች ብለው የሚፈርጁአቸውን ሰዎች በአስከፊ ቃላት ይገሥጹአቸዋል::

ኃጢአተኞችን ወደ ንስሓ እየመሩ እንደ ሆነ አድርገው ራሳቸውን ያስባሉ:: ስለ ጌታችንም ከእነርሱ በተለየ መልኩ እንደሚከተለው ተገልጾአል:: «አይከራከርም አይጮህምም ድምፁንም በአደባባይ የሚሰማ የለም::» /ማቴ. 12+19 ኢሳ. 42+3/

ቀረጥ ሰብሳቢውን ዘኬዎስን ከሕዝብ መሐል በስሙ ጠርቶ በቤቱ አብሮት እንዲውል እና እንዲጋበዝ ጠራው እንጂ የቀድሞ ኃጢአቱን አላስታወሰው፤ ሁሉም ከኃጢአተኛ

ሰው ጋር ሊውል ገባ ብለው ባንጎራጎሩ ጊዜ እርሱ ደግሞ « የአብርሃም ልጅ ነውና ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል» በማለት አወጀ:: /ሉቃ. 19+5-9/ ተመልከት! አስተውል! ጌታ ዘኬዎስን ቢገሥጸው ኖሮ ያሸንፈው ነበርን ? አያሸንፈውም ነበር! በቸርነቱ እና በደግነቱ ነው ያሸነፈው::

አንድን ሰው ስለ ኃጢአቱ ለመገሠጽ በሚደረግ ጭካኔ እና ኃጢአቱን በመናዘዝ በራሱ ፍቃድ ንሥሓ እንዲገባ በሚመራው ቸርነት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ ዘኬዎስ ላይ የተከሰተው ሁኔታም ይህ ነበር:: መጥፎ ዝና ስም ቢኖረውም በቤቱ ጌታን ለመቀበል ብቁ የሆነ አደረገው እንጂ ኃጢአተኛ እንደ ነበር ጌታ አልተናገረውም:: ይህ ደግነት ዘኬዎስ «ጌታ ሆይ ካለኝ ሁሉ እኩሌታውን ለድሆች እሰጣለሁ ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደሆንሁ አራት እጥፍ እመልሳለሁ::»/ሉቃ. 19+8/ እንዲል አደረገው::

በተመሳሳይ መንገድ ጌታ ሳምራዊቷን ሴት ተቀበላት:: ሳምራዊቷን ሴት ስለኃጢአቷ እና ስለመጥፎ ጠባይዋ አልገሠጻትም በቸርነት ረጋ ብሎ ስለሕይወት ውሃ እና በእውነት መንፈስ ስለማምለክ ነገራት እንጂ::/ዮሐ4÷14-23/ «ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነይ» ባላት ጊዜ ደግሞ በደግነት ወደ ንስሐ መራት::

ከእርሷ ጋር ያለው ባሏ እንዳልሆነ ግንኙነታቸውም በሚያስቀይም ቃል ሊገለጽ የሚችል እንደሆነ አውቋል:: ነገር ግን ጌታ የእርሷን ስሜት ላለመጉዳት ይህንን አላለም:: ይልቁንም «ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ አምስት ባሎች ነበሩሽና አሁን ከአንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም በዚህስ እውነት ተናገርሽ::»/ዮሐ.4+16-18/ አላት::



ጌታ ያንን አሳፋሪ ኑዛዜዋን በሁለት የምስጋና ቃላት እንዴት እንዳሸነፈው ተመልከት:: «መልካም ተናገርሽ» በሚል ቃል ጀመረ ይህንንም «በዚህስ እውነት ተናገርሽ» የሚል ቃል አስከተለበት::

እርሷ የኃጢአት ሕይወት ብትመራም እንኳን ሊያስመሰግናት የሚያበቃ አንድ ነገር በእርሷ ውስጥ አግኝቷል:: በዚህ መንገድ ወደ ንስሓ መራት ከዚህ በተጨማሪም እንድታምን እና እምነቷን እንድታውጅ አደረጋት:: ሴቲቱም «ጌታ ሆይ አንተ ነቢይ እንደሆንህ አያለሁ» አለችው ወደ ሰዎችም«ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን?»በማለት በእርሱ እንዲያምኑ ለመጥራት ሄደች:: ስለዚህ ጌታ እርሷንና የከተማዋን ሰዎች ወደ እምነት በማምጣት አሸንፏል:: /ዮሐ 4+19-29/

- ጌታ በኃጢአት ተይዛ የነበረችዋን ሴት በተመሳሳይ ቸርነት ተቀበላት::

ጸፎችና ፈሪሳዊያን እርሷን ለመውገር በመመኘት እንደ አራዊት አሰፍስፈው መጡ:: ሕጉ እንደሚያዝዘው ፍቃዱን ይሰጣቸው ዘንድ ፈለጉ:: ውርደቷን እና ሃፍረቷን ተሸክመላት ሊወግሯት የፈለጉአትንም ገሠጻቸው:: እርሱ ግን «ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት::» በማለት ገሰጻቸው:: በዚህም ሊወግሯት በሚፈልጉት ፊት ሁሉ ውርደትዋንና ሀፍረቷን ተሸከመላት /ዮሐ 8+7/::

ደግሞም ጎንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ ምናልባትም የእያንዳንዳቸውን ኃጢአት:: አዎ ሴቲቱ

በኃጢአት ወድቃ ነበር። ነገር ግን በእርግጥ ከሴቲቱ ጋር በኃጢአት የወደቀ ሰውም በመካከላቸው ነበር።

ሴቲቱን ከከሳሾቿ ካዳናትና እነርሱም ከወጡ በኋላ «እኔም አልፈርድብሽም ሂጂ ከአሁንም ጀምር ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ» አላት። ሴቲቱ በፈራጆች ላይ በመፍረድ እና «እኔም አልፈርድብሽም» በማለት ሕይወቴን ከውግረት የሚያድን እንዲህ ያለ ቸር እና ደግ ሰው አገኛለሁ ብላ አላሰበችም!

እግሮቹን በእንባዎቿ ላጠበችለት ኃጢአተኛ ሴትም እንዲሁ አድርጓል አንዲት አስከፊ ቃል እንኳን አልተናገራትም ይልቁንም «ኃጢአትሽ ተሰርዮልሻል» /ሉቃ.7+48/ አላት እንጂ። ለስምዖን እና ሲነቅፏት ለነበሩት ለፈሪሳውያን እርሷ ከእነርሱ የተሻለች እንደሆነችና በወዳጃቸው በዚያው መጠን ኃጢአቷ እንደተሰረየላት አረጋገጠላቸው። በቸርነቱም ከእርሷ ለምስጋንና የሚያበቃ ነገር ፈልጎ አገኘ።

ሁልጊዜ ቸርነት ሊመሰገኑ የሚችሉ መልካም ነጥቦችን ይፈልጋል እንጂ በጥቁር ነጥቦች ላይም ፈጽሞ ትኩረት አያደርግም። እዚህ ላይ የበረራ ሳይንስ ጥበብ ትምህርት ቤት መምህር የነበሩትን ሰው ታሪክ አስታውሳለሁ። መምህሩ ተማሪዎቻቸውን ለመጨረሻው የምረቃ ፈተና አዘጋጅተው እንደጨረሱ አንድ ተማሪ በአውሮፕላን በረረ ወዲያውኑም አሮፕላኑን መቆጣጠር ተሳነው። አውሮፕላኑ በአንደኛ ደረጃ በአየር ላይ መወዛወዝ ጀመረ። ተማሪው በእርግጠኛነት በፈተና እንደሚወድቅና እንደሚሰናበት በማየት ቢያንስ ራሱን ከሞት እንዴት ማዳን እንዳለበት አሰበ። ስለዚህ ከአውሮፕላኑ ጋር ሳይጎዳ ለመውረድ ታገለ።



ተማሪው የስንብት ውሳኔውን ከመምህሩ ለመስማት ጠበቀ ነገር ግን መምህሩ እጁን ሞቅ አድርገው ጨብጠው ለእርሱ በሚደንቅ ሁኔታ «በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ ያለ አንድ ብቃት ያለው አብራሪ ሊፈጽም የሚገባውን አድርገህ በተሳካ ሁኔታ ወደ ምድር በመመለስህ እንኳን ደስ አለህ አሉት።

ቸር ልብ ደካማዎችን ያበረታታል ይደግፋል እንጂ አይንቅም መጽሐፍ ቅዱስ «ድፍረት የሌላቸውን አጽኑአቸው ለደካሞች ትጉላቸው ሰውን ሁሉ ታገሡ» /1ተሰሎ. 5+14/ ይላል።

በርግጥ እግዚአብሔር በዚህ መንገድ ካልተቀበልን በስተቀር እኛ እንጠፋለን። በአንዱ አምስት መቶ ዲናር በሁለተኛውም አምሳ ስለነበረባቸው ተበዳሪዎች ጌታ «የሚከፍሉትም ቢያጡ ለሁለቱም ተወላቸው»/ሉቃ7+42/ አለ።

ኢየሩሳሌምንም በደሟ ተለውሳ ባያት ጊዜ አላጠፋትም ይልቁንም ከደሟ አጠራት፤ በዘይትም ቀባት፤ ወርቀዘቦም አለበሳት፤ በራስዋ ላይ የክብር አክሊል አደረገላት፤ እጅግ በጣም ውብ ሆነች ለመንግሥትም ደረሰች።/ሕዝ16+6-13/

አንዳንድ ጊዜ ጌታ በቸርነቱ ለደካሞች ይቅርታ ማድረግን ይፈልጋል። ጌቴሴማኒ በምትባል ስፍራ ከእሱ ጋር ለነበሩት አንድ ሰዓትም ከእርሱ ጋር ተግተው መቆየት ሳልቻሉት ለሦስቱ ደቀመዝሙር ይቅርታን አደረገላቸው። «መንፈስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው»/ማቴ. 26+41/ በማለት ይቅርታን ሰጣቸው፤እነርሱ ቢተኙም መንፈስ መዘጋጀቷን ተናገረ፤ መተኛታቸውም በሥጋ ደካማነት ምክንያት መሆኑን ገለጸ።

ከምሕረቱ የተነሳ እንደ ኃጢአታችን አላደረገብንም:: እንደ መተላለፋችንም አልቀጣንም:: ምክንያቱም ፍጥረታችንን እርሱ ያውቃልና አፈር እንደሆንን እርሱ ያስባልና:: /መዝ 102/ በተመሳሳይ ቸርነት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ምሕረት ለሞቱ ሰዎች እንዲደረግ «ፈራሽ ሥጋ ለባሾች የዚህ ዓለም ነዋሪዎችም ነበሩ» በማለት በመጽሐፍ ግንዘት ውስጥ ትጸልያለች::

እግዚአብሔር በቸርነቱ የሰዎችን ሁኔታ እና ደካማ ባሕርይ ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባል ስለዚህም ይቅር ይላቸዋል:: እርሱ በነፋስ ኃይል በአየር ላይ የተረፈ ትቢያ እንደሆኑ ያውቃል:: ስለዚህ ንፋሱ ጋብ እስኪል እነርሱም እስኪጸኑ ድረስ ይታገሳቸዋል::

እግዚአብሔር በቸርነቱ ልጆቹ እርሱን እንዲወቅሱ ወይም ከእርሱ ጋር እንዲከራከሩ ይፈቅድላቸዋል እነርሱ መጥፎ ቃላትን ሊናገሩ ይችላሉ እርሱ ግን አይናደድም በበለጠ ቸርነት አመለካከቶቻቸውን በነፃነት እንዲገልጹ ዕድል ይሰጣቸዋል::

አብርሃም ስለ ሰዶም በእግዚአብሔር ፊት ምን ያህል እንደታገለ ተመልከት«...በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ» «...እንደዚህ ያለው አድራጎት ከአንተ ይራቅ:: የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን»? /ዘፍ. 18÷28/ ሲለው ይህ እንዴት ልዩ ያልተለመደ ነበር::

አብርሃምም ታዲያ ከእግዚአብሔር ጋር መደራደር ጀመረ በከተማይቱ ውስጥ አምሳ ጻድቃን ባገኝ... አርባ... አሥር ብቻም እንኳን፤ እግዚአብሔርም «ስለ አሥሩ አላጠፋም» አለ:: /ዘፍ 18÷26-32/



እግዚአብሔር በቸርነቱ የአብርሃምን ቃል እንዴት እንደተቀበለ እና አብርሃም እስከመጨረሻው ሕቅታ ድረስ እንዲደራደር እንደፈቀደለት ተመልከት::

በተመሳሳይ ቸርነት ሙሴ ለሕዝቡ ያደረገውን አማላጅነት ተቀብሎአል:: በግብፅ እና በበረሃ እግዚአብሔር ለነርሱ ካደረገላቸው ተዓምራት ባሻገር ቸርነቱም ተደርጎላቸው ነበር:: ነገር ግን ራሳቸው የሠሩትን የወርቅ ጥጃ ሲያመልኩ በቁጣ ያጠፋቸው ዘንድ ፈለገ::

ነገር ግን ሙሴ ጣልቃ በመግባት ቁጣህ በታላቅ ኃይልና በጽኑ እጅ ከግብፅ ምድር በወጣኸው በሕዝብህ ላይ ስለምን ተቃጠለ...ግብፃውያንስ በተራራ መካከል ሊገድላቸው ከምድርም ፊት ሊያጠፋቸው ለክፋት አወጣቸው ብለው ስለምን ይናገራሉ ከመዓትህ ተመለስ ለሕዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ::»ሲል ጸለየ/ዘጸ.32+11-12/ እግዚ አብሔርም ይህን ቃል በመስማት ይቅር አላቸው እንጂ አልተቆጣም::

ነቢዩ ኤርምያስም«አቤቱ ከአንተ ጋር በተምዋገትሁ ጊዜ አንተ ጻድቅ ነህ:: ነገር ግን ከአንተ ጋር ስለፍርድ ልናገር:: የኃጢአተኞች መንገድ ስለምን ይቃናል? በደልንስ ለሚያደርጉ ሁሉ ስለምን ደኅንነት ይሆናል? /ኤር.12÷1/ አለው::

እግዚአብሔር ስለ ፍርዴ የሚናገረኝ ይህ ትቢያ ማን ነው? የኃጢአተኞች መንገድ ስለሚቃናበት ይህን በተመለከተ ስለ አደረግሁት ዝምታዬስ ሊገልጽልኝ እንዴት ደፈረ? አላለም ይልቁንም በቸርነት ሰማው አጽናናውም::

የእግዚአብሔር ቸርነት ከነቢዩ ዮናስ ጋር ባደረገው

ንግግር ውስጥም ደግሞ ታይቷል።እግዚአብሔር ዮናስ ስላልታዘዘው አልተቃወመውም ወደ መታዘዝ በጥበብ መራው እንጂ፤ ከዓሣ ነባሪ ሆድ አድኖታል። ዳግመኛም በአገልግሎቱ ነነዌን ያስጠነቅቅ ዘንድ እምነት ጥሎበታል። ነገር ግን ነነዌ ንስሓ ገባች፣ እግዚአብሔርም ቅጣቱን በነነዌ ሕዝብ ላይ እንዳላደረገ ባየ ጊዜ ዮናስ ከቶ ደስ አልተሰኘም አሁንም «ከሕይወት ሞት ይሻለኛልና እባክህ ነፍሴን ከእኔ ውሰድ» አለው እግዚአብሔርም በትሕትና «በውኑ ትቆጣ ዘንድ ይገባሃልን?» በማለት ገሰጸው/ዮና. 4÷1 –4/። እግዚአብሔር አምላክም ዮናስን ባዘጋጀት ቅል ደስ አሰኘው፣የነነዌንም ንስሓ ለምን እንደተቀበለ ገለጸለት። በእርግጥ ቁጡነት የምንወዳቸውን እንድናጣ ያደርገናል፣ ቸርነት እና ደግነት ግን በጠላቶቻችን ላይ ድል እንድንቀዳጅ ያደርጉናል።

ይሁንና ቸርነት ገደብ አለው። በእርሱ ያልተጠቀሙበት ቅጣት ይከተላቸውም ዘንድ ግድ ነው። ሐዋርያው ስለዚህ ሲናገር «የእግዚአብሔር ቸርነትና ጭከና ተመልከት ጭከናው በወደቁት ላይ ነው በቸርነቱ ግን ጸንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው። ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቆረጣለህ።»/ሮሜ.11+22/ብሏል። እዚህ ላይ ለሦስት ዓመታት ፍሬ ያልሰጠችውን ባለቤቷም ሊቆርጣት የፈለጋትን ዛፍ እናስታውሳለን። የወይን አትክልት ሠራተኛውም ለባለቤቱ«ጌታዬ ሆይ ዙሪያዋን እስክኮተኩትላትና ፋንድያ እስካፈስላት ድረስ በዚች ዓመት ደግሞ ተዋት። ወደፊትም ብታፈራ ደኅና ነው ያለዚያ ግን ትቆርጣታለህ» /ሉቃ 13+6-9/ አለው።



# ምዕራፍ ስድስት

# በጎነት

በገላትያ ምዕራፍ አምስት ከተገለጹት የመንፈስ ፍሬዎች መካከል አንዱ በጎነት ነው። ጌታ «ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም» /ሉቃ. 18+19/ ብሎ ሳለ አንድ ሰው እንዴት በጎ ሊሆን ይችላል።

በጎነት ሲባል ንጽጽራዊ በጎነት ማለት ነው፤ ፍጹም በጎነት የእግዚአብሔር ባሕርይ ብቻ ነውና። ይህ በጎነት በሰው ውስጥ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እና ሰው ለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የሚሰጠው መልስ እንዲሁም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለው ኅብረት እንደሚነጻጸር ያለን ጽጽር ነው።

«የሰማዩ አባታችን ፍፁም እንደሆነ እናንተም ፍጽማን ሁኑ»/ማቴ. 5÷48/ ተብሎ በጌታ ቃል ከተገለጸው ፍጹምነት ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህም ንጽጽራዊ ፍጹምነት ነው ትክክል ፍጹምነት የእግዚአብሔር ሕርይ ብቻ ነው።

## በጎነት ሁለት ዓይነት ነው አሉታዊና አዎንታዊ

አሉታዊ በጎነት ማለት ኃጢአትን ማስወገድ ነው። ይህም ብዙዎቹ አሥርቱ ትእዛዛት ውስጥ በአብዛኛው ተመልክቶአል። ለምሳሌ «እግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፣የተቀረጸውን ምስል ለአንተ አታድርግ፣ አትግደል፣አታመንዝር፣አትስረቅ፣በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር የባልንጀራህን ሚስት አትመኝ...»/ ዘዳ. 5+11 -21/በሌላ በኩል አዎንታዊ በጎነት በብሉይ ኪዳን ውስጥ

«አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍ ጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ»/ዘዳ. 6÷5/ በሚለው ቃል ውስጥ ተገልጿል። አዲስ ኪዳንም ውስጥ ክርስቶስ ስለ ብፁዓን በተናገራቸው ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ተገልጿል፤ በመንፈስ ድሆች የሆኑ...የዋሆች... ልበ ንጹሖች... የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው...ወዘተ።/ማቴ. 5÷3/ ዳግመኛም እዚህ ምዕራፍ ላይ እየተነጋገርንበት ባለው የመንፈስ ፍሬ ላይም በግልጽ ተቀምጦአል።

ሁለቱንም መንገዶች አሉታዊውንና አዎንታዊውን መከተል አለብን፤ ሁሉንም ዓይነት ኃጢአቶች ለማስወገድ እና በመልካም ምግባራት ሁሉ ለመጓዝ።

አንድ ሰው ሙሉ በጎነትን ገንዘቡ ካደረገ ከኃጢአት ነፃ ይሆናል። ኃጢአት ሊሸሸው ይችላል። በጎነቱ ከቀነሰ ኃጢአትን በእርሱ ላይ ያንጸባርቃል ኃጢአትንም ያደርጋል። በጎነትንም ሙሉ በሙሉ ካጣ ኃጢአት በመሥራት እርካታ ይሰማዋል ለኃጢአት ተገዢ ይሆናል ኃጢአትንም እንኳን አጥብቆ ይፈልጋል።

ስለዚህ የበጎነት ሕይወት ለመምራት «እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአት እሠራለሁ? የሚል ደረጃ መድረስ አለበት /ዘፍ. 39÷9/። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም... ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም» /1ኛ ዮሐ 3÷9/ ብሏል።

እውነት ነው መንፈሳዊ ሰው ሊያደርጋቸው ወይም ሊሠራቸው የማይችሉ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ የሚያሰናክል ወይም የውሸት ቃል ሊናገር አይችልም።ይህን ካደረገ ራሱን



ይንቃል የትሕትና ሥራም ፈፅሞ ሊሠራ አይችልም። አንድ ሰው የበለጠ በበጎነት ሲያድግ የበለጠ ስህተት ፈጽሞ ሊሠራ አይችልም።

ይሁንና በጎነት ማድረግን በተመለከተ አሳሳቢ ነገር አለ እርሱም አንድ ሰው የተወሰኑ ኃጢአቶችን እንደቀላል ነገር በመቁጠር ሊፈርድ ኃጢአቶችን በተመለከተም የሚጨነቅባቸው ላይሆን ይቻላል።

ኃጢአት ቀላል ወይም ከባድ ተብሎ ቢፈረጅም ተመሳሳይ ነው። ጌታ «ወንድሙን ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነም እሳት ፍርድ ይገባዋል።»/ማቴ. 5÷22/ እንዳለ በእርግጥ ከሌሎች ኃጢአቶች በበለጠ እጅግ መጥፎ የሆኑ አንዳንድ ኃጢአቶች አሉ። ነገር ግን ሁለቱም ዓይነት ኃጢአቶች በጎነትን ይጻረራሉ። በጎ ሰው ይህንንም ሆነ ያኛውን አይሠራም። ስለዚህ ሐዋርያው «እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ» /ኤፌ. 5+15/ ይላል።

### በጎነት የመንፈስ ፍሬ የመሆኑ ትርጉም ምንድር ነው?

ሁለት ትርጉም እንዳለው ምንም ጥርጥር የለውም። በሰው ልብ ውስጥ የሚገኝ የመንፈስ ቅዱስ የሥራ ውጤት ነው። እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ በሰው መንፈስ ውስጥ ለሚሠራው ሥራ ሰው የሚመልሰው የመንፈስ ፍሬ ነው። የሰው መንፈስ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር በፍላጎት እና በሥራ ተካፋይ የሚሆንበት ነው።

• የሰው ከኃጢአት ጋር መታገልስ እንዴት ነው ?

እንዲህ ዓይነት ሰው በጎ ነው ማለት እንችላለን? ሐ ዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለዚህ ትግል ይጠራናል፤ ይህንንም

«መታደል» ብሎ ይጠራዋል:: ዕብራውያንን «ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም » /ዕብ. 12+4/ በማለት ገሥጸቸዋል:: ስለዚህ ይህንን ከኃጢአት ጋር መጋደል ወደ በጎነት የሚመራ ነገር ልንለው እንችላለን:: ይህ የሚከሰተው ሰው በኃጢአት ላይ ድል ሲቀዳጅ እና መጋደል የማይኖርበትን የእግዚአብሔር ፍቅር ሲወርስ ነው::

ይሁንና መታገልን በሁለት ዓይነት ትግሎች መለየት አለብን:: አንደኛው ዓይነት ትግል በቅናት እና በአጋንንት ውጊያዎች በቅዱሳን ላይ እንደሚከሰተው ያለ ከውጭ የሚመጣ የኃጢአት ተቃውሞ ነው:: ይህ ዓይነት ትግል በጎነትን አይጻረርም:: ይልቁንም የሰው በጎነት የሚታገለውን ኃጢአት የመቃወሙ ማረጋገጫ ነው:: ይሁንና አንድ ሰው በዚህ ትግል ደም እስከ ማፍሰስ ድረስ ኃጢአትን ይቃወማል እንጂ ለኃጢአት ተገዢ አይሆንም::

ሌላው ዓይነት ትግል ከውስጥ፤ ከልብ፤ ከአእምሮ እና ከስሜቶች ከሚመጣ ኃጢአት ጋር በተቃውሞ የሚደረግ ትግል ነው:: ይህ የሚያሳየው ውስጣዊ ማንነት ንጽሕናን ወይም በጎነትን ለማግኘት አሁንም እየታገለ መሆኑን በጎነትን ሙሉ በሙሉ አለማግኘቱን ነው:: ይሁንና ይህ ትግል በጎ ለመሆን በመፈለግ የሚመነጭ እና ከልብ የሚደረግ መልካም ትግል ነው::

ኃጢአት መጥፎ ነው:: ጻድቅም ሁልጊዜ ከኃጢአት ይሸሻል:: ስለዚህ አንድ ኃጢአተኛ በምስጢር እና በጨለማ ኃጢአትን ያደርጋል እንጂ በጻድቅ ሰው ፊት አያደርግም::

ሰው ኃጢአት ሲፈጽም ጠባቂ መልአክ ከዙሪያህ እየራቀ



ነው:: ጠባቂ መልአክህ ኃጢአት ከመሥራት ሊጠብቅህ ይሞክራል:: ነገር ግን አንተ በዚህ ከገፋህበት ጥበቃውን ያቆማል ጠላትም አንተን በመንገዱ ያገኝሃል:: ኃጢአትም በጻድቃን እና በመላእክት ፊት እጅግ መጥፎ ከሆነ ቅዱስ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት ይልቁንም ምን ያህል መጥፎ ይሆን?

- ኃጢአትን በእግዚአብሔር ፊት ስለምንፈጽም መጥፎ ነው::

ስለዚህ ነቢዩ ዳዊት በንስሓ መዝሙሩ ውስጥ «አንተን ብቻ በደልሁ በፊትህም ክፉትን አደረግሁ» ብሏል:: ይህ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት የሚደረግ ብቻ ሳይሆን እግዚ አብሔርን በመቃወም ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ የምናሳዝንበትም ነው /ኤፌ. 4+30/ ጻድቁ ዮሴፍ «እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአት እሠራለሁ?»ያለው ለዚህ ነው::/ዘፍ. 39+9/ ጻድቁ «በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት እንደሚያደርግ» «የእግዚአብሔርንም መንፈስ እንደሚያሳዝን» እርግጠኛ ስለሆነ ከኃጢአት ሸሸቷል::

በእርግጥ ሰው ኃጢአት ሲሠራ በእግዚአብሔር ፊት መሆኑን እና እግዚአብሔር እንደሚያየው ይረሳል:: ስለመልካም ነገር ዳዊት «እግዚአብሔርን በፊታቸው አላደረጉም» /መዝ. 53+3/ ብሏል:: ኃጢአት ሲያደርጉ ከአእምሮአቸው ውጭ ይሆናሉ:: በሌላ በኩል ጻድቁ ያለማቋረጥ በፊቱ አይቶታል ስለዚህ በፊቱ ኃጢአትን ላለማድረግ ተጠንቅቆአል:: ይህንን በተመለከተ ነቢዩ ኤልያስ የተናገረው ቃል እንዴት ጥልቅ ነው:: «በፊቱ የቆምሁት

የሠራዊት ጌታ ሕያው እግዚአብሔር...»1ነገ.ሥ. 18+15/

ኃጢአቱን በእግዚአብሔር ፊት በቀጥታ የሚናዘዝ ያለ እፍረት ለሠራቸው ኃጢአቶቹ ይቅርታን ያገኛል። ነገር ግን ስለሠራው ኃጢአት እፍረት ላይሰማው ይችላል። ስለዚህ ኃጢአቱን በካህኑ ፊት ቢናዘዝ የተሻለ ነው። በዚህ ምክንያትም እፍረት ሊሰማው እና ተጨማሪ ኃጢአት ላይሠራ ይችላል።

- **አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔርን በጎነት አላግባብ ስለሚ ጠቀሙበት የራሳቸውን በጎነት ያጣሉ።**

የእግዚአብሔር ትሕትና ከበጎነቱ እና ከቅድስናው እኛንም ወደ ቅድስና እና ጽድቅ ከሚጠራበት ጥሪው ጋር የተያያዘ ነው።

የሐዋርያውን ቃል ማስታወስ ይገባል«ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሓ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግስቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን? ነገርግን እንደጥንካሬህ ንስሓ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቁጣ ቀን ቁጣን በራስህ ታከማቻለህ።» /ሮሜ. 2+4-5/

እግዚአብሔር በፍቅሩ ወደ በጎነት ይመራል። እንዲሁም ወደ በጎነት ይመሩን ዘንድ ብዙ ስጦታዎችን ወይ የላቁ ኃይሎችን ሰጥቶናል። ከእነዚህ ስጦታዎች ወይስ ኃይሎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

እግዚአብሔር እኛን በአርአያውና በአምሳሉ በቅድስና እና በጎነት እንዲሁም በመረዳት በእውቀት እና በጥበብ ፈጥሮናል። «ይህንን መለኮታዊ አምሳል በኃጢአት በኩል



ባጣን ጊዜ «የማይታይ አምላክ ምሳሌ» /ቆላ. 1+15/ በሆነው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አካል ውስጥ ሰጠን። እውነተኛውን ምሳሌ ሰጥቶናልና «እርሱ እንደተመላለሰ ልንመላለስ ይገባናል።» /1ኛዮሐ. 2+6/

በርግጥ የሥራው ቃል ዋና ዓላማ የድኅነትን ሥራ መሥራት ነው። ነገር ግን መለኮታዊ አምሳልን ፍጹም ተስማሚ ምሳሌ አድርጎ መስጠት ተጨማሪ ዓላማው ነው።

- **ሰብዓዊ ተፈጥሮአችን በኃጢአት በተበከለ ጊዜ እንደገና የሚሻሻልበትን መንገድ በጥምቀት ሰጥቶናል**

በዚህ ጥምቀት አሮጌው ሰው ተሰቅሎአል፤ አዲሱ ሰውም በእግዚአብሔር አምሳል ተነሥቶአል፤እኛም በአዲስ ሕይወት እንመላለሳለን። ከመጠመቂያው ምንጭ ከውሃና ከመንፈስ የተወለደ አዲስ ሰው ይወጣል። ይህንን በተመለከተሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረው ቃል እንዴት ያማረ እና ጥልቅ ነው። «ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን»? /ሮሜ 6÷3−4።/

- **በበጎነት እንድንመላለስ የቅዱስ መንፈሱ ቤተ መቅደስ አደረገን**

መጽሐፍ ቅዱስ «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደመሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?» /1ቆሮ.3+16/ እንዳለ። በቅዱስ ሜሮን አማካኝነት የምንቀበለው ነው። በተመሳሳይ መልእክት ውስጥ ተመሳሳይ የሆነ ቃል በሐዋርያው ተደግሟል «ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው

የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና የራሳችሁ አይደላችሁም»/1ቆሮ. 6+19/ ባለ ጊዜ።

ይህ ቅዱስ መንፈስ በውስጥህ ስላለ ስለ ኃጢአትህ ይወቅስሀል ወደ እውነትም ሁሉ ይማራሃል።ሁሉን ያስተምርሃል ጌታ የነገረህን ሁሉ ያሳስብሃል /ዮሐ.16+8-13 14+26/በዚህ በጎ እንድትሠራ ይረዳሃል ወደ በጎነት ሕ ይወትም ያደርስሃል።

- እግዚአብሔር በጎ እንድንሠራ ይረዳን ዘንድ ጸጋውን ሰጥቶናል

ቤተ ክርስቲያን በዚህ ጸጋ እያንዳንዱን ሕብረት «የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን»/2ቆሮ. 13+14/ በሚል የማጠቃለያ ቡራኬ ታጠቃልላለች።

ብዙዎቹ የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት በዚህ የእግዚአብሔር ጸጋ እንደሚጀመሩ ወይም እንደሚፈጽሙ እንገነዘባለን። ለቆሮንቶስ በላካት የመጀመሪያይቱ መልእክት «ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን»በሚል ቃል ጀምሯልና። ይህቺን መልእክትም«የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን» በሚል ቃል አጠቃልሏል።/1ቆሮ.1+3፣16+23/ በሁሉም መልእክታት ውስጥ እንዲሁ አድርጓል።

ይህ ጸጋ የሚመራህ ወደራስህ በጎነት ብቻ ሳይሆን በአገልግሎት ውስጥ ሌሎችን ወደ በጎነት እንድትመራ ነው።



ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ነገር ግን በእግዚ አብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም ከሁላቸው ይልቅ ግን ደከምሁ ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም።» /1ቆሮ. 15+10/ ብሏል።

ታዲያ እነዚህን ሁሉ ኃይላት አትርሳ፤የበጎነት መንገድም አስቸጋሪ ነው አትበል። ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ መሆኑ /ማቴ.7+14/ ወደ እግዚአብሔር መንግሥትም በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ እንደሚያስፈልገን እውነት ነው/ሐዋ. 14+22/። ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋ ከእግዚ አብሔር ጋር ወዳለ ፍጹምነት ሕይወት የመውሰድ አቅም አለው። ይህ ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ካህናት የተናገረው ነው «አሁንም ለእግዚአብሔርና ያንጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ።» /ሐዋ 20÷32/

- ጌታ ክርስቶስ ራሱ ወደ እርሱ መንገድ እንድንጓዝ እኛን በመርዳት ከእኛ ጋር ነው

«እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ብሏል። እንዲሁም «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና»/ዮሐ15÷5/አለ። ስለዚህ በጎ ልትሆን የምትችልበትን ኃይል እንዲሰጥህ ጠይቀው። «መልሰኝ እኔም እመለሳለሁ» /ኤር31÷18/ በለው። «ለምኑ ይሰጣችኋል ፈልጉ ታገኙማላችሁ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችኋልም» /ማቴ 7÷7/ አላለምን?

- ወደ በጎነት እንዲመራን እግዚአብሔር ኀሊናን ሰጥቶናል

ኅሊና በእኛ ውስጥ ያለ የእግዚአብሔር ድምፅ ነው። ይፈርዳል፣ያዝዛል፣ይገሥጻል፣ይወቅሳል፣ወደ መልካም ይመራል፣ስሕተት ከመሥራትም ይጠብቃል።ኅሊናህ በውስጥህ ባለ ቅዱስ መንፈስ ከበራ ወደ በጎነት የሚመራ ጠንካራ መሪ በመንፈስ የተቀጣጠለ ሕሊናህን ብቻ የምትታዘዝ ከሆንህም ክፋት ከመሥራት ይከለክልሃል።

- **ለበጎ ነገር ሲል እግዚአብሔር ትእዛዛትን ሰጥቶናል**

ስለዚህም ነቢዩ ዳዊት «የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው ነፍስን ይመልሳል» «ሕፃናትን ጠቢባን ያደርጋል» «ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው»/መዝ18÷7-8 118÷105/። ስለዚህ በበጎ መንገድ በመራመድ ብርቱ የሆነ ይመራው ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል ይያዝ።ኢያሱ ወልደ ነዌ «ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቃናልሀል ይከናወንልሀልም።» /ኢያሱ1+8/ ሲል እንደተናገረ።

ዳግመኛም ሐዋርያው «የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።» /2ጢሞ 3+16-17/ ብሏል።

- **ለበጎ ነገር ሲል እግዚአብሔር ነቢያትን ካህናትን እና መሪዎችን ልኮልናል**

ሐዋርያትን ልኮልናል ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለው ስለ ክርስቶስ እንዲለምኑን የማስታረቅም አገልግሎት ሰጥቷቸዋል /2ቆሮ 5+18-20/ ለእኛም ለዋኖቻችሁ ታዘዙና



ተገዙ...ስለ ነፍሳችሁ ያተጋሉና /ዕብ. 13+17/ እንዲሁም ወደ በጎነት እንዲመሩን መንፈሳዊ አባቶችን እና ካህናትን ሰጥቶናል።

- **በጎነትን በትዕግሥት እንድንጠባበቅ ያግሩ ቃልኪዳኖችን ሰጥቶናል**

«ድል ለነሳው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ» «አዲስ ስም እሰጠዋለሁ» «በነጭ ልብስ ይጎናጸፋል» «እኔ ደግሞ ድል እንደነሣሁ ከአባቴ ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ» /ራዕ. 2+3/ በተጨማሪም ዓይን ያላየውን ጆሮም ያልሰማውን በሰውም ልብ ያልታሰበውን እግዚአብሔር ለሚወደን ለእኛ ያዘጋጀውን ነገር ሊሰጠን ቃል ገብቶልናል /1ቆሮ. 2÷9/

- **ቀደም ብሎ የተገለጸው ሁሉ እኛን በማይጠቅምበት ሁኔታ ውስጥ ሲሆን ደግሞ ቅጣትን አዘጋጅቶልናል**

«የጥበብ መጀመሪያው እግዚአብሔርን መፍራት ነው።» /ምሳ. 9+10/ ተብሎ እንደተጻፈ አንዳንድ ሰዎች ቢያንስ በነገር መጀመሪያ ላይ ባለ ፍርሃት ወደ በጎነት ይመራሉና። ሐዋርያውም «አንዳንዶች ተከራካሪዎችንም ውቀሱ አንዳንዶችንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ አንዳንዶችንም በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳ እየጠላችሁ በፍርሃት ማሩ።» /ይሁ 22-23/ ብሏል።

ቅጣት ከፍጥረት መጀመሪያ ከአዳምና ከሔዋን ኃጢአት ጀምሮ ነው የተዘጋጀው /ዘፍ. 3/በብሉይ ኪዳን ውስጥ ብዙ የቅጣት ምሳሌዎች አሉ። በአዲስ ኪዳንም እንዲሁ

የሐናንያን እና የሰጲራን ቅጣት እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ይህንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት እንዴት እንደሆነ እናነባለን።/ሐዋ. 5+11/ሌላው የአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለ የቅጣት ምሳሌ ለበቀል ሳይሆን መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው ተብሎ በጳውሎስ የተገደደው ቆሮንቶሳዊው ኃጢአተኛ ነው። /1ቆሮ. 5÷5/

- እኛ በኃጢአት ሳለን ፈጥኖ ያልወሰደንን እግዚአብሔርን አመስግነው

ወደ ንስሐ እንድንመለስ ዕድልን በመስጠት እና ኩነኔ እንዳይኖርብን በማድረግ መሥራት ወዳለብን መልካም ሕ ይወት ሊመራን እስከአሁኗ ቅጽበት ድረስ እንድንኖር ፈቅዶልናል። ሐዋርያው «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ ለማይመላለሱት አሁን ኩነኔ የለባቸውም»/ሮሜ.8+1/ ብሏልና።በእርግጥ እንደመንፈስ ፈቃድ መመላለስ በጎነት ሲሆን እንደሥጋ ፈቃድ መመላለስ ግን ውድቀት ነው። ሐ ዋርያው ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘለዓለምን ሕይወት ያጭዳል»/ገላ. 6+7-8/ ያለው ለዚህ ነው።

ታዲያ ይህ የመንፈስ ፍሬ ነው በጎነት በዚህ ዓለም ውስጥ እና በሌላኛው ዓለም በዚያ በዘለዓለማዊው ሕይወት ውስጥ አለ። በሰማያዊው መንግሥት በጎ የሆነ እንጂ ሌላ የሚገባ የለም። በሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ርኩሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም። /ራዕ 21÷27/



# ምዕራፍ ሰባት

# እምነት

መንፈሳዊ ሕይወት የሚመራ ሰው እምነት አለው ምክንያቱም ቅዱስ መጽሐፍ ያንን እምነት ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ /ገላ 5+23/ እና ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ ይለዋል። /1ቆሮ 12÷9/

እዚህ ላይ እምነት ማለት ውጪያዊ ወይም በተግባር ያልታየ እምነትን ማለት አይደለም ወደ መላ ሕይወት የሚሰራጨውን መንፈሳዊ እምነት ማለታችን ነው። ከዲያብሎስ ጋር የሚመሳሰል በተግባር ያልታየ ያልተፈተነ ሳይሆን የተግባር እምነት ነው። ሐዋርያት «እግዚአብሔር አንድ እንዲሆን አንተ ታምናለህ መልካም ታደርጋለህ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀ ጡማል።» /ያዕ 2+19/ ብሏልና አጋንንት ያምናሉ ነገር ግን ይቃወሙታል ስለዚህም ይንቀጠቀጣሉ ።

በመሠረተ እምነት ማመንእና በተግባር ማመን አለ

አንዳንዶች በእውነተኛ ሕይወታቸው ከእምነት እጅግ ርቀው ሳሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመመላለሳቸው ምክንያት ራሳቸውን አማኞች አድርገው ሊያስቡ ይችላሉ። ነገር ግን እውነተኛ እምነት በተግባራዊ ሕይወታችን በሥራዎቻችን እና ከእግዚአብሔር እና ከሰዎች ጋር በምናደርገው ግንኙነት በግልጽ የሚታይ ነው።

- ተግባራዊ እምነት

በአንድ ሰው ሥራዎች ውስጥ የሚገለጸው ነው። ስለዚህ

መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር «እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ» ይላል ይህንን እውነትም «ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው።» /ያዕ 2÷18 17-20/ ሲል ያስረግጣል።

ሕይወት ያለው እና ፍሬያማ እምነት ብቻ የተባረከ ነው። እምነትህ ሕይወት ካለው ፍሬው በሕይወትህ ይገለጣል ምክንያቱም «መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል።»/ሉቃ3÷9/ሐዋርያውም «...በፍቅር ሆኖ የሚሠራ እምነት እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምም።» /ገላ 5÷6/ ብሏል። በእርግጥ ፍቅር በ /1ቆሮ 13/ እንደተገለጸው ብዙ ምግባራትን የሚያጠቃልል ከፍተኛ መንፈሳዊ እቅድ ነው።

- የእምነትና ፍሬው በሕይወታችን ሊገለጽ የሚችለው እንዴት ነው ?

ይህ ሙሉውን የሕይወታችን ዝርዝር ጉዳዩን የሚሸፍን ረዥም ታሪክ ነው። ይህንንም ከስሜቶቻችን ወይም ከእግዚአብሔር እና ከሰዎች ጋር ካለን ግንኙነት ጋር በማጣመር በምሳሌዎች እናብራራ።

እግዚአብሔር በሙሉ ቦታ መኖሩን እና እንደሚያይህ እንደሚሰማህም በትክክል ካመንህ ፈጽመህ ኃጢአት አትሠራም።

እግዚአብሔር ኃጢአት ውስጥ ሳለህ ሲመለከትህ ሀፍረት ይሰማሃል። ዳግመኛም መላእክትና የቅዱሳን መንፈስ ኃጢአት ስትሠራ ይመለከቱሃልና ኃፍረት ይሰማሃል።

በምድር ላይ ባሉ ሰዎች ፊት ኃጢአት መሥራትንም



ታፈራለህ። ስለዚህ በዚህ የማታፍር ከሆንህ በእግዚአብሔር ሕልውና እና አንተን በማየቱ ላይ ያለህ እምነት ደካማ ነው እምነቱ ላይኖርም እንኳን ይችላል። ጻድቅ ዮሴፍ ኃጢአትን እንዴት እንደተቃወመ ተመልከት «እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? /ዘፍ 39+9/

በእግዚአብሔር በጥበቃው እና በኃይሉ በትክክል የምታምን ከሆነ አትፈራም። ፍርሃትህ የደካማ እምነት ማስረጃ ነውና። ሐዋርያው ጴጥሮስ ማዕበሉን በፈራበት ጊዜ መስጠም ጀመረ ስለዚህ ጌታ «አንተ እምነት የጎደለህ ስለምን ተጠራጠርህ?» /ማቴ 14÷31/ አለው።

በመጽሐፍ እንደተጻፈልን ግያዝ ከተማውን ከብቦ የነበረውን የጠላት ሠራዊት ፈርቶ እንደነበር እናነባለን። ነገር ግን ነቢዩ ኤልሳዕ የእግዚአብሔር ሠራዊት ሲያሸንፋቸው አየ። ስለዚህ ያይ ዘንድ ዓይኖቹን እንዲገልጥለት ለግያዝ ጸለየለት /2ነገ.ሥ 6+17/ አዎ በስብዓዊ ዓይኖቹ ሳይሆን በእምነት ማየት ይችላል ከእርሱ ጋር ያሉትም ከጠላት ጋር ካሉት እንደሚበልጡም ማየት ይችላል።

በዚህ ፍርሃት አልባ እምነት ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ /መዝ 22/ «በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም።» ብሏል። በሌላኛው መዝሙሩም «ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በፊቴ አየዋለሁ በቀኜ ነውና አልታወክም።» ብሏል /መዝ 15+8/

ጌታ ከአንተ ጋር እንደሆነ በእርግጥ ብታምን አትፈራም እርሱ ሁልጊዜ በፊትህ እና በቀኝህ እንደሆነ ካመንህ አትታወክም ከመዝሙረኛው ጋር «ሠራዊትም ቢሰፍርብኝ

ልቤ አይፈራም ሰልፍም ቢነሳብኝ በዚህ እተማመናለሁ» /መዝ 26+3/ ትላለህ::

ብዙዎቹ እምነት በማጣታቸው መፍራት ብቻ ሳይሆን ከመጨነቃቸው የተነሳ በተስፋ መቁረጥም እንኳን ይወድቃሉ::

በውስጡ ባለው እግዚአብሔር ኃይል የሚያምን ሁሉ «ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል /ማር 9+23/ የሚለወን የወንጌል ቃል ያምናል::

ይህ ቃል እንዴት የሚያስደስት እና የሚያጽናና ነው፤ እግዚአብሔር ሁሉን ያደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆነ አሳቡም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል እናምናለን /ኢዮ42÷3/

ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል የሚለው ቃል ግን አስደናቂ እና ከፍተኛ የሆነ ነገር ነው:: ይህም ስለ ኃይል እና ስለ እምነት ፍቱንነት አሳብ ይሰጠናል:: ይህ «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ» /ፊል 4+13/ የሚለውን የሐዋርያውን የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ያስታውሰናል::

እምነት ኃይል እስከሆነ ድረስ ሁልጊዜ ለሰው ኃይልን ይሰጣል በዚህም ምክንያት ሳይፈራ ሳይጨነቅ ወይም በተስፋ መቁረጥ ሳይወድቅ ይችላል:: የዚህ ኃይል ምንጭ ለሰውየው ይህን ኃይል የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው:: ስለዚህም መዝሙረኛው «ኃይሌም ዝማሬዬም እግዚ አብሔር ነው እርሱም መድኃኒት ሆነልኝ::» /መዝ 117÷14/ አለ::

- ሰላም እምነትን ይከተላል ውስጣዊ ሰላምን ወይም ከእግዚ አብሔር ጋር ያለ ሰላምን ይይዛል

ሐዋርያው «እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር



ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ» /ሮሜ 5+1/ እንዳለው:: ጌታ ኃጢአቶቻችን ሁሉ እስከ መስቀል ድረስ በራሱ ላይ እንደተሸከመልን እናምናለንና ይህ ሰላም አለን እንዲሁም «በደሙ ከጸደቅን...በልጁ ሞት ከታረቅን በሕይወቱ እንድናለን» /ሮሜ. 5+9-10/ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር::» /1ቆሮ. 5+19/ ብለን እናምናለን::

- በእምነት እና ሰላም እንደሰታለን

አማኞች ሁልጊዜ ደስተኞች ናቸው:: እግዚአብሔር እንደሚጠብቃቸው እምነት ስላላቸው ይደሰታሉ ፍጹም ኃያል እና ርኅሩኅ አባት እንደሆነም ያምናሉ:: የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣቸዋል በንስሓቸው ይቅር ይላቸዋል፤እነርሱን በማዳንም ችሎታ ያለው ነው ያድናቸዋጠ ልም::

በችግራቸው የተጨነቁ ቢመስሉም እንኳን ከሐዋርያው ጋር «ኃዘንተኞች ስንሆን ዘወትር ደስ ይለናል::»/2ቆሮ6÷10/ ይላሉ ስለዚህ ሐዋርያው ለሚያምኑ «ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ::» /ፊል4÷4/ ብሏቸዋል:: የመንፈስ ፍሬዎች ውህደት እንዳላቸው ግልጽ አይደለምን? ማለትም ደስታ፣ ሰላም፣ እምነት....::

- የሚያምን መጠራጠር የለበትም

እምነት የጥርጣሬ ተጻራሪ ነው ስለዚህ የሚያምን መጠ ራጠር የለበትም:: ጥርጣሬ የእምነትን ደካማነትን ይገልጻል ጌታ «አንተ እምነት የጎደለህ ስለምን ተጠራጠርህ» /ማቴ

14÷31/ እንዳለው ግንኙነት አላቸው።

በእምነት ደካማነት ምክንያት በተደጋጋሚ ብዙዎቹ በጥርጣሬ ውስጥ ይወድቃሉ! ይጸልያሉ ነገር ግን እግዚ. አብሔር አይመልስልንም ወይም ለመመለስ ይዘገያል ብለው ያስባሉ ስለዚህም ይጠራጠራሉ። አንዳንድ ችግሮች አንዳንድ በሽታዎች ወይም አደጋዎች ሲደርሱባቸው ወይም የሚወዱት ሰው ሲሞት የእግዚአብሔርን ፍቅር እና ምሕ ረት ይጠራጠራሉ። አንድ ሰው በእምነት ደካማ ሆኖ ሳለ እምነትን የሚጻረሩ መጻሕፍትን በማንበቡ ምክንያት መሠረተ እምነትን በተመለከተ ጥርጣሬ ውስጥ ሊወድቅ ይችላል።

- **እውነተኛ እምነት ጽኑና ሊናወጥ የማይችል ነው**

እውነተኛ እምነት ሁልጊዜ እና በሁሉም ጊዜያት በማንኛውም ሁኔታዎች መከራ ወይም ችግር ሥር ይኖራ ል። ሐዋርያው ምን እንዳለ ተመልከት «ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ የማትነቃነቁ የጌታም ሥራ ሁልጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ።» /1ቆሮ 15÷58/ እነዚህን ቃላት እናስታውስ ሁልጊዜም በፊታችን እናስቀምጣቸው።

- **በእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን በእኛ ውስጥ እና ከእኛ ጋር በሚሠራው ሥራም እንመን**

እግዚአብሔር ሁልጊዜ እንደሚሠራ እንመን ለየብቻችንም ሆነ በኅብረት ከቤተ ክርስቲያን ጋር ከማኅበረሰብ ጋር እና ከመላዓለም ጋር ለእኛ ጥቅም ከእኛ ጋር እንደሚሠራ እንመን በዚህ መንገድ በክስተቶች ሁሉ



የእግዚአብሔር እጅ እንዳለበት እርግጠኞች መሆን አለብን «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።»/ሮሜ8÷28/እርግጠ ኞች እንሆናለን። እንደዚህ አይነት እምነት ሰላምና ጽናት ይሰጠናል።

## የእምነት ደረጃዎች

በሁሉም ሰዎች ዘንድ ወይም በአንድ ሰው የሕይወቱ የተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ እምነት አንድ ዓይነት ደረጃ የለውም። ለአንድ ሰው በተወሰነ ጊዜ እምነት ጠንካራ በሌላ ጊዜም ደካማ ሊሆን ይችላል። በተመሳሳይ መልኩ የጀማሪ ሰው እምነት የተለየ ነው። መንፈስ ያደረበትን ብላቴና አባት ጌታ በጠየቀው ጊዜ የብላቴናው አባት ጮኾ «አምናለሁ አለማመኔን እርዳው።» /ማር. 9÷24/ አለው ተአምራትን የሚያደርግ የጠንካራ እምነት አይነት እና የፍ ጹም እምነት ዓይነት አለ። ስለዚህ ሐዋርያው «ተራሮችን እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ» /1ቆሮ 13÷2/ አለ።

እንደማንኛውም ምግባር እምነት ሊጨምርና ጥንካሬው ሊያድግ ይችላል። ሐዋርያው ጴጥሮስ ክርስቶስ በተያዘ ጊዜ በአንዲት ገረድ ፊት እምነቱ ደካማ ነበር። / ማቴ 26÷70/ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ከተቀበለ በኋላ እምነቱ ጠንካራ ሆነ በዚህም ምክንያት «ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል» /ሐዋ 5÷29/ አለ።

ሐዋርያውም እምነትን «ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።»/ዕብ 11÷1/ በማለት ገልጾታል።

በእምነትና በሚታዩ ነገሮች መካከል ልዩነት አለ። እግዚአብሔር የማይታይ ቢሆንም እግዚአብሔር እንዳለ እናምናለን በተመሳሳይ መልኩ መላእክትንና መናፍስትን ባይኖቻችን ባናያቸው እንዳሉ እናምናለን። ዳግመኛም በሚሥጢራት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምንቀበላቸውን የማይታዩ ስጦታዎችን እናምናለን የሆነ ሆኖ በእነዚህ ነገሮች እርግጠኞች ነን።

ይሁንና እምነትን ራሱን የሚገልጹና የሚያረጋግጡ የተወሰኑ ምልክቶች አሉ። አንድ አማኝ እግዚአብሔር እንዳለና እንደሚኖር የሚያምን፤ ማንም ሰው በእግዚአብሔር ፊት ትቢያና አመድ እንደሆነ የሚያውቅ እንጂ፤ በእግዚ አብሔር ፊት በትዕቢት መናገር የማይቻል በመሆኑ ምክንያት ሊታበይ ወይም እብሪተኛ ሊሆን አይገባውም። /ዘፍ 18÷2/

አንድ ምዕመን በፍርሃት ለጸሎት የሚቆመው ለዚያ ነው። በጸሎት ውስጥ ቅዱሳን «በጸሎት ውስጥ ያለ መልካም አቀራረብ» ብለው የሚጠሩት ሥርዓት አለ፤ እርሱም መስገድን እና የመሳሰሉትን ማለታቸው ነው። አንድ ሰው በእሳት ዓምድ ፊት እንደቆመ አድርጎ ለጸሎት ይቆማል፤ ስለዚህ በቅዳሴ ጊዜ «በእግዚአብሔር ፊት በፍርሃት ቁሙ ቅዱስ ወንጌልንም ስሙ» «እግዚአብሔርን በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ አምልኩት።» እንላለን።

በሌላ በኩል በጸሎት ጊዜ ችላ ብሎ የሚቆም ዙሪያ ገባውን የሚመለከት ወይም በተለያዩ ነገሮች ትኩረቱ የሚሳብ በእግዚአብሔር ፊት እንደሚቆም አለማመኑን ያሳያል።



በእምነት በሚደረግ ጸሎትና ያለ እምነት በሚደረግ ጸሎት መካከል ልዩነት አለ አንድ ምዕመን ጸሎቱ እግዚ አብሔር ዘንድ እንደሚደርስ፣ እግዚአብሔር እንደሚሰማው መልስም እንደሚሰጠው ያምናል። እግዚአብሔር እንደሚሠ ራ እርግጠኛ ነው።

ከዳዊት መዝሙራት መካከል አንዳንዶቹ በጥያቄ የሚጀምሩት እና በመልስ የሚያጠቃልሉት ለዚህ ነው። ለምሳሌ መዝሙር «ዓመጽን የምታደርጉ ሁሉ ከእኔ እራቁ እግዚአብሔር የልቅሶዬን ቃል ሰምቶአልና። እግዚአብሔር ልመናዬን ሰማኝ...» /መዝ 6÷8/ በሚል ቃል ያጠቃልላል።

ከእምነት ምልክቶች ውስጥ ልንገልጸው የምንፈልገው ሌላው ነጥብ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ...።» /ዮሐ 14÷6/ በሚለው ቃል መሠረት እውነት በሆነው በእግዚአብሔር ታምናለህ? «በእውነት» የምታምን ከሆነ ስለእውነት ትናገራለህ ስለ እርሷስ ትመሰክራለህ?

ከእውነት መራቅ ከእግዚአብሔር መራቅ በመሆኑ በሐሰት መመስከር የእምነት መድከም መገለጫ ነው። በተመሳሳይ መንገድ እግዚአብሔር ብርሃን እንደሆነ ካመንህ /ዮሐ 8÷13/ በብርሃን ታምናለህ በእርሷስ ትመላለሳለህ ወይስ በጨለማ ትመላለሳለህ? በብርሃን ስታምን እንዴትስ በጨለማ ልትመላለስ ትችላለህ? ጌታ «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም።» /ዮሐ 8÷12/ ብሎ አልተናገረምን?

በተጨማሪም በዘለዓለማዊ ሕይወት ካመንህ ለእርሱ የተዘጋጀህ መሆን አለብህ። አንድ ሰው ለዚህ እስከተዘጋጀ ድረስ ከዚህ ዓለም ምንም ነገር አይመኝም መጽሐፍ ቅዱስ

«ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል ነው» /ያዕ 4÷4/ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም:: /1ኛ ዮሐ 2÷15/ ብሏልና ስለዚህ ማንም በዓለም ፍቅርና ምኞት የሚመላለስ ራሱን የሚቃወም እንጂ እውነተኛ አማኝ አይደለም::

ሥጋህ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆነ ካመንህ ልታፈርሰው ትችላለህን? ሐዋርያው«የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲ ኖረባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል:: የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ::» /1ቆሮ 3÷16-17/ አለ::

ዳግመኛም «ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና የራ ሳችሁ አይደላችሁም::» /1ቆሮ 6÷19/ አለ::

ስለዚህ ማንም ሥጋውን የሚያፈርስ ሥጋው የእግዚ አብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆነ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደኖረበት አያምንም የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ማደሪያ የሆነችውን ሴት ሥጋ የሚያፈርስ ሰውም እንዲሁ ነው::

ከዚህ በኋላ እምነት መላ ሕይወትን ጨምሮ ጥልቅና ሰፊ ጥቅም እንዳለው እናያለን:: ስለዚህ ሐዋርያው «በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ ራሳችሁን ፈትኑ::»እንዳለን:: /2ቆሮ. 13÷5/ መከራዎች የአንድ ሰው እምነት መፈተኛ መንገዶች ናቸው የአንዳንድ ሰዎች



እምነት በመከራዎች ምክንያት ይደከማል ወይም ይጠፋልና:: ሌሎች ሁሉም የሥቃይ፣ የጉዳት እና የዛቻ ዓይነቶች ቢደርሱባቸውም ጽኑ ሆነው እንደቀጠሉት ቅዱሳን ሰማዕታት መከራ ቢፈራረቅባቸውም በእምነት ጽኑ ሆነው ይቀጥላሉ::

- **ጥርጣሬዎችም የእምነት መፈተኛ ዘዴዎች ናቸው::**

እግሮቻቸው ወደ ቀይ ባሕር በመጨመር የተሻገሩት በሁለቱ አቅጣጫ በዙሪያቸው ውሃና ማዕበል ቢኖርም ሙሉ በሙሉ ጥርጣሬ አልነበራቸውም::

ጠንካራ እምነት እርሱን የሚዋጋውን ጥርጣሬን ድል ያደርገዋል፣ በአራተኛውና በአምስተኛው ክፍለ ዘመን የተሰራጨውን የመናፍቃን ኃይል ቤተ ክርስቲያን በኃይሏ መቋቋም የቻለችው ለዚህ ነው:: ቤተ ክርስቲያን ኑፋቄን አውግዛለች እምነቷ እንዲታወቅም አውጃለች::

እምነትን በመጻረር የሚያጠቁንን በውጊያዎች ሁሉ ድል ማድረግ እንችል ዘንድ በእምነታችን እንድንጸና እና በመንፈስ እንድንጠነክር እግዚአብሔር ይጠብቀን::

# ምዕራፍ ስምንት
# የዋሃት

የውሃት የመንፈስ ፍሬ ነው። /ገላ5÷23/ ጌታ ስለተባረኩት ከተናገራቸው ዓረፍተ ነገር ግንባር ቀደም መሆኑን /ማቴ5÷5/ «የዋሆች ብፁዓን ናቸው ምድርን ይወርሳሉና።» በማለት ገልጿል።

አንዳንድ ቅዱሳን አባቶች «ምድርን ይወርሳሉ» የሚለውን ቃል የዳዊት መዝሙር «የእግዚአብሔርን ቸርነት በሕያዋን ምድር አይ ዘንድ አምናለሁ።» /መዝ 26÷13/ ሲል በሕያዋን ምድር አይ ዘንድ አምናለሁ።» /መዝ 26÷13/ ሲል የተናገረውን የሕያዋንን ምድር እንደሚጠቁም አድርገው ይተረጉሙታል።ነገር ግን የምንኖርባት ምድርም ልትጨመር ትችላለች የዋሆች በዚህ ምድር ላይም በሁሉም ሰው ዘወትር ይወደዳሉና። ይቺን ምድር ድል ያደርጋል የሕያዋንን ምድርም እንዲሁ።

የውሃት ወይም ደግነት ጌታ ከእርሱ እንማረው ዘንድ የጠየቀን እጅግ ጠቃሚ ምግባር ነው። «ከእኔ ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና» /ማቴ 11÷29/ ብሏልና።

ከእርሱ ስብከትን መምህርነትን አገልግሎትን ፍቅርን ምሕረትን ጥበብን እና ሌሎች ምግባራትን እና ፍጹምነትን ሁሉ እንድንማር ጠይቆናል ፍጹምነትን እና ምግባርን ሁሉ ይወክላልና ነገር ግን በየውሃት እና ቸርነት ላይ ትኩረት ያደርጋል። ይህንን ለሚማሩትም «ለነፍሳችሁ እረፍት ታገኛላችሁ» ብሏቸዋል።

ከየውሃት ጥቅም የተነሳ ቤተ ክርስቲያን የውሃትን



ከጥዋት ጸሎታት መጀመሪያ ላይ አስቀምጣዋለች። ከመዝሙረ ዳዊት በፊት በጥዋት ጸሎት መግቢያ ውስጥ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን በላከው መልእክቱ አንድ ክፍል ውስጥ «እንግዲህ በጌታ እስር የሆንሁ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ በትሕትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም እርስበርሳችሁ በፍቅር ታገሡ....» /ኤፌ 4÷1-2/ የሚለውን እናስታውሳለን። ታዲያ የዋህነት በክርስቲያናዊ መንፈሳዊ ጠባይ ውስጥ ግንባር ቀደም ራስን ዝቅ ከማድረግ እና ከትሕትና ጋርም የተያያዘ ነው።

አባቶች ሐዋርያት በንግግራቸው ውስጥ ስለየዋህነት በተደጋጋሚ ተናግረዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ወንድሞች ሆይ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ። /ገላ 6÷1/ አለ።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም «ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማን ነው? በመልካም አንዋዋሩ ሥራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ።» /ያዕ 3÷13/ አለ። እናም ታዲያ እንዲህ ዓይነት የዋህነት ከመራራ ምቀኝነት ለራስ ከመፈለግ ግራ ከመጋባት እና ከማንኛውም ክፉ ነገር እንዴት የነፃ እንደሆነ አብራርቶአል። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ ስለከበረው የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ውበት ተናግሯል /1ጴጥ3÷4/ ዳግመኛም «በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን /1ጴጥ 3÷15/ አለ።

• የዋህነት ክርስቲያኖች የሚለይበት ጠባይ ነው

ይህ አንድ እምነት የሌለው ጓደኛውን ባገኘው እርሱንም የዋህ እና ደስተኛ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ዛሬ በመንገድ አንድ ክርስቲያን አግኝተሃል? ባለበት በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውስጥ ከነበረው ከሐዋርያት ዘመን ጋር ግንኙነት አለው:: ይህ ማለት ሁልጊዜ የዋህ ከሆነ ክርስቲያን ጋር መገናኘት የራሱ የሆነ ተጽዕኖ እርሱን በሚገናኙት ሰዎች ገጽታ ላይም የዋህነትን ያንጸባርቃል::

ከቸርነት ወይም ከየዋህነት ጥቅም የተነሳ መጽሐፍ ቅዱስ ገር እና የዋህ የሆነ ሰውን ያመሰግናል ሁለቱም ምግባራት እርስበርሳቸው ግንኙነት አላቸውና:: መዝሙረኛው «ገሮችም ሰምተው ደስ ይላቸዋል» /መዝ 34÷2/ «ገሮች ግን ምድርን ይወርሳሉ በብዙም ሰላም ደስ ይላቸዋል» /መዝ 36÷11/ «እግዚአብሔር የዋሀንን ያነሳል ኃጢአተኞችን ግን እስከ ምድር ድረስ ያዋርዳል::» «መዝ 146÷6/ «ገሮችን በፍርድ ይመራል ለገሮችም መንገድን ያስተምራቸዋል::»/መዝ 24÷9/ አለ::

አሁን ስለ የዋህነት እና ስለየዋህ ይህን ሁሉ ካወቅን የዋህነት ምንድር ነው? የዋህ ወይም የገር ሰው ባህርያት ምንድር ናቸው? የሚሉትን እንመልከት::

## የየዋህ ሰው ጠባይ

• **የዋህ ሰው መልካም ጠባይ ያለው እና ሰላማዊ ሰው ነው:: እርሱ ሁልጊዜ የተረጋጋ ነው::**

በጠባዩ የረጋ ነው ኑሮቹ ንግግሮቹ ስሜቶቹ እና እንቅስቃሴዎቹም ሰላማዊ ናቸው:: ውጫዊ ገጽታው ብቻ



ሳይሆን ውስጣዊ እሱነቱም እርጋታ የተሞላበት ነው:: ልቡና ስሜቶቹ የረጉ ናቸው::ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚያደርጋቸው ውይይቶች እና ንግግሮች የረጋ ነው:: ጻግመኛም «ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበር::» /ዘኁ 12÷3/ ተብሎ እንደተገለጸው እንደ ነቢዩ ሙሴ ትሑት ነው::

• የ የዋህ ሰው ድምጽ ሁልጊዜ የዋህ ነው

ድምጹ ፈጽሞ ከፍተኛና ኃይለኛ አይደለም:: ንግግሮቹ ኀጂም አስቸጋሪም አይደሉም የረጋ እና አነስተኛድም ጽ የየዋህ ሰው ጠባይ ነው:: ይህም የየዋሁ ጌታችንን ድምጽ የሚመስል ነው:: እግዚአብሔር ነቢዩ ኤልያስን ከአጭበርባሪዋ ከንግሥት ኤልዛቤል ሲሸሽ ባገኘው ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ትልቅና ብርቱ ነፋስ ነፈሰ እግዚ አብሔር ግን በነፋሱ ውስጥ አልነበረም:: ከነፍሱም በኋላ በምድር መናወጥ ሆነ እግዚአብሔር ግን በምድር መናወጥ ውስጥ አልነበረም:: ከምድር መናወጥ በኋላም እሳት ሆነ እግዚአብሔር ግን በእሳቱ ውስጥ አልነበረም:: ከእሳቱም በኋላ ትንሽ የዝምታ ድምፅ ሆነ ድምፁም «ኤልያስ ሆይ በዚህ ምን ታደርጋለህ?» የሚል የእግዚአብሔር ድምፅ ነበር:: /1ኛ ነገ 19÷11-13/

ጌታ ክርስቶስ በየዋህነቱ «አይከራከርም አይጮህምም ድምጽንም በአደባባይ የሚሰማ የለም::...የተቀጠቀጠን ሸንበቆ አይሰብርም የሚጤስንም የጥዋፍ ክርም አያጠፋም::» /ማቴ12÷19-20/ በሚል ቃላት የገለጸው ለዚህ ነው::

የየዋህ ሰው ችሎታዎች ተብለው የሚገለጹ አሉ:: የዋህ ሰው ሁከት አይፈጥርም፣ አይከራከርም፣አይጮህምም

ድምፁንም በአደባባይ አያሰማም። ንግግሮቹ ርጋታ ያላቸውና የዋህን ናቸው። ቃላቱ እጅግ ትሑት እና ጥሩ እንደሆኑ ይመረጣል። የአንድ ሰው ጠባይ ምንም ይሁን ምን የማንንም ስሜቶች ፍጹም አይጎዳም። ይህን ሁሉ የሚያደርገው ደካማ ከመሆኑ የተነœ ሳይሆን ከየዋህነቱ የተነሳ ነው።

- **የዋህ በስሜቱ ኃይልና ቁጣ የለበትም።**

እርሱ የረጋና ተቃውሞ የማያስነœ ወይም የማይቀሰቅስ ነው።ፍጹም ንዴት አያገኘውም። በስሜትም በስሜታዊነትም አይነሳሳም። ነገሮችንም አይጋፈጥም። ስሜቶቹ ሁልጊዜ ሰላማዊ ናቸው የፊት ገጽታዎቹም መልካም ባህርይ እና ደስታ የተላበሱ ናቸው። ራሱን አይበቀልም፤ ችግሮቹንም በኃይል አይፈታም። ማንም ቢያስከፋውም በትዕግሥትና በ ጽናት ይጋፈጣል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥቃዩና ወደ ስቅለት በተጓዘበት መንገድ «ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ» እንዴት እንደነበረ ተመልከት። አፉንም አልከፈተም /ኢሳ 53/ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለራሱ እና ተከታዮቹ ስለነበሩት አገልጋዮች «ሲሰድቡን እንመርቃለን፤ ሲያሳድዱን እንታገœለን፤ ክፉ ሲናገሩን እንማልዳለን።» /1ቆሮ 4÷12-13/ ይላል።

- **የዋህ ራሱን እንደታዛቢ አድርጎ በሌሎች ላይ አያስቀምጥም።**

ራሱን እንደ ዳኛ በሌሎች ዘንድም ጣልቃ እንደሚገባ



አድርጎ አያስቀምጥም። ሌሎችን ለመታዘብ እና በሥራቸው ላይ ለመፍረድ ለራሱ ሥልጣን አይሰጥም። ማንንም አይኮንንም። ይፈርድ ዘንድ ከተገደደም ፍርዱ የጭካኔ አይሆንም።

- **የዋህ ሁልጊዜ ዓይን አፋር ነው ማንንም ፊቱን ሞልቶ ፊት ለፊት አይመለከትም።**

የአንድን ሰው ውስጣዊ ስሜቶች ወይም የቃላቱን እውነትነት ለማወቅ የፊቱን ገጾች አይመረምርም። ከዚህ ጋር ግብ ግብ ከገጠመ ለራሱ ይህ ከእኔ ጉዳይ አይደለም። የራሴን ጉዳይ ላስብ ይላል። በተፈጥሮው የዋህ ሌሎችን ድርጊት ለመመርመር ዝንባሌ የሌለው ነው።

- **አንድን ነገር ለማስተካከል ጣልቃ ከገባ በእርጋታ በቅንነት እና በየዋህነት ያደርጋል።**

ሐዋርያው «መንፈሳዊያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት» /ገላ 6÷1/ እንዳለ። አምላካችን ክርስቶስ ለሳምራዊቷ ሴት በየዋህነቱ እንዲሁ አደረገላት /ዮሐ 4/

በአንዲት ቃል እንኳን ስሜቶቿን አልጎዳም። በቅንነት እና በየዋህነት ወደ ንስሐ መራት እንጂ አልወቀሳትም። እርሷን ለማመስገን የሚያበቃ መልካም ነገርም አገኘባት «ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ… በዚህስ እውነት ተናገርሽ» /ዮሐ 4÷17-18/ በዚህ የዋህነት ወደ ንስሓ ወደ ማመን እና በከተማዋ ላሉ ሰዎች ስለ ክርስቶስ ወደ መመስከር ሊመራት ችሏል /ዮሐ 4÷29/

በኃጢአት ወድቃ ለነበረችው ሴትም እንዲሁ

አደረገባት:: ይወግሩአት ዘንድ ከፊጉአት እጆች አዳናት እንጂ አልወቀሳትም:: ከሳሾቿም በሄዱ ጊዜ «አንቺ ሴት እነዚያ ከሳሾችሽ ወዴት አሉ? የፈረደብሽ የለምን?... እኔም አልፈርድብሽም ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ» /ዮሐ 8÷10-11/ አላት:: በተመሳሳይ የዋህነት ከትንሣኤ በኋላ ደቀመዝሙሩን ቅዱስ ጴጥሮስን ምንም እንኳን ጌታን ፣ስት ጊዜ ቢክደው፣ እርሱን እንደማያውቀው ቢምልም /ማቴ26÷74/ ጌታ ፣ስት ጊዜ «ትወደኛለህ?» ብሎታል:: ዳግመኛም ሦስት ጊዜ «ግልገሎቼን አሠማራ... ጠቦቶቼን ጠብቅ... በጎቼን አሰማራ»/ዮሐ 21÷15-17/ በማለት አገልግሎቱን ነግሮታል::

በዚህ የዋህነት ኒቆዲሞስን በምሽት ተገናኘው:: በጨለማ በመምጣቱ በዚህም ምክንያት አይሁዳውያን ስለ ነገሩ ባለማወቃቸው እንጂ አይሁዳውያንን በመፍራቱ ምክንያት አልገሠጸውም:: በዚህ የዋህነት ጌታ ለኒቆዲሞስ እምነቱን እንዲያውጅ ከስቅለቱ በኃላ የጌታን መቃብር በማዘጋጀት ድርሻ እንዲኖረው ኒቆዲሞስን መራው::

እግዚአብሔር ከየዋህ ሰው ጋር መልካም ግንኙነት በቀላሉ መመሥረት ይቻላል፣ ማንኛውም ሰው ከእርሱ ጋር በመልካም ድርጊት ውስጥ መሆን ይችላል:: ስምምነቶች የስሜት መነቃቃት ወይም የስሜት መጎዳት አያገኘውም:: በአሳብ የተለየ ቢሆንም ማንም ከእርሱ ጋር ቢከራከር እንደማይከፋ እርግጠኛ በመሆን ወይም ስሕተቶችን የራሱ አድርጎ በመቀበል እፎይታ እንዲሰማው ያደርጋል::

ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው አብርሃም እና ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉት ክርክር በእሳት ስለነደደችው



ሰዶም አባታችን አብርሃምን ከእርሱ ጋር ያወያየው አምላካችን እግዚአብሔር እጅግ የዋህ ነበር::

አብርሃም ለእግዚአብሔር «በውኑ ጻድቃን ቢገኙ....ይህ ከአንተ ይራቅ ጻድቁን ከኃጢአተኛ ጋር ትገድል ዘንድ እንደዚህ ያለው አድራጎት ከአንተ ይራቅ:: የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን?»/ዘፍ 18÷23-25/ አለው:: እግዚአብሔርም ትዕግሥተኛ ነበር:: አብርሃምን በየዋህነት «በከተማይቱ ውስጥ አምሳ ጻድቃን ባገኝ ስፍራውን ሁሉ ስለእነርሱ እምራለሁ::» አለው እንጂ አልወቀሰውም:: ታዲያ አብርሃም ቀጥሩ ወደ አሥር እስኪቀንስ ድረስ ተከራከረ::

ዳግመኛም በየዋህነቱ እስራኤላውያን የጥጃ ምስል ባመለኩ እርሱም ሊያጠፋቸው በፈለገ ጊዜ ሙሴ እንዲ ለምነው ፈቀደለት፤ አለውም «ቁጣህ በሕዝብህ ላይ ስለምን ተቃጠለ? ግብፃውያንስ በተራራ መካከል ሊገድላቸው ከምድርም ፊት ሊያጠፋቸው ለክፋት አወጣቸው ብለው ስለምን ይናገራሉ? ከመዓትህ ተመለስ ለሕዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ» /ዘጸ 32÷11-12/ እግዚአብሔርም ለሙሴ ጥያቄ በየዋህነት መልስ ሰጠው ሕዝቡንም አላጠ ፋቸውም::

• የዋህ እና ቅን ሰው ልቡ ሰፊ እና ትዕግሥተኛ ነው::

ነቢዩ ሙሴ እንዲህ ዓይነት ሰው ነበር:: እህቱ ማርያም እርሱን በመቃወም በተናገረች እግዚአብሔርም በገሠጻት ጊዜ ሙሴ በእርሷ ቢከፋም ስለ እርሷ ጸለየ:: ወደ እግዚአብሔርም «አቤቱ እባክህ አድናት» /ዘኍ 12÷13/ በማለት ጮኸ ውብ ከሆኑት ምሳሌዎች መካከል በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ የልብ ስፋት እግዚአብሔር ሰጠው /1ነገ 4÷29/

ተብሎ ስለ ጠቢቡ ሰሎሞን የተነገረው ቃል አንዱ ነው፡፡

- **የዋህ ሰው ሁልጊዜ ደስተኛ ነው በማንም ላይም ፈጽሞ አይቆጣም፡፡**

ፈገግታው ጣፋጭ እና በሁሉም ሰው የሚወደድ የፊቱ ገጽታም እርሱን ለሚመለከተው ሁሉ ምቾት የሚሰጥ ሽጋ ነው፡፡ ከእርጋታው የተነœ በአስቸጋሪ ሁኔታ ድርጊቶችን አይፈጽምም በስሜት ወይም በሚገሥጽበት ጊዜም የድምፁን ቃና አይለውጥም፡፡

- **በመጥፎ አያያዝ ቢያዝም የዋህ ሰው አይቆጣም አይሰለችም ወይም አያማርርም፡፡**

ሁልጊዜ ለሌሎች ይቅርታ ማድረግን ይፈልጋል፡፡ ተግባራቸውን ያምናል ክፋትም አያስብላቸውም፡፡ በእርሱ ላይ ስለሚያደርጉ ጉዳቶች ምንም እንዳልተከሰተ ፈጽሞ አይናገርም፡፡ በውስጡ ምንም ዓይነት ኃዘን አይሰማውም፡፡ ከተናደደም ቁጣው ፈጥኖ ይጠፋል፡፡ ወደ ክፋትም አይለወጥም፡፡

- **የዋህ ሁልጊዜ ለቁጣ የዘገየ ነው፡፡**

ሐዋርያው ያዕቆብ እንደተናገረው «ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቁጣም የዘገየ ይሁን የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና»/ያዕ 1÷19/ የዋሁ ጌታችን «ለቁጣ የዘገየ» /ዮና 4÷2/ እንዲሁም «መሐሪና ይቅር ባይ» /መዝ 102÷8/ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

- **የዋህ ሰው በየምክንያቱ አይናደድም**

የዋህ ሰው ከተናደደም የሚናደደው ከባድ ለሆነ ነገር



እና በአብዛኛው ለእግዚአብሔር ሲል ነው፡፡ ንዴቱ ለራሱ ጉዳይ ለራሱ ክብር ሌሎቹ እንደሚያደርጉት ለራሱ መብትም አይደለም፡፡

ከተናደደ ቁጡ ወይም ስሜታዊ አይሆንም፡፡ ቁጣው የተቃውሞው እና ያለመደሰቱ መግለጫ ብቻ ነው ዘወትር ሰላማዊ ነው በቀላሉም አይቆጣም በበቀልም አይነድም፡፡

- **የዋህ ሰው ሰላማዊ ነው ራሱን ለመቀበል አይፈቅድም**

የዋህ ሰው ጌታ በ/ማቴ 5÷39/ እንዳዘዘው ክፉውን አይቃወምም አይበቀልምም፡፡ ሌሎች ይከራከሩለታል እርሱን የሚጎዱትንም ይሀን ደግ ሰው ለመጉዳት ምንም መጥፎ ነገር አላገኛችሁብትም በማለት ያልፉታል እንጂ፤ እርሱ ለራሱ ጠበቃ ባለመሆን የጸና ይሆናል፡፡ በማንም ላይ ክፉ ነገር አያደርግም፡፡ ከሚጎዱትም ጉዳትን ይቀበላል ፡፡ውስጣዊ ሰላም አለው፡፡ ስለዚህ አይከፋም ወይም ስሜታዊ አይሆንም ሊረብሸው የሚችል ውጪያዊ መከራና ችግር የለም፡፡

ቅዱስ ይስሐቅ «ተራራ መውጣት ቀላል እንዳልሆነ የዋህ ሰውን ለማስከፋት ማነœœት ቀላል አይደለም እንዳለ ው፡፡በማጭበርበር ሰላማዊ አያስመስልም አቀራረቡ እንደልቡ ነውና፡፡ ማንኛውም ማዕበል ቢያናውጠው እንደማይሰነጠቅ ዓለት ነው፡፡

- **የዋህ ሰዎች ሁልጊዜ ታጋሾች እና ለራሳቸው መብቶች የማይከራከሩ ናቸው፡፡**

የዚህ ምሳሌ ነቢዩ ዳዊት ነው፡፡ በነቢዩ ሳሙኤል ንጉሥ ሆኖ ተቀብቶ ነበር /1ሳሙ 16÷13/ ወደ እርማቴም ሄደ ሳሙኤል ግን ግዛቱን አልሰጠውምያለ ግዛት ንጉሥ ሆኖ ቆየ

አስቀድሞ እንደተባለው የዋህነት፣ ቸርነትን፣ ደግነትን እና ሰላማዊነትን ያመለክታል:: ችግሩ የዋህ ሰውን እንደማይንቀሳቀስ አካል የደካማ ስብእና ባለቤት ሊሆን ይችላል ብለው በማሰብ አንዳንድ ሰዎች የዋህነትን በተሳሳተ አቅጣጫ ሊረዱት ይችላሉ:: ሰዎች የመሳለቂያ እና የመዝናኛ ርዕስ ሊያደርጉት ይችላሉ:: በምንም ነገር ውስጥ ተሳትፎ የሌለው ሰነፍ ሰው አድርገው ሊቆጥሩት ይችላሉ:: ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶችን ፣ የቅዱሳን አባቶችን እና ሐዋርያት ታሪክ የሚጻረር የተሳሳተ መረዳት ነው:: በእርግጥ የዋህ ሰው ልበቀና እና የረጋ ነው ይህም ግን የእውነታው ግማሽ ነው...::

ሌላው የእውነታው ግማሽ የዋህነት ወኔንና ጀግንነትን አይቃረንም፤ ነገር ግን ከሰማይ በታች ሊሆን ነገር ሁሉ ጊ ዜ አለው::መጽሐፍ ቅዱስ «ለመትከል ጊዜ አለው የተተከለውንም ለመንቀል ጊዜ አለው....ዝም ለማለት ጊዜ አለው ለመናገርም ጊዜ አለው» ነገርግን የዋህ ሰው መቼና እንዴት ምን መሥራት እንዳለበት ያውቃል:: /መክ 3÷1/ ይላል::

ቅዱስ እንጦንስ እጅግ ጠቃሚ ስለሆኑት ምግባራት በተ ጠየቁ ጊዜ ጸሎት ጾም እና ዝም ማለትም ጠቃሚ ምግባራ ት ቢሆኑም እጅግ ጠቃሚው ምግባር በጥንቃቄ መሥራ ትን መረዳት ነው ብሎአል::

ልበ የዋህነት በየዋህ ሰው ልብ ውስጥ በብዛት የሚገኝ ባህርይ ነው:: ነገር ግን ይህ ልበ የዋህነት በጀግንነት እና በደፋርነት እንዲሠራ ወይም ለእውነት እንዲመሰክር ሲጠራ ው በየዋህነት ሰበብ ማፈግፈግ የለበትም::



አስፈላጊ በሆነ ጊዜ አንድን ነገር ከመሥራት መሸሽ የዋህነቱ ውሸት እንደሆነ ግዴለሽ ብቻ እንደሆነ ወይም በአጠቃላይ የየዋህነት ወይም የመንፈሳዊነት የተሳሳተ ግንዛቤ እንዳለው ያረጋግጣል::

መንፈሳዊነት ሌሎቹን ምግባራት ሁሉ በመተው አንድ ምግባር ብቻ መያዝ ሳይሆን የሁሉም ምግባራት በስምምነትና በውህደት እና በጽናት መጣመር ነው::

ክብር ለርሱ ይሁንና በጌታችን በክርስቶስ ዘንድ ምኞታችን ሁሉ አለ:: ኢየሱስ ክርስቶስ የዋህ በልቡም ትሑት ነው የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም፤ የሚጤስን የጥዋፍ ክርም አያጠፋም::/ማቴ11÷29፣12÷20/ይሁንና አይሁድ ቤተ መቅደስ ውስጥ በመሸጥና በመለወጥ መቅደሱን እንዳረከሱት ባየ ጊዜ የሚገዙትንና የሚሸጡትን ሁሉ አስወጣ:: የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች የርግብ ሻጮችንም ወንበሮች ገለበጠና «ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላች ተብሎ ተጽፎአል እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት» አላቸው::/ማቴ 21÷12-13. ዮሐ 2÷14-16/

ጌታ በየዋህነት ስም የአባቱን ቤት የንግድ ቤት እንዲ ያደርጉት ይተዋቸው ዘንድ ይችላልን? አይችልም:: የዋህነትን ከተቀደሰ ቅንአት ጋር አዋህዶ ይዟል:: ደቀመዛሙርቱም «የቤትህ ቅናት ይበላኛል» /ዮሐ 2÷6-17/ ተብሎ እንደተጻፈ አሰቡ:: የዋሁ ክርስቶስ ቤተ መቅደስን እንዳጠራ ሁሉ ጸሐፍትን እና ፈሪሳውያንንም ገስጾአል::

ለእያንዳንዱ ዓላማ ከሰማይ በታች ጊዜ አለው፣ ጸጥ ለማለት ጊዜ አለው፣ ለማስተማርም ጊዜ አለው፣ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ስሕተት በሆነ ትምህርታቸው ሰዎችን ወደ

ተሳሳተ አቅጣጫ ለመውሰድ ተጠቅመዋል፤ ስለዚህ ታላቁ መምህር አጋለጣቸው፤ በአዲሱ የክርስቲያን ማኅበረሰብ ውስጥም በሙሴ ወንበር ላይ እንዲቀጥሉ አልፈቀደላቸውም:: እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳዊያን መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም ትከለክላላችሁ /ማቴ23÷3/ አላቸው:: መንግሥተ ሰማያትን እንዲዘጉ በየዋህነት ስም ይተዋቸው ዘንድ ይችላልን?

የዋህነት ታላቅ ምግባር ነው ነገር ግን እዚህ ላይ ምሳሌያችን ክርስቶስ ራሱ እንዳደረገው ከተቀደሰ ቅናት እና ለእውነት ከመመስከር ጋር የተዋሀደ ነው::

ለእውነት መመስከር እግዚአብሔር እኛ እንድንሠራው የሚፈልገው ጠቃሚ ነገር ነው:: ቃሉን በነቢዩ ኤርምያስ እንደበት እናነበዋለንና «በኢየሩሳሌም መንገድ እየተመላለሳችሁ ሩጡ፤ ተመልከቱም፤ እወቁም፤ በአደባባይዋም ፈልጉ ፍርድን የሚያደርገውን እውነትንም የሚሻውን ሰው ታገኙ እንደሆን ይቅር እላታለሁ::»/ኤር 5÷1/ ጌታም ለደቀመዛሙርቱ «ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» /ሐዋ 1÷8/ ብሏቸዋል::

የዋህነት ለእውነት ለመመስከር እንቅፋት ሊሆን ይችላልን? እግዚአብሔር ከልክሏል የሐዋርያው የጳውሎስ ምሳሌነት አለን ኬፋ ከአሕዛብ ጋር አብሮ ይበላ ነበርና በመጡ ጊዜ ግን ከተገረዙት ወገን ያሉትን ፈርቶ ያፈገፍግ በነበረበት ጊዜ ጳውሎስ በኬፋ ላይ ባደረገው ድርጊት ላይ በግልጽ ይታይ ነበር:: «በመጣ ጊዜ ፊት ለፊት ተቃወምሁት ይፈረድበት ዘንድ ይገባ ነበርና....ኬፋን አንተ አይሁዳዊ



ሳለህ በአይሁድ ኑሮ ያይደለ በአሕዛብ ኑሮ ብትኖር አሕዛብ በአይሁድ ኑሮ ሊኖር እንዴት ግድ አልኃቸው?/ገላ 2÷1-14/ ብሎታል::

ተመልከት ያንን ያደረገው ማን ነው? ቆሮንቶሳዊያንን በመገሠጽ «እኔም ራሴ ጳውሎስ በእናንተ ዘንድ ፊት ለፊት ሳለሁ ትሑት የሆንሁ ከእናንተ ግን ብርቅ የምደፍራችሁ በክርስቶስ የዋህነትና ገርነት እመክራኋለሁ::» /2ቆሮ 10÷1/ ያለው የዋሁ ጳውሎስ ነው:: ያ የዋህ ሰው በመንፈሳዊ ልጆቹ ፊት ራሱን ዝቅ አድርጎ የቆመ ትችቱን እንደ ጀግንነት በመቁጠር በአገልግሎትና በዕድሜ ታላቅ የነበረውን ሐዋርያውን ኬፋን ለመገሠጽ በወቅቱ አስፈላጊ መሆኑን ተመልክቷል:: የዋህነትን ለእውነት ከመመስከር ጋር አጣምሮታል ምክንያቱም የዋህነት ለሌሉች ምግባራት እንቅፋት አይሆንምና::

ሌላው ምሳሌ የዋህነትን ከወኔ እና ከድፍረት ጋር አዋህዶ የያዘው አበ ብዙኃን አብርሃም ነው::ያለምንም ጥርጥር አብርሃም የዋህ ነበር:: የኬጢ ልጆችን ሥራን ይቀብርበት ዘንድ የመቃብር ርስት እንዲሰጡት ራሱ ሲለምን እና የዋለንና የኬጢ ልጆችም ለአብርሃም መለሱ አሉትም«ጌታ ሆይ ስማን አንተ በእኛ መካከል ከእግዚ አብሔር አለቃ ነህ:: ከመቃብር ስፍራችን በመልካሙ ቦታ ሬሳህን ቅበር::» አብርሃም ተነሳ ለምድሩ ሕዝብም ለኬጢ ልጆች ሰገደ:: /ዘፍ 23÷6-7/

የዋሁ አብርሃም በአራቱ ነገሥታት እና በአምስቱ ነገሥታት መካከል በነበረው ጦርነት ወንድሙ ሎጥ እንደተማረከ በሰማ ጊዜ «በቤቱ የተወለዱትን ሦስት መቶ

አሥራ ስምንት ብላቴኖቹን አሰልፍ ... ፍሊጋቸውንም ተከትሎ እስከ ዳን ድረስ ሄደ...እስከ ሖባ ድረስ አሳደዳቸው...ከብቱንም ሁሉ አስመለሰ ደግሞም ወንድሙን ሎጥንና ከብቶቹን ሴቶችንና ሕዝቡን ደግሞ መለሰ።» /ዘፍ 14÷14-16/ የአብርሃም ድፍረትና ወኔ የዋህነቱን እና ደግነቱን የሚቃወም ነበርን? እግዚአብሔርስ ከልክሏልን? ወጣቱ ዳዊት ከደፋሩ ጎልያድ ጋር መዋጋት ከጀግንነት እና ጥንካሬ ጋር የተዋሀደ የየዋህነት ሌላ ምሳሌ ነበር።

ዳዊት የዋህ እንደነበር ምንም ጥርጥር የለውም። እርጋታ ያለው እረኛ በገና መልካም አድርጎ የሚመታ፣ ቀይ ዓይኑም የተዋበ፣ መልኩም ያማረ ነበርና /1ሳሙ 16÷12-22/። ነገር ግን የወንድሞቹን የነፃነት ዜና ለመስማት ወደ ሰልፍ በሄደ ጊዜ ጎልያድ የእስራኤልን ሠራዊት እንደናቀ ሰማ እያንዳንዱ ሰውም ሁሉም ዝም እንዳሉና እንደፈራ ተመለከተ።

ቅናት አቃጠለው በድፍረት በኃይል እና በእምነት «ስለ እርሱ የማንም ልብ አይውደቅ»ብሏል ሄዶ ሲዋጋውም ፍቃደኛ ሆኗል። ለጎልያድም «እግዚአብሔር ዛሬ አንተን በእጄ አሳልፎ ይሰጣል።»/1ሳሙ. 17÷32-46/ ሲል አስጠንቅቋል።

ይህን ሁሉ ጥንካሬ እና ጀግንነት ቢያሳይም የዋህነቱን አላጣም ሳኦል ባሳደደው ጊዜም ሳኦልን «የእስራኤል ንጉሥ ማንን ለማሳደድ መጥቶአል? አንተስ ማንን ታሳድዳለህ? የሞተ ውሻን ወይስ ቁንጫን ታሳድዳለህን? /1ሳሙ 24+14/ አለው።

ለእግዚአብሔር ሲል በተቀደሰ ቅናት የሚገሥጸው እና



የሚወቅሰው ነቢዩ ሙሴ ሌላ የየዋህ ሰው ምሳሌ ነው። ሙሴ በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው እንደነበር የሚቃወም ማንም የለም። /ዘኁ 12+3/ ነገር ግን ያ የዋህ ሰው ከተራራው ወርዶ ወደ ሰፈሩ ሲቀርብ ጥጃውንም ዘፈኑንም አየ የሙሴም ቁጣ ተቃጠለ ጽላቶቹንም ከእጁ ጥሎ ከተራራው በታች ሰበራቸው። የሠሩትንም ጥጃ ወስዶ በእሳት አቃጠለው እንደትቢያም እስኪሆን ድረስ ፈጨው በውሃውም ላይ በተነው.... /ዘጸ 32÷19-20/ ።

ሙሴም አሮንን ይህን ታላቅ ኃጢአት ታመጣበት ዘንድ ይህ ሕዝብ ምን አደረገህ በማለት ገሠጸው። በመጨረሻም አሮን ተረበሸ ፈራም እንዲህም አለ «ጌታዬ ሆይ ቁጣህ አይቃጠል ይህ ሕዝብ ክፉትን እንዲወድድ አንተ ታውቃለህ....እኔም ከእናንተ ወርቅ ያለው ሰው ከእርሱ ሰብሮ ያምጣልኝ አልኳቸው ሰጡኝም በእሳትም ላይ ጣልሁት ይህም ጥጃ ወጣ።» /ዘጸ 32÷22-24/ ሙሴም የዋህነቱ ሕዝቡን ከመቆጣትና እና ከመቅጣት እንቅፋት አልሆነበትም።

- **የዋህነት ከጠንካራ ስብዕና እና ተጽዕኖ ግፊት ጋር አይጋጭም።**

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የዋህ ነበር ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ ጠንካራ አቋም እና በሌሎች ላይ ታላቅ ተጽዕኖ የማድረግ ኃይል አለው። ነገር ግን በሰው ደረጃ ምሳሌ እንውሰድ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን። ከአሁን በፊት ስለ ሐዋርያው ቅዱስ ሥራ ተነጋግረናል ነገር ግን አሁን ስለ ስብእናው እና በሌሎች ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ እንነጋገር።

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ስለ ቅዱስ ጳውሎስ መታሰር እናነባለን:: እርሱም ስለ ጽድቅና ራስን ስለመግዛት ስለሚመጣውም ኩነኔ ሲነጋገር ሳለ ፊልክስ ፈርቶ «አሁንስ ሂድ በተመቸኝ ጊዜ ልኬ አስጠራሃለሁ» /ሐዋ 24÷25/ ብሎ መለሰለት::

በተጨማሪ ጳውሎስ እንደ እስረኛ በአግሪጳ ፊት ቆሞ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ «ነቢያትን ታምናለህን? እንድታምናቸው አውቃለሁ» አግሪጳም ጳውሎስን በጥቂት ክርስቲያን ልታደርገኝ ትወዳለህን» አለው /ሐዋ 26÷27-28/ ጳውሎስም በኃይልና በክብር «በጥቂት ቢሆን ወይም በብዙ አንተ ብቻ አይደለህም ነገር ግን ዛሬ የሚሰሙኝ ሁሉ ደግሞ ከዚህ እስራት በቀር ወደ እንደ እኔ ይሆኑ ዘንድ ወደ እግዚአብሐ ሔር እለምናለሁ አለው» /ሐዋ 26÷29/ ይህንን ኃይል የዋህነት ይጻረራልን? በእርግጠኝነት አይጻረርም::

- አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ የዋህነት ስለ እውነት ከመከራከር ጋር አይጋጭም

የሻለቃው አይሁድ እንደዚህ በጳውሎስ ላይ የጮኹበትን ምክንያት ያውቅ ዘንድ እየገረፉ እንዲመረምሩት ባዘዘ ጊዜ በነበረው ክስተት ላይ በግልጽ ይታያል:: በጠፍርም በገረፉት ጊዜ ጳውሎስም በአጠገቡ የቆመውን መቶ አለቃ የሮሜን ሰው ያለ ፍርድ ትገርፉ ዘንድ ተፈቅዶላችኋልን? አለው....ሻለቃውም ይህንን በሰማ ጊዜ ወደ ጳውሎስ እውነታውን ለማወቅ ቀረበ ሊመረምሩት ያሰቡትም ከእርሱ ወዲያው ተለዩ:: የሻለቃውም ደግሞ ሮማዊ መሆኑን ባወቀ ጊዜ ፈራ:: /ሐዋ 22÷24-29/

ጳውሎስ ከመገረፍ ለማምለጥ ፈልጎ ነበርን? አልፈለገም



ነበር «አርባ ግርፋት አምስት ጊዜ ገረፉኝ» /2ቆሮ 11÷24/ ብሏልና:: ነገር ግን በዚህ ክስተት ውስጥ ለተወሰነ እውነት ተከራክሯል:: ለመቶ አለቃውም የሚወድቅበትን ጥፋት ገለ ጸለት:: ይህም የጳውሎስ የዋህነትን የሚጻረር አልነበረም:: አይሁድን ደስ ያሰኝ ዘንድ ወደ አይሁድ ራሳቸው ይፈርዱበት ዘንድ ጳውሎስን ለነርሱ ለማስረከብ በፈለገ ጊዜ እንደገና ተከስቷል:: ነገር ግን ጳውሎስ ለመብቱ በጽናት ተከራከረ:: እፈረድበት ዘንድ በሚገባኝ በቄሳር ፍርድ ወንበር ፊት ቆሜአለሁ....ወደ ቄሳር ይግባኝ ብዬአለሁ አለ:: ፊስጦስም «ወደቄሳር ይግባኝ ብለሃል ወደ ቀሳር ትሄዳለህ» /ሐዋ 25÷9-12/ ብሎ መለሰለት::»

በእርግጥ ቅዱስ ጳውሎስ አይሁድን አልፈራም ነበር ነገርግን ወደ ሮም ወደ ቄሳር በመሄድ በዚያም ለመስበክ ነበር ዓላማው በምክንያቱ ጌታ በአጠገቡ ቆሞ «ጳውሎስ ሆይ በኢየሩሳሌምም ስለ እኔ እንደመሰከርህ እንዲሁ በሮሜም ትመሰክርልኝ ዘንደ ይገባሃልና አይዞህ::» /ሐዋ 23÷11/ በማለት ተናግሮት ነበርና:: ጳውሎስ ምንም ስሕተት የሆነ ነገር ሳይናገር ሕጋዊ መከላከያ በመስጠት ለገዛ መብቱ የሚከራከረው ለዚህ ነው::

- የዋህነት ኃጢአተኛ ከስሕተት ወይም ከአደጋ ለመዳን ከማስጠንቀቅ አይከለክልም::

ሐዋርያው ይሁዳ በመልዕክቱ «አንዳንዶች ተከራ ካሪዎችንም ውቀሱ አንዳንዶችንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ:: አንዳንዶችንም በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳን እየጠላችሁ በፍርሃት ማሩ::» /ይሁዳ 23/ እንዳለው::

ሕገወጥ በሆነ ጋብቻ ለማግባት ከዘመድ ጋር ለመጋባት

የሕግ ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ለማግባት ሃማኖቱን በመለወጥ ወይም በዓለማዊ ጋብቻ ለማግባት የወሰነ ጓደኛ ወይም ዘመድ እንደተመለከትህ አስብ፤ በየዋህነት ሰበብ እየሠራው ያለው ነገር ስሕተት መሆኑን ከማስጠንቀቅ ትታቀባለህን? አትታቀብም:: ትመክረው ዘንድ ይህ የአንተ ሥራ ነው:: ነገር ግን ይህን ስታደርግ እርሱን ሳትጎዳ ወይም ትዕቢትን በርሱ ላይ ሳታሳይ በሰላም ይሁን:: ዝም ካልህ ዝምታህ ስህተት ነው::

የዋህነት በማኅበረሰብ ውስጥ እንደ ሬሳ ሆኖ መኖር ማለት አይደለም:: የራስህ አቋም ሊኖርህ ይገባል ነገር ግን መጥምቁ «ለአንተ ትሆን ዘንድ አልተፈቀደም::» /ማቴ 14÷4/ በማለት እንዳደረገው ራስህን በአንድ ቃል ለመግለጽም እንኳን በየዋህነት አድርገው::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ስለዚህ ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በእንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሠጽ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትጉ::/ሐዋ20÷31/ብኋል::የዋህነቱ እያንዳንዳቸውን በትሕትናና በእንባ ከመገሠጽ አልከለከለውም::

አንድ ሰው አስቸጋሪ ቃል ቢናገርም እንኳን....ሰዎች ከየዋህ ሰው ምንም ዓይነት አስቸጋሪ ቃል አዘውትረው አይሰሙም:: ስለዚህ አንድ ቀን ይህ ሲከሰት ለዚህ ነገር ጠንካራ አቋም ያለው ሰው እንዳለ እርሱ የተናገረው ቃልም በነርሱ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ያውቃሉ::

የዋህ ሰው ጌታ ለደቀመዛሙርቱ «ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» ሲል ከተናገረው ትእዛዝ /ሐዋ 1÷8/ ሊሸሽ ይችላልን? በእርግጥ ይህን አያደርግም:: አስፈላጊ በሆነ ጊዜ አንድ ሰው ለእውነት ይመሰክራል::



አንድ ሰው አንደን ሰው ከተከሰተበት ጥቃት ለማዳን እድል አጋጣሚ ቢኖረው በየዋህነት ሰበብ አያደርግምን? ይህ የኔ ሥራ አይደለም:: ያንን የማደርገው ምን ለማግኘት ነው? ብቻዬን ተውኝ ሊል ይችላልን? ወይስ በየዋህነት እርሱን ለማዳን ደፍሮ እርምጃ ይወስዳል? በዚህ መንገድ ጌታ በኃጢአት ተይዛ የነበረችውን ሴት በድንጋይ ከመወገር አድኗታል:: ሊወግሯት የፈለጉአትን ሰዎች «ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት» ብሏቸዋል:: ይህንንም ኃጢአታቸውን ሳይገልጽ በምድር ላይ በመጻፍ በየዋህነት ተናገር::

አንዳንዶች የዋህ ማንንም ሊያወግዝ ይችላል? ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ? ብለው ይጠይቃሉ አዎን የዋህ በልቡም ትሑት በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ብዙ ምሳሌዎች አሉ::/ማቴ 11÷29/ «ዓለም በልጁ እንዲፈርድ ነው እንጂ በዓለም እንዲፈረድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውም» ለአይሁድም እናንተ ሥጋዊ ፍርድን ትፈርዳላችሁ እኔ በአንድ ሰው ስንኳ አልፈርድም ቢልም ከዚህ በኋላ ወዲያውኑ ፈጥኖ «እኔ ብፈርድ ፍርዴ እውነት ነው::»/ዮሐ 8÷15-16/ ብሏል:: ለኃጢአተኛዋ ሴትም «እኔም አልፈርድብሽም::»/ዮሐ 8+11/ ቢላትም በብዙ አጋጣሚዎች በብዙዎች ላይ ፈርዷል /ማቴ 23/ የካህናት አለቆችንም «የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ትወሰዳለች ብሎ ፈርዶባቸዋል:: የጌታን ስቅለት በተመለከተ «ጌታ ሆይ ይህ ከቶ አይደርስብህም» ብሎ ጴጥሮስ በተናገረው ጊዜ ገሥጾታል:: /ማቴ 16÷23/

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀመዝሙሩ ለጢሞቴዎስ «ሌሎቹ ደግሞ እንዲፈሩ ኃጢአት የሚሠሩትን በሁሉ ፊት

ገሥጻቸው::» /1ጢሞ 5÷20/ ብሎታል::አሁን ክርስቶስ እና ይህ ሐዋርያ ሲፈርዱ አይተሃል ጳጳሳትም ይህን ያደርጋሉ:: በአንዳንድ አጋጣሚዎች ውስጥ የዋህ ሰው ልክ በጻድቁ በኢዮብ እና በጓደኞቹ ታሪክ ውስጥ ኤሊሁ እንዳደረገው ለመናገር ግዴታ ያለበት ዝም ማለትም የማይችል ሆኖ ራሱን ያገኘዋል::

አራተኛው የኢዮብ ጓደኛ ኤሊሁ በኢዮብ እና በሦስቱ ጓደኞቹ መካከል ያሉትን ውይይቶችን በሚያካትቱት 28 ምዕራፎች ውስጥ ዝም ብሏል ኢዮብ ራሱን ጻድቅ እንዳደረገ አይተው ጓደኞቹ መልስ መመለስን ሲተው መጽሐፍ ቅዱስ «ከራም ወገን የሆነ የቡዛዊው የባርክኤል ልጅ የኤሳሁ ቁጣ ነደደ ከእግዚአብሔር ይልቅ ራሱን ጻድቅ አድርጎ ነበርና ኢዮብን ተቆጣው::

ደግሞም በኢዮብ ፈረዱበት እንጂ የሚገባ መልስ ስላላገኙ በሦስቱ ባልንጀሮቹ ላይ ተቆጣ» ይላል:: /ኢዮ 32÷2-3/ ኤሊሁ ግን ከእርሱ ይልቅ ሽማግሌዎች ነበሩና ከኢዮብ ጋር መናገርን ጠብቆ ነበር::

ኤሊሁም በነዚህ በሦስቱ ሰዎች አፍ መልስ እንደሌለ ባየ ጊዜ ቁጣው ነደደ:: ስለዚህም ተናገረ እንደዚህም አለ «እኔ በዕድሜ ታናሽ ነኝ እናንተ ግን ሽማግሌዎች ናችሁ ስለዚህ ሰጋሁ እውቀቴን እገልጥላችሁ ዘንድ ፈራሁ እንደዚህም አልሁ ዓመታት በተናገሩ ነበር፤ የዓመታትንም ብዛት ጥበብን ባስተማረች ነበር፤ ነገር ግን በልባቸው ጠቢባን እንዳልሆኑ ባየ ጊዜ ኢዮብን ተናገረው ገሠጸውም በእግዚአብሔርም ቃል ተሞልቷልና:: ኢዮብ ያልተከራከረው ብቸኛው ሰው እርሱ ብቻ ነው:: /ኢዮ 32÷37/



አንዳንድ ሰዎች ለመፍረድ ሥልጣን እና ኃላፊነት አላቸው ይህ ከየዋህነት ጋር አይጋጭም:: ቤተሰቦች መንፈሳዊ አባት መምህር በተማሪዎቹ ላይ አለቃ በበታቾቹ ላይ.... እነዚህ መካከል ናቸው:: ዔሊ ልጆቹ የእርግማን ነገር እንዳደረጉ አውቆ አልከለከላቸውም ስለ ኃጢአቱ በእግዚአብሔር እንደተፈረደበት አስታውስ /1ሳሙ 3/

መጽሐፍ ቅዱስ ከሴሰኞች እና ጣዖትን ከሚያመልኩ ጋር ኅብረት እንዳይኖረኝ እያዘዘኝ:: /1ቆሮ6÷1/ እኔ ግን እነዚህን አልፈርድባቸውም እላለሁን?! ከእነርሱስ ጋር ምንም ሕብረት ባኖረኝ ይህ በእኔ ላይ ፍርድ ሊያስከትል ይችላልን? በተመሳሳይ መንገድ ከአባተቶች ሐዋርያት ሃይማኖትና ትምህርት የወጡትን እንዳንቀበል ሐዋርያው ዮሐንስ እንዳለው «ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና::» /2ዮሐ1÷10-12/ በየዋህነት ስም እነዚህን እንቀበላለን? ሐዋርያው «የአንዳንድ ሰዎች ኃጢአት የተገለጠ ነው ፍርድንም ያመለክታል»/1ጢሞ 5÷24/ ይላል:: የምትፈርድባቸው አንተ ሳትሆን ሥራቸው ነው:: አንተ እነርሱን በየዋህነት አለመቀበል ብቻ ነው የሚጠበቅብህ::

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# ራስን መግዛት

በመንፈስ የሚኖር ሁሉ የመንፈሳዊ ሕይወት ፍሬ የሆነው ራስን መግዛት ይኖረዋል። ታዲያ ራስን መግዛት ምንድር ነው? እርሱስ እንዴት ይገኛል?

ራስን መግዛት የሥጋ፣ የስሜቶች፣ የአንደበት፣ የአእምሮ፣ የልብ፣ የሙያ፣ የእጅ....ንጽሕናን እና እነዚህን ሁሉ መቆጣጠርን ያጠቃልላል።

## የአንደበት ንጽሕና

- የአንደበት ንጽሕና ማለት መጥፎ እና ከንቱ ቃልን ማስወገድ ማለት ነው።

ስለዚህ ጌታ «ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል።» /ማቴ. 12÷36/ ብሏል። እንዲህ ዓይነቱንም ቃል የሚያረክስ ብሎ ይቆጥረዋል።

«ሰውን የሚያረክሰው ወደ አፍ የሚገባ አይደለም ከአፍ የሚወጣው ግን ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው።» /ማቴ 15÷11/ ብሏልና። በእርግጥ ንጹሕ ሰው በምንም ቃል አይረክስም።

- ንጹሕ አንደበት የስድብ ወይም የፌዝ ቃል አያሰማም

ንጹሕ ሰው ሌሎችን ያከብራል ማንንም በኀጂ ቃል ወይም የንቀት በሆነ በሚያዋርድ ወይም በፌዝ ቃል አይጎዳም። ንጹህ አንደበት ትሁት ሰው አክባሪ ከመናገሩ በፊትም እያንዳንዱን ቃል የሚመዝን የተከበረ አንደበት በመሆኑ ምክንያት የማንንም ስም አያጠፋም ወይም አያስደነግጥም። ከዚህ በተጨማሪ ተፈጥሮ በመሆኑ ንጹሕ



ቃልን ይጠቀማል እንጂ ንጹሕ ቃል ለመናገር ምንም ዓይነት ጥረት አይፈልግም።

- ንጹህ አንደበት ሥነ ምግባር የጎደለው ወይም የብልግና ቃላትን አይናገርም

ለምሳሌ አስቀያሚ የተራከቦ ቃላትን ወይም ታሪኮችን ወይም ቀልዶችን ሊናገር ከሌሎችም ስለነዚህ ሊሰማ እንኳን አይችልም። ንጹሕ አንደበት ያለው ሰው ጋጠወጥ ዝማሬ አይዘምርም ይልቁንም በቤቱ ብቻውን ሲሆን ስለሠራው ክፉ ሥራ ይጸጸታል እንጂ እስከዚያ ደረጃ ድረስም ራሱን አያቀልም ። ትሕትናው የጨዋነት ሥርዓቶቹን የሚቃወም ቋንቋ ከመጠቀም ይጠብቀዋል።

- ንጹሕ አንደበት የትሕትና ንግግርን እና ቃለ ምልልስን ለመምራት ያገለግላል።

ለምሳሌ ተናጋሪን አይረብሽም። በተወሰኑ ቃላት ጣልቃ በመግባት አይናገርም ወይም በውይይት ውስጥ ድምፁን ከፍ አያደርግም የራሱን የአሳብ ነጥብ ለማጽናት ማንንም ፍጹም አይንቅም በክርክር መሐልም አንድን ሰው አይሰድብም። ትሕትናው ይህንን እንዲያደርግ አይፈቅድለትም።

ንጹሕ አንደበት ያለው ሰው በክርክሮቹ ውስጥ ሁልጊዜ ለስሜቱ አይሸነፍም ግላዊ ጉዳዮችንም አያነሳም። ንግግሩ ምክንያታዊ እና ተገቢ ነው። በጉዳዩ የመወያያ ርዕስ ላይ ትኩረት ያደርጋል እንጂ የሌላውን ወገን አላዋቂነት ወይም የመረዳት እጦት አይገልጥም እነዚህን የችሎታ ማነሶችም ገልጦ አያሳይም።

• የጽሑፍ ንጽሕና የአንደበት ንጽሕና ያጅባል

ይህ ሲባል አንድ ንጹሕ ሰው ከላይ የተገለጹትን ነገሮች ሁሉ በጽሑፎቹ ውስጥም ይመለከታቸዋል ማለት ነው:: የማንንም ስም የሚያጠፋ ወይም ማንኛውንም ሰው የሚያስቀይም እና የሚሳደብ ምንም ነገር አይጽፍም:: ለሁሉም ሰው ዋጋ ፣ክብርም ይሰጣል እንጂ ስለ ማንም ሰው ምንም ውሸት ነገር አይናገርም:: ዝናቸውን እንደ እምነት ይወስዳል ብዕሩንም በእነርሱ ላይ ሊቀስር አይፈቅድም:: በሚጽፈው በማንኛውም ነገር ላይ የታመነ ነው::

ይህ እኛን ወደ ንጹህ እና ወደ ሚታመን ሂስ ያመጣናል:: አግባብ ያለው ትችት ንጹሕ እና በገሃድ የሚታይ ነው:: እውነትን ብቻ የሚፈልግ ሲሆን በነገሮች ላይ ፍርድ የሚሰጠው ተቀባይነት ስለሌላቸው ካስወገዳቸው ነጥቦች በፊትም ጥሩ ጥሩ ነጥቦችን ይገልጻል:: ስለዚህም ለእያንዳንዱ ሰው የየራሱን መብት ይሰጣል:: እግዚአብሔር ብቻ የሚያውቀውን የሰዎችን አሳብ እና ውስጣዊ ዓላማ አይመረምርም::

• የአንደበት ኃጢአት ሁለተኛ ኃጢአት ነው::

ማለትም ንጹሕ ያልሆነ አንደበት ኃጢአት ይህንን የሚያስከትለው የሌላ ኃጢአት ውጤት ነው፣ እርሱም የልብ ንጹሕ አለመሆን:: ጌታ «መልካም ሰው ከልብ መልካም መዝገብ መልካሙን ያወጣል ክፉ ሰውም ከልብ ክፉ መዝገብ ክፉውን ያወጣል» /ሉቃ 6÷45/ ብሏልና ::

## የልብ እና የአእምሮ ንጽሕና

ይህ ንጽሕና የእያንዳንዱ ውጪያዊ ንጽሕና መሠረት



ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ «አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና::» /ምሳ 4÷23/ ይላል:: የልብ ንጽሕና የስሜቶችን የደስታዎችን እና የድርጊቶችን እንዲሁም የዕቅዶችን፣ የአሳቦችን እና የፍላጎቶችን ንጽሕና ያጠቃልላል::

ከአንድ ምንጭ እርሱም ከልብ ንጽሕና የአእምሮ ንጽሕና የአንደበት ንጽህና እና የስሜቶች ንጽሕና ይወጣል :: ስለዚህ አእምሮህ ንጹህ ባልሆነ መንገድ ሲባክን ካገኘኸው ፈጥነህ ተቃወመው ወደ ሌሎች የሰውነት ክፍሎች ከመሸጋገሩ በፊትም አቁመው:: አእምሮ ራሱን በአንደበት በስሜቶች ወይም በድርጊት አማካይነት ይገልጻልና::

• የልብ እና የአእምሮ ንጽሕና ከውስጠ ኅሊና ጋርም ደግሞ የተያያዘ ነው

ውስጠ ኅሊና የሚሠራው በውስጡ በተከማቹ አስተሳሰቦች ምስሎች ምኞቶች እና ስሜቶች አማካይነት ነው:: እነዚህ ሁሉ ንጽሕና አልባ ከሆኑ ከዘፍጥረት እንደተረዳነው ዛፍ እንደየወገኑ ፍሬ የሚያፈራ መሆኑን /ዘፍ 1÷1-12/ ውስጠ ኅሊናም ንጽሕና አልባ በሆኑ ህልሞች እና አስተሳሰቦች ቅርጽ ይገለጣል:: ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው የልቡን እና የአእምሮውን ንጽሕና በመንፈሳዊ ሥራዎች እና የአንደበት ስሜቶች እና የአካል ንጽሕና ምንጭ ሊሆኑ በሚችሉ በመንፈሳዊ ሥራዎች እና መልካም ነገርን እና ንጽሕናን በመውደድ ለመሙላት የበረታ ይሁን::

## የሥጋ ንጽሕና

የሥጋ ንጽሕና ሥጋን መጥፎ ከሆነ ሥጋዊ ደስታ እና

እንኳን ፋሽን መንፈስን ሊያሳምን አይችልም ወይም የፋሽን ዲዛይንነቱን ትዕዛዝ ከእግዚአብሔር ትእዛዛት የበለጠ ጠቃሚ አድርጋ መውሰድ የለባትም፤ ትሁት ሴት ከትሕትና ጋር ሊስማማ የማይችል ወይም ለአንድ ሰው መሰናከል ምክንያት ሊሆን የሚችል ማንኛውንም አዲስ ፋሽን ፈጽማ ልትቀበል አትችልም። በማንኛውም ቦታ ይህን ብታደርግም እንኳን በእንደዚህ ዓይነት ፋሽን ወደ ቤተ ክርስቲያን በተለይም በቅዳሴ ጊዜ አትገባም።

- **ንጽሕና የተወሰኑ የመዋቢያ እና የማጋጊያጫ ዓይነቶችን ይጻረራል።**

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ስለአካላዊ መዋቢያ ውበት እና የመንፈስ ውበት ይዋብ ዘንድ እንዴት እንደሚመረጥ የተናገረው ታዋቂ ቃል አለን። «በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለው..» /1ጴጥ 3÷4/

ራሷን ለማስዋብ ያላትን የሴቷን መብት አንቃወምም ነገር ግን ለሌላው እንቅፋት ላለመሆን በንጽህና የተወሰነ መሆን አለበት።

- **የአረማመድ መይም የአነጋገር ዘይቤ ንጽህናን የሚፃረር ሊሆን ይችላል።**

ንጽሕና ወደ ሁሉም የሕይወት ጠባይ የሚዘምት ሲሆን ኃጢአታማ ስሜቶችንም ሊቀሰቅስ የሚችል ማንኛውንም ጠባይን ያስወግዳል። አንዲት ሴት ስሜቱ የሚነሳሳ ወንድ ደካማ እና ንጽሕና የጎደለው ሰው ነው ልትል ትችላለች። ይህ እውነት ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ለደካማነታቸው ትኩረት ልትሰጠው እንዲሰናከሉ አለማድረግም



ይገባታል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እኛም ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ራሳችንንም ደስ እንዳናሰኝ ይገባናል።»/ሮሜ 15÷1/ ብሏል። የራሳችንን ንጽሕ ና እንድንጠብቅ ብቻ ሳይሆን በእኛ ምክንያት ንጽሕናቸውን እንዳያጡ ለሌሎችም ንጽሕና እንድንጠነቀቅ ጭምር ተጠይቀናል።

ይህንን በተመለከተ ጌታ «መሰናከሉን ለሚያመጣው ወዮለት ከእነዚህ ከታናናሾች አንዱን ከማሰናከል ይልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይጠቅመው ነበር።» /ማቴ 18÷7 ሉቃ 17÷1-2/ ብሏል።

ሴትም ትሁን ወንድ ንጽሕናቸውን በመቃወም ለጦርነት ከማነሳሳት ይልቅ ስለ ንጽሕናቸው ሊጨነቁ ይገባቸዋል። ኢንዲት ሴት በውበቷ እና በሴትነቷ የወንጀል ምክንያት መሆን የለባትም። ወንድም በፈተናዎቹ በስሜቶቹ እና በቃል ኪዳኖቹ ወይም ጓደኝነትን እና ወዳጅነትን በማራዘም ለወንጀል ምክንያት መሆን የለበትም። እነዚህ በአብዛኛው በንጽሕና ተጀምረው በተቃራኒው ይጠናቀቃሉ።

የአካል ንጽህና በአንድ ሰው የግል ክፍል ውስጥ የተጠበቀ መሆን አለበት ይህ አንድ ሰው በሚቀመጥበት ወይም በሚተኛበት መንገድ ላይ ይታያል አንድ ሰው በግል ክፍሉ ትሑት ከሆነ ከሌሎች ጋርም ሲገናኝ በውጪ እንዲሁ ይሆናል። ተቃራኒውም ደግሞ እውነት ነው ተግባር አስፈላጊ ነውና እርሱም ከውስጥ ይጀምራልና።

- **በጋብቻ ግንኙነቶች ውስጥም እንኳን ንጽሕናመጠበቅ አለበት**

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጽሕ ይሁን ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።» /ዕብ 13÷4/ ብሏል።

የጋብቻ ግንኙነቶች ተቀባይነት ያላቸው ናቸው። ነገር ግን በንጽሕና የተገደቡ ሊሆኑ ይገባል። ሐዋርያው «መኝታው ንጹህ ይሁን።» ያለው ይህን ነው። ይህ ስለ ስሜቶች ንጽሕና በተለይም ስለማየት፣ ስለመስማት እና ስለመዳሰስ ወደ መናገር ይመራናል።

## የማየት ንጽሕና

የማየት ንጽሕና ማንኛውንም ምኞታዊ እይታ በማስወገድ እውን ይሆናል። ምን አልባት ይህ ቅዱስ ዮሐንስ «የዓይን አምሮት» /1ዮሐ2÷16/ በሚል ቃል የገለጸውና ጻድቁ ኢዮብ «ከዓይኔ ጋር ቃልኪዳን ገባሁ እንግዲህስ ቆንጆይቱን እንዴት እመለከታለሁ?።»/ኢዮ 31÷1/ በሚል ቃል የገለጸው ሊሆን ይችላል። ጌታ ራሱ «ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያንጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል።»/ማቴ5÷28/ ብሏል።

• የልብ ንጹሕ አለመሆን የዓይኖች ንጹህ አለመሆን ያስከትላል።

በማንኛዋም ሴት ላይ የንጹሕ ሰው እይታ ንጹሕ ነው። እይታው ኃጢአታማ የሚሆነው ልቡ ሲረክስ ነው። ይህ በጲጥፋራ ሚስት ላይ ተከስቷል እርሷ «በዮሴፍ ላይ ዓይኗን ጣለች።»/ዘፍ39÷7/ያለምንም ጥርጥር ሁልጊዜ ትመለከተዋለች ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን በተለየ ዓይን በምኞት በተሞላ ልብ ትመለከተው ጀመር።



መልካሙንና ክፉን የምታሳውቀው ዛፍን በተመለከተ በእናታችን በሔዋን ላይም እንዲሁ ተከስቷል። ያዛፍ በገነት መካከል ነበር /ዘፍ. 3÷3/ ሔዋንም በአጠገቡ ሁል ጊዜ ታልፍ ታየውም ነበር፤ ነገር ግን ምኞት በሌለበት በንጹህ ልብ ነበር። ታዲያ ችግሩ መቼ ተጀመረ? እባብ ለሔዋን «ሞትን አትሞቱም....ዓይናችሁ ይከፈታሉ....እንደ እግዚ አብሔር ትሆናላችሁ።» /ዘፍ. 3÷4-5/ ባላት ጊዜ በእባቡ ፈተና የሴቲቱ ልብ ሲለወጥ ተጀመረ። ሴቲቱም በዚህ ጊዜ «ዛፉ ለመብላት ያማረ.... ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች።/ዘፍ. 3÷6/ ዛፉን ምኞት ባለበት ክፍ እይታ መመልከት ከየት መጣ? ከልብ የውስጥ ንጽህና መለወጥ የመጣ አይደለምን።

•የንጹሕ ሰው እይታ በምኞት የተሞላ ሳይሆን ዓይን አፋር ነው።

ይህ ለሥጋዊ እርካታ ብቻ የሚተገበር ሳይሆን ታላላቆችን ለማክበርም የሚተገበር ነው። ልጅ በፋክክር በአባቱ ላይ ዓይኖቹን ሳያነሳ በታላቅ አክብሮት አባቱን ይመለከታል እንጂ አባቱን በድፍረት ለማየት አይደፍርም።

ቅዱስ አባ ፒጊሚ በገዳም ውስጥ ከታላላቆቻቸው ጋር ለአሥራ ስምንት ዓመት የኖሩ ናቸው። ከታላላቆቻቸው ውስጥ አንዱን በሙሉ ዓይናቸው ፈጽመው አይተው እንደማያውቁ ተነግሮላቸዋል።

•አንዳንድ እይታዎች ንጽሕና የጎደላቸው ሲሆኑ ነገር ግን የተለያየ ዓይነት አላቸው

የዚህ ምሳሌዎች የሌሎች ሰዎችን አሳቦችና ምሥጢ

ሮች ለማወቅ ወይም በእነርሱ ላይ ተጽእኖ ለማሳደር የሰዎችን ልብ በጥልቀት የሚመረምር የስለላና የምርመራ እይታ ነው።

## የጆሮ ንጽሕና

ንጹሕ ጆሮ የሰው ወሬ በድብቅ የሚሰማ አይደለም። የሰው ወሬ በድብቅ የሚሰማ ጆሮ ያውቀው ዘንድ መብት የሌለውን ምሥጢር ለማወቅ ይሞክራል። የሌሎች ሰዎችን ግላዊ ጉዳዮች የሚሰርቅ እንዲህ ዓይነት ሰው መልካም ጠባይ ያለው አይደለም።

ሌላው ዓይነት ጆሮ በምኞት የተሞሉ ወሬዎችን ተራ ከቦአዊ ቀልዶችን ወይም ዘፈኖችን በመስማት ደስታ የሚያገኝ ነው። እንደዚህ ዓይነት ጆሮዎች ዘማዊ ጆሮዎች ናቸው። አንዳንድ ጆሮዎች ሐሜት ወይም ስለ ጠላቶቻቸው ውድቀት የሚወራ ወሬ በመስማት ደስታ ያገኛሉ። ይህ ንጽሕናን የሚቃረን የደስታ ዓይነት ነው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር «ጠላትህ ቢወድቅ ደስ አይበልህ በመሰናከሉም ልብህ ሐሴት አያድርግ እግዚአብሔር ያንን አይቶ በዓይኑ ክፉ እንዳይሆን...።» /ምሳ 24÷17-18/ ይላል።

## የእጅ ንጽሕና

ንጹሕ እጅ በመስረቅም ይሁን ከኪስ በማውጣት ወይም በጉልበት በመቀማት የሌላ ሰው የሆነውን ነገር አይወስድም።

ዳግመኛም ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ በተገኘ ትርፍ የሚደሰት እጅ በእርግጠኝነት ንጹሕ አይደለም። እንደዚህ ዓይነቱ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ገንዘብ የሚወድ» /1ኛ ጢሞ. 3÷3/ ተብሎ ተገልጿል። ይህም አራጣ አበዳሪ



በድሆች ላይ የሚጥለውን አራጣ ማበደርን፣ በገበያ ውስጥ የተወሰኑ የፍጆታ እቃዎችን መቆጣጠርን፣ ገዢዎችን ሊጎዳ የሚችል ከፍተኛ ዋጋ መጨመርን ያጠቃልላል። በእንደ እነዚህ ዓይነት ሥራዎች ይህን ሥራ የሚሠሩ ሰዎች እጆች በድሆች የድካም ፍሬ የተሞላ ይሆናል።

- ንጹሕ እጅ የልብ ንጽሕናን ይጠይቃል

ንጹሕ ሰው ለመጠየቅ በጣም ጠንቃቃ ነው ከተሰጠውም ለመቀበል ዓይን አፋር ነው። ከዚህ ጋር በሚቃረን መልኩ ይኖረው ዘንድ መብቱ ያልሆነውን ነገር ሊጠይቅ መብቱ ከሆነም ሊቀማ የሚችል ንጹሕ ያልሆነ ሰው ከዚህ ጋር የማይመሳሰል ነው።

ከተሰጠውም እንኳን ጥቂት መሆኑን በማየት ተጨማሪ ሊጠይቅ ይችላል እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ይኖራቸው ዘንድ መብታቸው አድርገው ለቆጠሯቸው ነገሮች እግዚአብሔርን የሚጠይቁ ናቸው። እንዲህ ዓይነቱ ከአባቱ ገንዘብ የሚደርሰውን ክፍል እንዲሰጠው የጠየቀው የጠፋው ልጅ ነበር /ሉቃ 15/።

ጐቀዺ